በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

አማርኛን በማስተማር ሂደት የአንብቦ መረዳት ክሂሎች አፈታተን የደብትና የላይ አግባብነትና ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት፤ በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች የ12ኛ ክፍል የሞዴል ፈተናዎች

አገኘሁ ተስፋ

ግንቦት 1990 ዓ.ም.

አማርኛን በማስተማር ሂደት የአንብቦ መረዳት ክሂሎች አፈታተን የይዘትና የላህይ አግባብነትና ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት፤ በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች የ12ኛ ክፍል የሞዴል ፈተናዎች።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አማርኛን በማስተማር ዘዴ
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ
አገኘሁ ተስፋ

ግንቦት፣ 1990 ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

አማርኛን በማስተማር ሂደት የአንብቦ መረዳት ክሂሎች አፈታተን የይዘትና የላህይ አግባብነትና ያጠያየቅ ዘይዎች ብቃትኛ በአዲስ አበባ ትምህርት ቢቶች የ12ኛ ክፍል የሞዴል ፈተናዎች

በ

አገኘሁ ተስፋ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ ማረጋገጫ

አማካሪ

ፈራማ

ፈራማ

ፈራማ

ፈራማ

ፈራማ

ማውጫ፣

አርዕስት	ገፅ
የሰንጠረዥ ዝርዝር	ሀ
ምስጋና	I
አጠቃሉ	II
ምዕራፍ አንድ	
1. መግቢያ	1
1.1 የጥናቱ ዳራ	1
1.2 የጥናቱ ጎላማ	2
1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት	3
1.4 የጥናቱ ወሰን	4
1.5 የቃላት(ሀረጋት) ትርጓሜ	4
1.6 በጥናቱ የጎሙተ ምሀረት አጠቃቀም	5
ምዕራፍ ሁለት	
2. ከለላ ድርጎናት	6
2.1 የቋንቋ ፈተና	6
2.2 የቋንቋ ፈተና አይነቶች	13
2.3 የትሎታ መለኪያ ፈተና	14
2.4 የትሎታ መለኪያ ፈተና ይዘት መስረቶች	15
2.5 አግባብነት	18
2.6 የአግባብነት አይነቶች	20
2.6.1 የይዘት አግባብነት	20
2.6.2 የላህይ አግባብነት	21
2.7 አንባቢ መረጃትን መፈተን	31
2.7.1 በአንባቢ መረጃት ፈተና ጥያቄምች ሊመዘኑ የሚችሉ ክሂሎች	31
2.7.2 በአንባቢ መረጃት ፈተና የምንባቦችና ያጠያየቅ ዘዴምች አመራረጥ	40
2.7.2.1 የምንባቦች አመራረጥ	40
2.7.2.2 ያጠያየቅ ዘዴምች አመራረጥ	41

ምዕራፍ ሶስት

3. የአጠናን ዘዴ 48
3.1. ተጠኝዎች 48
3.2 ናሙና 48
3.2.1 የፈተናዎች የክልልና የባለሙያዎች አመራረጥ 48
3.2.2 የትምህርት ቤቶችና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ..... 49
3.2.2.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ 49
3.2.2.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ 50
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች 50
3.3.1 ፕክሊስት 50
3.3.2 የ12ኛ ክፍል የእግርኛ መርሀ ትምህርትና የመማሪያ መፅሐፍ 51
3.3.2.1 መርሀ ትምህርቱ 51
3.3.2.2 የመማሪያ መፅሐፉ 51
3.3.3 መጠይቆች 52
3.3.3.1 የመምህሩ መጠይቅ 52
3.3.3.2 የተማሪው መጠይቅ 56
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ 57

ምዕራፍ አራት

4. የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ 58
4.1 የዖፅት አግባብነት 58
4.1.1 የምንባቦች አመራረጥ 58
4.1.2 የፕክሊስቱ ከሂሎች ውክልና በፈተናዎቹ ጥያቄዎች .. 66
4.1.3 በ12ኛ ክፍል መርሀ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ዖፅንኑት የቀረቡ ከሂሎች ውክልና በፈተናዎቹ ጥያቄዎች 86
4.2 የላህይ አግባብነት 94
4.3 ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት 98

ምዕራፍ አምስት

5. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና ጥቆማ 107
5.1 ማጠቃለያ 107
5.2 መደምደሚያ 111
5.3 ጥቆማ 113
ዋቢ ፅሑፎች 116
አባሪዎች 121
አባሪ ሀ በቸከሊስቱ የተለዩት የአንብቦ መረዳት ክሂሎች 121
አባሪ ለ በ12ኛ ክፍል መርሀ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ይዘትንት የተመረጡ የንባብ ክሂሎች 123
አባሪ ሐ የመምህሩ መጠይቅ 124
አባሪ መ የተማሪው መጠይቅ 129
አባሪ ሠ በዮናቱ የታቀፉት ሞዴል ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ክፍሎች የየአመቱ ናሙናዎች 131

የሰንጠረዡ ሙለያ ቁጥር	የሰንጠረዡ ዝርዝር ርዕስ	ገፅ

1. የሙህራን መጠይቅ ስርጭት፣ ተሞልተው የተመለሱ ቁጥርና መቶኛ 54
2. የናሙና መምህራኑን ፆታ፣ የት/ደረጃ የሰለጠኑበትን ትምህርት፣ ያገለገሉበትን ዘመን ወዘተ. የሚያሳይ 55
3. የናሙና ተማሪዎች ፆታ፣ ዕድሜና የእፍ መፍቻ ቋንቋ የሚያሳይ 57
4. በሞዴል ፈተናዎቹ እንብዙ መረዳትን ለመፈተኖንት የተመረጡ ምንባቦች የፅሑፍ አይነት ብዛትና መቶኛ 59
5. በሞዴል ፈተናዎቹ እንብዙ መረዳትን ለመፈተኖንት የተመረጡ ምንባቦች የተወሰዱባቸው ምንጮች 60
6. በሞዴል ፈተናዎቹ ከአንድ ገጽ በላይ፣ ከግማሽ እስከ አንድ ገፅና ከግማሽ ገጽ በታች የሚሆን ርዝመት ያላቸው ምንባቦች ብዛትና መቶኛ 63
7. እንብዙ መረዳትን ለመፈተኖ መሳሪያንት በየዓመቱ ከተመረጡት ውስኖ ከ10 በታች፣ 10፣ ከ11 - 15 እና ከ15 በላይ ጥያቄዎች የወጡባቸው ምንባቦች ብዛትና መቶኛ 63
8. እንብዙ መረዳትን ለመፈተን የምንባቦች አመራረጥን በሚመለከት ከሙህራኑ የተገኙ መረጃዎች 65
10. በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ከ1987 - 1990 በተሰጡት የሞዴል ፈተናዎች የተካተቱት የፅሁቀትና የክሂል ክፍሎች ብዛትና መቶኛ. 68
11. ከ1987 - 1990 የተጠየቁ ጥያቄዎች ቢያንስ በሶስት መዳቢዎች ስምምነት የተደረሰባቸው ብዛት 70
12. በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የሞዴል ፈተናዎች የተመዘኑ የእንብዙ መረዳት ክሂሎች 71
13. በየክሊስቱ የተለዩት ክሂሎች አወካከል በናሙና ሞዴል ፈተናዎቹ ጥያቄዎች. 78
14. በእንብዙ መረዳት ትምህርት ትኩረት የሚሰጣቸውንና የማይሰጣቸውን ክሂሎች በሚመለከት ከሙህሩ መጠይቅ የተገኘ መረጃ 80
15. በእንብዙ መረዳት ፈተና ትኩረት የሚሰጣቸውንና የማይሰጣቸውን ክሂሎች በሚመለከት ከሙህሩ መጠይቅ የተገኘ መረጃ 82
16. 50፤ እና ከዚያ በላይ በሆኑ መላሾች በማስተማርና በመፈተን ከአማካይ በላይ የሆነ ትኩረት እንደሚሾ አስተያየት የተሰጠባቸው ክሂሎች ውክልና በፈተናዎቹ ጥያቄዎች 83
17. በአብዛኖቹ መላሾች ዝቅተኖ (ከአማካይ በታች የሆነ) ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው የሚል አስተያየት የተሰጣቸው ክሂሎች ውክልና በፈተናዎቹ 85
18. በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የሞዴል ፈተናዎች ጥያቄዎች የተመዘኑ የ12ኖ ክፍል መርሀ ትምህርት የእንብዙ መረዳት ክሂል ይዘቶች.. 87
19. በ12ኖ ክፍል መርሀ ትምህርት የእንብዙ መረዳት ይዘትንት የቀረቡ ክሂሎች ውክልና በሞዴል ፈተናዎቹ ጥያቄዎች 92

የሰንጠረዥ መለያ ቁጥር	የሰንጠረዥ ዝርዝር ርዕስ	ገፅ
20.	የደጠት አግባብነት ይረጃን ከፍ የሚያደርጉ ቅድመ ሁኔታዎችን በሚመለከት ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘ መረጃ	94
21.	የላሀይ አግባብነትን በሚመለከት ከተማሪው መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች	96
22.	የሞዱል ፈተናዎቹ የአንብቦ መረዳት ክፍል ያጠያየቅ ዘዴዎች በተለያዩ ተመራማሪዎች ጥናቶች ከቀረቡት የአንብቦ መረዳት ፈተና ያጠያየቅ ዘዴዎች ጋር ያላቸው ተዛምዶ	100
23.	የመግረያ መፅሐፉ ያጠያየቅ ዘዴዎች እይንት የየአይነቶቹ ድግግሞሽና መቶኛ	103
24.	የመግረያ መፅሐፉና የሞዱል ፈተናዎቹ የአንብቦ መረዳት ክፍል ያጠያየቅ ዘዴዎች ተዛምዶ	104
25.	ያጠያየቅ ዘዴዎችን በሚመለከት ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘ መረጃ	106

ምስጋና

አማካሪዬ ዶ/ር ተሾመ ደምሴ የጥናቴን እረቂቅ በማረም፣ ጠቃሚ ሀሳቦችን በመስጠት፣ ግስተካከያ አቅጣጫዎችን በማመላከት፤ ያጋጠመኝን ችግሮችና ያልገቡኝን ጉዳዮች በግንኙነውም ጊዜና ቦታ ስጠይቃቸው ያለመታከት ምላሽና አስተያየት በመስጠት ላደረጉልኝ ድጋፍ ያለኝ አክብሮትና ምስጋና ከሁሉም የላቀ ነው።

ዶ/ር ደጀኔ ለታ፣ ከርዕሰ መረጣው ጀምሮ አማካሪ እስከተመደበልኝ ድረስ ብዙ የረዱኝ ከመሆናቸውም በተጨማሪ መጪሕፍት በማቅረብ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመገምገም አማካሪዬ በሀገር ባልነበሩበት ወቅት የጥናቴን ረቂቅ ክፍሎች በማረም፣ ዶ/ር ግረው ጸውዲ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመገምገም፣ አማካሪዬ ወደውጭ ሀገር ወጥተው በነበረበት ወቅት የጥናቴን ረቂቅ ክፍሎች በማረም ላደረጉልኝ ትብብር ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው የፈተናዎቹን ጥያቄዎች በመከፋፈል፣ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹን በመገምገምና ለሎች ድጋፎችን በማድረግ የተባበሩንም ብዙዎች ናቸው። ከነዚህ ውስጥ የአቶ ግስተሞል ውበቴ፣ የአቶ ጌታቸው አዳኘ፣ የአቶ መኮንን፣ የአቶ ተመስገን መላኩ የአቶ ተስፋዬ ተሰማ፣ የአቶ ሞለልኝና የተግሪ አዲስና የእይኔ ተስፋ አስተዋጽኦ ይበልጥ ሊታወስ የሚኖር ነው።

መጠይቆቹን በመሙላት የተባበሩንን መምህራንና ተማሪዎችም ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ፤

ድጋፋቸው ተለይቶ ላግያወቀው ወላጆቼ፣ ብዙ ጉዳዮችን እኔ በሌለሁበት መስመር አስይዘው ቤኦም እንድሜር ላስቻሉኝና በሥነብና በሞራል ላልተለዩኝ የስራ ባልደረቦቼ፣ የዕዋ ማህበረተሰቼና ለሎች ንደኞቼ ያለኝ አድናቆት በቀላሉ ሊገለፅ የማይችል ነው። በተለይም ወ/ሮ ጥጋብ መስፍን፣ አቶ አበበ ንሉ፣ ጋሺ ሀይሌ በላይ፣ ጥሩ ሰውነት ራስን ለሌላው አሳልፎ አስከመስጠት የሚደርስ እንደሆነ ያስተማሩኝ ናቸውና መቼም ከውስጤ ሊጠፉ የማይችሉ ናቸው።

በመጨረሻም ቅሉቆን በኮምፒውተር በመተየብ የተባበረችኝ ወ/ት ጓባይነሽ ወ/ሚድቅን ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ።

አጠቃሉ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የ12ኛ ክፍል የእማርኛ ሞዴል ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ክፍል የይዘትና የላህይ አግባብንትና ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት መመርመር ነው።

ተጠናዎቹ በተራ የዕጣ ናሙና የተመረጡት ትምህርት ቤቶች ከ1987-1990፤የተሰጡ የሞዴል ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ክፍል ሲሆኑ በተለያዩ ምሁራን የቀረቡ የይዘትና የላህይ አግባብንት፤ ያጠያየቅ ዘዴዎች ነክ ንድፈ ሀሳቦች፤ መርሆዎች፤ አተያዮች፤ መመዘኛዎችን፤ የ12ኛ ክፍል የእማርኛ መርሀ ትምህርትና የመማሪያ መፅሐፍ፤ ለጥናት የተመረጡት ፈተናዎች፤ አጥኒው በተለያዩ ምሁራን የወጡ በአንብቦ መረዳት ፈተና ሊመዘኑ የሚገባቸው ክሂሎች ሞዴሎቹን (የክሊስቶችን) መነሻ በማድረግ ያዳበረው የክሊስትና መጠይቅ በዋና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መላሪያነት እገልግለቸል። በፈተናዎቹ በአንብቦ መረዳት ክፍል የተጠየቁትን ጥያቄዎች በየክሊስቱና በመርሀ ትምህርቱ በተለዩት ክሂሎች መሰረትነት የሚከፋፍለ ባለሙያዎችም ተመርጠው ከጠቅላላው 1187 ያንብቦ መረዳት ክፍል ጥያቄዎች ውስጥ በየክሊስቱ መሰረትነት 1118፤ በመርሀ ትምህርቱ 1139 ጥያቄዎች አከፋፈል ቢያንስ ሶስቱ ሰምንት ላይ ለመድረስ ችለዋል።

ከላይ በተጠረጠሩት የመረጃ መሰብሰቢያዎች የተሰበሰበው መረጃ በተለያዩ ክፍሎች በቀጥርና በፈደል (በገላጭ እስታትስቲክስ (በድግግሞሽና በመቶኛ)ና በአይነታዊ የመረጃ አተናተን) የሚገመገመው ተንሞገሞ የሚተነተነው ተተንትኖ ከጥናቱ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል።

- የፈተናዎቹ የምንባቦችና ያጠያየቅ ዘዴዎች አመራረጥ በተለያዩ ተመራማሪዎች ከቀረቡ መርሆዎች፤ መመዘኛዎች _ አኳያ ሲገመገሙና ከመጠይቅ የተገኘው መረጃ ሲተነተን አለታዊ ነጥቦው የበዛ ሆኖ ተገኝቷል። በተለይ ያጠያየቅ ዘዴዎች አመራረጥ ድክመት በጣም የነጣ፤ በተፈታዮቹ የፈተና አሰራርና ውጤት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሆኖ ተገኝቷል።
- የክሂሎቹን በፈተናዎቹ ጥያቄዎች መሸፈን አለመሸፈንና የአወካከላቸውን ተገቢነት ለመመርመር በባለሙያዎቹ የተከፋፈሉትን 1118 ና 1139 ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ የተካሄደው ትንተና እንዳመለከተውም 1ኛ በቸክሊስቱም፤ በመርሀ ትምህርቱም የተለዩት አብዛኞቹ ክሂሎች በፈተናዎቹ ጥያቄዎች ቢሸፈኑም ያልተሸፈኑት በመርሀ ትምህርቱም ሆነ በመስኩ በተደረጉ ጥናቶች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው እንደመሆናቸው መጠን መሸፈን ሲኖርባቸው ባለመሸፈናቸው፤ 2ኛ በጥያቄዎቹ መሸፈን

የቻሉት፤ አወካከል በቂ፤ ወካይና ተመጣጣኝ ነው ለማለት የማያስችል ሆኖ በመገኘቱ፤ በዚህም እንደምንባባቸው አመራረጥ ሁሉ የፈተናዎቹ የአንብቦ መረዳት ክፍል የይዘት አግባብነት ደረጃ ዝቅተኛ ነው (አሉታዊነቱ የንላ ነው) ወደሚል መደምደሚያ የሚመራ ሆኖ ተገኝቷል።

- ፈተናዎቹ ለአብዛኞቹ ተፈታኞች ተገቢ የመመዘኛ መሳሪያ መስለው መታየት ችለዋል። በፈተናዎቹ ምርመራ አምንታዊነቱ የንላ ግኝት ይኸው የፈተናዎቹን የላህይ አግባብነት የሚመለከተው ብቻ ነው።

ባጠቃላይ የሞዴል ፈተናዎቹ የአንብቦ መረዳት ክፍል የላህይ አግባብነት ከተፈታኞቹ አኳያ አምንታዊ ገፅታ የሚታይበት ሆኖ ቢገኝም በሌሎቹ ግን ደካማ ሆኖ ተገኝቷል። የተለያዩ ተመራማሪዎች በየጉዳታ መለኪያ ፈተና የይዘት አግባብነት ዋና ጉዳይ እንደሆነ ቢያስረዱም በንዚህ ፈተናዎች ይህ ክፍል የሚገባውን ያህል ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ ተረጋግጧል። በአጠያየቅ ዘዴዎችም እንዲሁ።

በመሠረቻም ከንዚህ አሉታዊነት የሚበዛባቸው የጥናቱ ውጤቶች በመነሳት በትምህርት ቤት ደረጃና ከትምህርት ቤት ውጭ ባሉ የሚመለከታቸው ክፍሎች ቢከናወኑ የችግሮቹን ደረጃ መቀነስ ሊያስችሉ ይችላሉ የተባሉ የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል።

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ (Background of the Study)

ግሩላንድ (1988)፣ ሂቩዝ (1995)፣ ሂተን (1990)፣ አልያርሰን፣ ክላፓምና ምል (1995)፣ ባቱማን (1995)፣ ቄየር (1990፣ 1993)ና ሌሎችም ተመራማሪዎች በተለያየ አገላለፅ እንደሚያስረዱት የተግሪዎችን ችሎታ ለመመዘን በየጊዜው የሚሰጡ ፈተናዎች በተገቢ መንገድ በጥንቃቄ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ በጎ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ እንጂ በተቃራኒው ጉዳት የሚያስከትሉ አይነት መሆን የለባቸውም። ከሁለቱ በየትኛው ጎራ እንደሚፈረጁ ማረጋገጥና የተሻሉ ፈተናዎችን ማዘጋጀት የሚቻለው ደግሞ ፈተናዎቹን መገምገምና ጥንካሬ/ድክመታቸውን መለየት ሲቻልና ጠንካራ ገፅታዎች የሚንጸባረቁበት፣ ደካማዎቹ የሚታረሙበት መንገድ በጥናትና ምርምር መፈለግ ሲችል ነው።

ከዚህ መሰረታዊ ሀሳብ ስንነሳ አማርኛን በማስተማር ሂደት በ1984 ዓመተ ምህረት (እ.ኢ.አ) አዳዲስ መርሀ ትምህርቶች (Syllabus)ና የመማሪያ መፅሐፎች ታትመው ግልጋሎት መስጠት ከጀመሩ ወዲህ ከመርሀ ትምህርቶቹና ከመማሪያ መጻሐፎቹ ይዘት ድክመት/ጥንካሬ ጋር የተያያዙ ጥናቶች በመጠኑም ቢሆን የተካሄዱ ሲሆን ከመማር ማስተማሩ ሂደት ጥብቅ ቁርኝትና ትስስር ባላቸውና ሰፊ ምርምር በሚያስፈልጋቸው በፈተናዎች አዘገጃጀት፣ አፈፃፀም፣ ነክ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የተደረገ ጥናት የሌለ ያህል ነው። በተለይ በክሂሎች አፈፃፀም ላይ ተመስርቶ የተካሄደ አንድም ጥናት ማግኘት አልተቻለም። በርግጥ በቃላት አፈፃፀም ላይ የተካሄደ አንድ ጥናት አለ። ነገር ግን የቃላት መደብ በሌላ የቋንቋ ዘርፍ እንጂ በክሂል ስላልሆነ / ባቱማን (1995)፣ ሂተን (1991)/ በዚህ በክሂል መስክ ሊጠቀስ የሚችል አይደለም።

የሆነ ርዕሰ ይዞ ተንሸው በዚህ አቅጣጫ ያቅሙን ያህል ለማጥናት መነሳሳቱ አንደኛው ምክንያት ከላይ የተገለፀው የጥናቶች አለመኖር ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ቋንቋውን በማስተማር በቆየባቸው ጐሎችት፣ በሰራባቸው ትምህርትቤቶች "የፈተና ባንክ" ፋይሎች ውስጥ በሚገኙ ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች ተገቢ ትኩረት ማግኘት አለማግኘታቸው፣ ክሂሎቹን ለመመዘን የሚመረጡት ምንባቦችና ያጠያየቅ ዘዴዎች ያላቸው የአግባብነት ደረጃ በጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚቀመጥ አይነት መሰሉ ስለታየው ሰፋ ባለ መረጃ ይህንኑ (የክሂሎቹን በጥያቄዎች አወካከል፣ የምንባቦችና ያጠያየቅ ዘዴዎች አመራረጥ በአምንታዊነት የሚፈረጅ መሆን አለመሆኑን) ለማረጋገጥ ነው።

አጥኚው በተለይ ለንባብ ክሂል ትኩረት የሰጠበት አንደኛው ምክንያት ቀደም ብሎ የተገለፀው ሲሆን ሌላው ግስተዋል (1989 እ.ኢ.አ) በየነ (1985)ንና ጊታቸው (1986)ን ጠቅሰው እንዲሁም ትንላኤ (1988 እ.ኢ.አ) እንደሚገልፁት በመርሀ ትምህርቶቹና በመማሪያ መፅሐፎቹ ከሌሎች ክሂሎች የበለጠ ቦታ የተሰጠው በመሆኑና በፈተናዎቹም በስፋት ሊወከል ስለሚችል ነው። ከንዚህ በተጨማሪና በተያያዘ ሁኔታ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የአንብቦ መረዳት ክሂል መዳበር የሌሎችም ክሂሎች መዳበር ስለሆነ የትምህርቱ ሂደት አንዱ አካል የሆነው ያፈታተኑ ስልት አግባብነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ብዙ ጠቀሜታዎች የሚኖሩትን ያህል አግባብነት የሌለው ሲሆን ደግሞ የዚያኑ ያህል ጉጂ ስለሚሆን አምንታዊ ገፅታዎችን ማጎልበት፣ አሉታዊንት ያላቸውን ለማረም የሚቻለው ከፍ ብሎ እንደተገለፀው ይበልጥ በጥናት ማረጋገጥ ሲቻል ስለሆነ ነው።

ለማጠቃለል ከዘመናዊ የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት፣ ከቋንቋን ለምንና በምን፣ በማን፣ ምን፣ እንዴት እናስተምር ትምራዎችና ጥናትና ምርምሮች ባልተናነሰ ማለት ይቻላል የቋንቋ አፈታተንን በተመለከተ ታትመው ለንባብ እየበቁ ያሉት አዳዲስ ጠቃሚ ጥናትና ምርምሮች እንደሚያስረዱት የእንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና በውስጡ የተለያዩ ንዑሳን ክሂሎችን ያቀፈ፣ የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎችና የምንባቦች አመራረጥ መርሆዎችና ቴክኒኮች ያሉት ነው። እነዎ ይህ ጥናት ከንዚህ ተመራማሪዎች አተያይ፣ ከአማርኛ ማስተማሪያዎች የንባብ ክሂል ይዘት፣ ከቋንቋው አስተማሪዎችና ተማሪዎች አመለካከት አኳያ ሲመረመሩ፣ የሞዴል ፈተናዎቹ የእንበቦ መረዳት ጥያቄዎች ያላቸው አግባብነት የት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማሳየት የሚሞክር ነው ማለት ነው።

1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ አንብቦ የመረዳት ክሂሎች አፈታተን አምንታዊ የሆነ የያዘትና የላህይ አግባብነትና ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት የሚንፀባረቅበት መሆን አለመሆኑን በምርመራ ለማሳየት ነው።

ከዚህ አጠቃላይ ግብ ለመድረስ የሚያበቁ ዝርዝር አላማዎችም አሉ። እነሱም -

1. በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችና በክሂሎቹ መካከል ዝምድናና አግባብ ያለው ዝምድና መኖር አለመኖሩን ለመመርመር፣ ማለትም መሸፈን ያለባቸው ክሂሎች ሁሉ እንደሚሸፈኑና እሸፋፈኑ በቂ፣ ወካይና ተመጣጣኝ በሆነ ናሙና መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ፣
2. ለመፈተኛ መግለጫነት የሚመረጡት ምንባቦች የተለያዩ ክሂሎችን ለመፈተን የሚያስችሉና ወካይነት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ፣
3. በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችና በመርሀ ትምህርቶቹ ምንባቦ መረዳት ክሂል ይዘቶች መካከል አግባብነት ያለው ግንኙነት እንዲኖር መደረጉን ለማረጋገጥ፣

4. በፈተናዎቹ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የሚታዩት ያጠያየቅ ዘዴዎች፦
   4.1 ከተመራማሪዎቹ የአንብቦ መረዳት ጥያቄ ማቅረቢያ ዘዴዎች፣
   4.2 ተማሪዎቹ በመማሪያ መፅሐፎቹ ከተለማመዷቸው ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ፣
5. ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ከሚሉት ፈተናዎች ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ፣
6. እየተሰራበት ያለው ያፈታተን መንገድ አሉታዊ ጎኖች የሚታዩበት ሆኖ ቢገኝ የተሻለ የአንብቦ መረዳት ከሚሉት አፈታተን ስልት የሚቀየስበትን መንገድ ለማመልከት፣

1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

የትምህርት ጊዜትን በማራመድ ወይም በመጉዳት ፈተናዎች ቀላል የማይባል ተፅዕኖ (washback) ያላቸው ስለመሆናቸው ብዛት ያላቸው ተመራማሪዎች በተለያዩ ስራዎቻቸው ደጋግመው የሰገንዘቡት ጉዳይ ነው። የተለመዱት ያፈታተን ስልቶች ተፅዕኖ አምንታዊነት ወይም አሉታዊነት መረጋገጥ የሚችለው ደግሞ በፈተናዎች ላይ ጥናት ማድረግ ሲቻል ነው፤ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሲመረመሩና ሲተነተኑ ነው። በምርምሮቹ ግኝቶች መሰረት ይካማ ገፅታው በየጊዜው እየታረመ፣ ከአዳዲስ ትምራዎችና ተግባራዊ የምርምር ግኝቶች ጋር እየተገናዘበ እንዲሰጥ ማድረግ ሲቻል ነው። ብዙዎቹ ተመራማሪዎች የዚህ አይነት አመለካከት እንዳላቸው ስራዎቻቸው ያሰገንዝባሉ።

ከዚህ አመለካከት ስንነሳ ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ማስገኘት ስለሚችል አስፈላጊነት ያለው ነው።

1. የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ከሚሉቱን ወካይነት ባለው መንገድ እንዴት መፈተን እንደሚቻል ሀሳብ መስጠት ይችላል።
2. የምንባቦቱ አመራረጥ መርሆዎችን የመከተሉን ጠቀሜታ ለማሳየት ይችላል።
3. ለየትኞቹ ከሚሉቱ የትኞቹ ያጠያየቅ ዘዴዎች የተሻሉ እንደሆኑና የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎች የሚኖራቸውን ጠቀሜታ ለማመልከት ይችላል።
4. ለመምህራን አስልጣኝ ተቋማት የመምህራንን ተማሪዎቻቸውን የመገምገም ብቃታቸው የት ላይ እንዳለ ለማሳየት ይችላል።
5. ተማሪዎቱ የአንብቦ መረዳት ከሚሉቱ ፈተና ላይ ያላቸውን አመለካከት ማሳወቅ ይችላል፣
6. የአማርኛን ትምህርት አስጣጥ የተሻለና የተቃና ለማድረግ የሚደረግ ሙከራ ቢፈጠር መጠነኛ የሆነ ሀሳብ ሊሰጥ ይችላል።
7. በመሰኩ ወደፊት ለሚካሄዱ ጥናቶች መነሻ በመሆን መጠነኛ አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይችላል።

1.4 የጥናቱ ወሰን

ከፍ ብሎ እንደተገለፀው ጥናቱ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ፈተና የይዘትና የላህይ አግባብነትና ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት በአምንታዊ ደረጃ የሚፈረጅ፤ የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች በሚደግፉት ስልት የሚንፀባረቅ መሆን አለመሆኑን በመመርመር ላይ የተመሰረተ ነው።

ከጊጄፐ ከንንዘብና ከመሳሰሉት ችግሮች አኳያ ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ፣ ከአዲስ አበባም በውስጧ ከሚገኙ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማማሸቱ ላይ ነው። የሚጠኑት ፈተናዎችም ከ1987 - 1990 የተሰጡት ናቸው። በጥናቱ መነሻ ላይ የ '1986'ንም ለማካተት የታሰበ ቢሆንም ለጥናት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የዚህን ዓመት ፈተና ለማግኘት ስላልተቻለ በሌሎቹ ዓመታት የተሰጡትን ብቻ ማጥናቱ ግድ ሆኗል። ከፈተናዎቹ ጋር በተያያዘ በ12ኛ ክፍል መርሀ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ይዘት ስር የተዘረዘሩት የክሂሉ ይዘቶችና የመግረያ መፅሐፉ ያጠያየቅ ዘዴዎችም ይመረመራሉ። ከዚህ በላይ ለመረመር ግን እንደተባለው የጊጄፐ የገንዘብና የመሳሰሉት ችግሮች ስላሉ አልተቻለም።

ለጥናቱ በተመረጡት ዓመተ ምህረቶች የተሰጡ ፈተናዎችን በሙሉ ለማግኘት ባለመቻሉም በተለይ የፈተናዎቹን የይዘት አግባብነትና ያጠያየቅ ዘዴዎች ምርመራ በአንዱ ዓመተ ምህረት (በ1987)፤ በ10ኛ በሁለቱ (በ1988ና በ1989) በ11ኛ በ1990 ዓ.ም. በ12 ፈተናዎች ላይ እንዲካሄድ ተደርጓል። የላህይ አግባብነቱን ጥናት ግን በሌሎች ቀደም ያሉ ዓመታት በተሰጡ ፈተናዎች ጭምር ለማካሄድ አመች ሆኖ ባለመገኘቱ በ1990 በተሰጡት ላይ ብቻ የተወሰነ እንዲሆን ሆኗል።

1.5 የቃላት (ሀረጋት) ትርጓሜ (Definition of terms)

ሀ. ሞዱል ፈተናዎች፤

በ12ኛ ክፍል ከሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በፊት በክፍሉ መምህራን ተዘጋጅቶ የሚሰጠው ፈተና መጠሪያ (ስም) ነው። በጥናቱ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች ምክትል ርዕሳነ መምህራንና የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተቀዳሚ መምህራንን በማነጋገር መረዳት እንደተቻለው ከሆነ ለዚህ ፈተና ይህ ስያሜ ሊሰጠው የቻለበት ምክንያት እንደ መልቀቂያ ፈተናው በየትምህርት አይነቱ ከመጠናቀቅ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል የሚሰጠውን ትምህርት የማካተት ባህሪ ስላለው ነው።

ለ. ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት፤

በዚህ ጥናት ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት በሚለው ሀረግ ውስጥ የሚገኘው " ብቃት" የሚለው ቃል የሚመለከተው ለጥናት የተመረጡት ፈተናዎች አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የተጠቀሙባቸው ያጠያየቅ ዘዴዎች ተገቢ /አምንታዊ/ መሆን አለመሆናቸውን ነው። ተገቢ /አምንታዊ/ መሆን አለመሆናቸው የሚመዘነውም 1. አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የሚያገለግሉ እንደሆኑ በተለያዩ ተመራማሪዎች ከተመሰከረላቸው፤ 2. በመማሪያ መፅሐፉ ተግባሮች ከተለማመዷቸው ያጠያየቅ ዘዴዎች ጋር በሚኖራቸው የተዛምዶ (ግንኙነት) ደረጃ ነው።

ሐ. ቸክሊስት፤

የግሪጋገጫ ዝርዝር

መ. ባክቸኛ፤

ባክቸኛ ፈተናዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚኖራቸው ተፈላጊ (አምንታዊ) ወይም ነጂ (አሉታዊ) ተፅዕኖ "ባክቸኛ" ይባላል ሂዩዝ (1995፣ 1)፣ ዌየር (1990፣ 27)፣ ሀሪስና ማክካን (1994፣ 61)።

1.6 በጥናቱ የጎሙተ ምህረት አጠቃቀም

በዚህ ጥናት በኢትዮጵያና በውጭው የዘመን አቆጣጠር የተፃፉ ፅሑፎች፣ የተገለፀ ንኖቶ አሉ። ከነዚህ ውስጥ ሞዴል ፈተናዎቹን ከሚመለከቱት በቀር ሌሎቹ በኢትዮጵያ አቆጣጠር የተገለፁት በሙሉ እሙተ ምህረቱን ከሚያመለክቱት ቁጥሮች ቀጥሎ በቅንፍ ውስጥ (እ.አ.አ) የሚል እንዲታከልባቸው ተደርጓል። ስለዚህ ሞዴል ፈተናዎቹን የሚመለከቱ ካለሆኑ በቀር (እ.አ.አ) የሚል ያልተጨመረባቸው ሁሉ የውጭውን አቆጣጠር የሚመለከቱ እሙተ ምህረቶች ናቸው ማለት ነው።

ምዕራፍ ሁለት

ከለሳ ድርሳናት

2.1. የቋንቋ ፈተና

ባከቃላይ መልኩ ሲታይ የተለያዩ የፈተና ተመራማሪዎች እንደሚያመለክቱት ፈተና በመደበኛ ትምህርት መስክ የባህሪ (የዕወቀት፣ የክሂል...) መመዘኛ መሳሪያ ነው። ለአብነት በባትማን (1995 ፣ 20) የተጠቀሱት ካሮል (1968፣ 46) ብያኔ መሰረት " ስነ-ልቡናዊ ወይም ትምህርታዊ ፈተና የተወሰነ ባህሪን ለማወቅ የሚዘጋጅ ሰልት ነው።"

ከካሮል (1968) ብያኔ በመነሳት ባትማን (1995) አንድ የንግግር ክሂል ፈተናን በምሳሌነት በመጥቀስ ጭምር ከቋንቋ ፈተና አኳያ እንደሚያስረዱት፣ ፈተና የአንድን ግለሰብ የተወሰነ ባህሪ ለማወቅ የሚዘጋጅ የመመዘኛ መሳሪያ ነው። እንደሌሎቹ የመመዘኛ /የመለኪያ/ መሳሪያዎች ሁሉ የግለሰቦችን ጠባያት (characteristics) ግልፅ በሆኑ መንገዶች በአህዛ የሚገልፅ ነው። ከሌሎች የመለኪያ /መመዘኛ እይነቶች የሚለየው የተወሰነ ናሙና ባህሪን ለማግኘት /ለመለካት/ ተብሎ የሚዘጋጅ በመሆኑ ነው (ባትማን 1995፣ 20-21) ።

ፕይዝ (1995) የቋንቋ ፈተናዎች የተማሪውን የቋንቋ ችሎታ ለመመዘን፣ ችግር ለመፍታት ... በመሳሪያነት የሚያገለግሉ ናቸው በማለት ከተግባር አንፃር ይገልጿቸዋል።

አገላለፃቸው ቢለያይም በመሠረታዊ ሀሳብ ከነዚህ ምሁራን አተያይ በተቀራረበ መንገድ የተለያዩ ተመራማሪዎች ለምሳሌ አለር (1979)፣ ዌየር (1990፣ 1993)፣ ሂተን (1990፣ 1991)፣ ዶይኔ (1990፣ 1994 ተመራማሪዎችን በመጥቀስ)፣ አልደርሰን፣ ክለፓምና ዎል (1995)፣ ተጅመ (1995፣ ተመራማሪዎችን በመጥቀስ) በዘመናችን የቋንቋ ትምህርት፣ የቋንቋ ፈተና የሚለው የታዘውን ፅሁፍ ወይም የወከለውን ከተለያየ አቅጣጫ ለማስረዳት ከሞከሩት ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

እነዚህና ሌሎች ወደፊት የምናነሳቸው የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች የቋንቋ ፈተናን ከባህሪ መለኪያነት፣ ከትግር ፈቺነት፣ ... አንፃር ሲገልፁልን በሌላ አቅጣጫ የምንረዳው ያ የሚለካው ... በአብዛኛው በትምህርትነት የቀረበ ባህሪ (ችሎታ/ዕውቀት) መሆኑን ነው። ስለዚህም ፈተና ሲታሰብ ትምህርት፣ ትምህርት ሲታሰብ ፈተና መታወሳቸው (መታሰባቸው) አይቀሬ ነው ማለት ነው። "ማስተማርና መፈተን ሁለት የማይነጣጠሉ የጠቅላላው የማስተማር ሙግር ቲዩት ክፍሎች ናቸው" (ዶይኔ 1994፣2 እንደጠቀሱት) የሚለው አገላለፅም ይህንኑ በግልፅ የሚያመለክት ይመስለናል።

ሂተን (1991፣5) እንዲሁ ሁለቱ (መፈተንና ማስተማር) አንደኛውን መስክ ከሌለኛው ነጥሎ ለማሰብና በተግባር ለማዋል እስከማይቻል ድረስ የተሳሰሩ እንደሆኑ ያስረዳሉ።

በሁለቱ መካከል ያለውን የግንኙነት ሁኔቴና ደረጃ በመግለፅ በኩል በተመራማሪዎች መካከል ልዩነት አይታይም ማለት ግን እይደለም። ልዩነት አለ። ልዩነቱ ግን በአብዛኛው ከጊዜ አንፃር፣ በአስተሳሰብ ለውጥ (ፅድገት) የተነሳ የተከሰተ ይመስላል። ይኸውም ቀደም ባሉ ተመራማሪዎች አስተሳሰብ ፈተናን በቀጥታ የትምህርቱ አገልጋይ በክፍል የቀረበን ትምህርት የመመዘን ተግባር ያለው ብቻ አድርጎ የመቁጠር አዝማሚያ ነበር። የቅርቦቹ ይህን እንዳለ የሚቀበሉ አይደሉም። ዞሮ ዞሮ ግን ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸው አንድ ነገር አለ። ይኸውም ሁሉም፣ የሁለቱን ቢተዘመድነት (የተሳሰሩ) መሆን ይቀበላሉ። ለምሳሌ ቀደም ካሉት የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች አንዱ የሆኑትና በሂዩዝ (1995፣ 2) የተጠቀሱት ዴቪስ (1968፣ 7) ጥሩ ፈተና የታሰበውን ትምህርት ስለሚከተልና የተማሩትን ስለሚጠይቅ የትምህርቱ ቅን አገልጋይ ነው በማለት ነው የገለፁት። ገለፃው የሁለቱን ግንኙነት የሚያሳይ ነው። የሁለቱን ግንኙነት ከግሳየቱም በተጨማሪ አንዱ የሌላው /ፈተና የማስተማር/ ታማኝ አገልጋይ እንደሆነ አድርገው የሚገነዘቡት መሆናቸውን ጭምር ነው የዐረፍተ ነገራቸው ይዘት የሚያመለክተው።

የዘመናቱን ምሁራን በተለይም ቺየር (1990፣1993)፣ ዴቪስ (1991)፣ ሂዩዝ (1988፣1995)፣ ደጀኔ (1994 ተመራማሪዎቱን በመጥቀስ)፣ ባቶማን (1995)፣ ተሾመ (1995 ተመራማሪዎቱን በመጥቀስ)፣ ሁለቱ የተሳሰሩ በመሆናቸው ላይ ተቃውሞ ባይኖራቸውም በዴቪስ በተገለፀው የጊዜ-ሉሊ አይነት ግንኙነታቸው የሚስማሙ አይደሉም። እንደነሱ ትንታኔ ፈተና ከታዛዥነት (አገልጋይነት)፣ ከማስተማር ተከታይነት በላይ የሆነ ሚና ያለው ነው። የተወሰኑትን ለአብነት ብናይ ሂዩዝ (1995፣2)፣ ለምሳሌ ስለሁለቱ ተዛምዶ የሚገልፁት ሁለቱ ትክክለኛ እኖነት ወይም ሽርክና (partnership) አይነት ግንኙነት ያላቸው እንደሆኑ አድርገው ነው። እንደላቸው አስተያየት ፈተና ሁልጊዜ ማስተማርን የሚከተል እንዲሆን አድርገን ማሰብ የለብንም። ለጥሩ ማስተማር ድጋፍ ሰጭ ሆኖ እንዲገኝ መጣር አለብን። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በመጥፎ ማስተማር ሂደት ላይ በን ተፅዕኖ አድርጎ የማስተማር ሂደቱ የሚጓጓልበትን (የሚስተካከልበትን) ሰልት የሚያመለክትም መሆን አለበት። በማስተማር መማር ሂደት ላይ በተገቢ መንገድ የተዘጋጀ ፈተና ተፈላጊ የባክዋሽ (beneficial backwash) ማሳደር የሚችል መሆኑን ምሳሌ በመጥቀስ ጭምር ያስረዳሉ።

ቺየር (1990) እንዲሁ እንደሂዩዝ ባንዲት ሀገር /በኒሪላንካ/ በተግባር የታየ፣ በስራ ላይ ያለን የቋንቋ ስርአተ ትምህርት የማሰለውጥ የፈተናን ከፍተኛ ሀይል በምሳሌነት በመጥቀስ ፈተና በስርአተ ትምህርት፣ በማስተማር፣ በመማር፣ በትምህርት መሳሪያዎች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማድረግ የሚችል መሳሪያ መሆኑን ይገልፃሉ።

ዴቪስ ራሳቸው በ (1991) የቀድሞ አቋማቸውን ቀይረው የቋንቋ ፈተና የትምህርቱ ሂደት ተገቢ አቅጣጫ መያዝ አለመያዙን ለማረጋገጥ፣ ተስማሚ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና መሳሪያዎቱን ለመምረጥ ... የሚውል መሆኑን አመልክተዋል (ዴቪስ 1991፣ 136)።

ባጠቃላይ በብዙዎቹ የዘመናችን የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች እንደሚገለፀው የቋንቋ ፈተናዎች በተለይም የንፁፅ መለኪያ ፈተናዎች በክፍል ከሚሰጠው ትምህርት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው ናቸው። ከመረጃ ሰጭነት /ከመመዘኛ መሳሪያነት/ በተጨማሪ በትምህርቱ ላይ፣ በመሳሪያዎቹ ላይ፣ በስነዘዴዎች ላይ ተፈላጊ የባክዋሽ ውጤቶችበጉልህ የሚያንፀባርቁ /ማንፀባረቅ ያለባቸው/ እንደሆኑ ነው የሚገለፀው።

እስካሁን ከተነሱት ነጥቦች ለመረዳት የተቻለው የቋንቋ ፈተናዎች በደምሳሳው ሲታዩ ተግሪ በተግሪው ትምህርት ያላየውን የባህሪ ለውጥ ለመለካት የሚያገለግሉ የተለያዩ ጠቋሚዎች ያሏቸው፣ እምንታዊ ወይም አሉታዊ የሆኑ የባክዋሽ ውጤቶች ሊያመጡ የሚችሉ መሆናቸውን ነው። ከሚሰጡበት አላማ አኳያ ግን በግልፅና በቀጥታ ለመመልከት አልተሞከረም። ስለዚህ ከዚህ አቅጣጫም በተወሰነ ደረጃ ማንሳቱ የቋንቋ ፈተናን ምንነት፣ ተግባር፣ ባህርያት ይበልጥ ለመረዳት የሚያግዝ ይመስላል። እናም በመጠኑ በቅንነት መልክ ለመመልከት እንሞክር።

ዌየር (1990) በቋንቋ ትምህርት የቋንቋ ፈተናዎች ለምን ይሰጣሉ? ጥያቄን የቋንቋ ፈተና ስልቶች (approaches to language test design) ብለው ከከፈሏቸው ሦስት ስልቶች ጋር አያይዘው ለመመለስ ሲሞክሩ፣ ሂቶን (1990) ደግሞ በቋንቋ ትምህርት ፈተናዎች በተግሪዎች የታየውን የንፁፅ ፅድገት (progress) ለግውቅ፣ ለመግር አስቸጋሪ የሆኑ ነጥቦችን ለመለየት፣ ተግሪዎቹን ለግበረታታት፣ የንፁፅ ደረጃቸውን ለመለየት፣ በተገቢ ቦታቸው ለመደልደል፣ ለመረጣት፣ ስለንፁፅታቸው ለግውቅ፣ ጎላግ እንደሚሰጡ በስፋት እያንዳንዱን ጎላግ በግብራራት ያስረዳሉ።

የባንግን (1995) አተያይም ከሂቶን ብዙ የሚለይ አይደለም። በእንድ የትምህርት ፕርግራም ፈተናዎች የሚሰጡበት ምክንያት /ጎላግ/ የተለያዩ ውሳኔዎችን ለመወሰን የሚያስንል መረጃ ለግግኘት ነው። እነዚህ ውሳኔዎች /ግምገማዎች/ /decision/evaluation/ በሁለት ክፍል ሊጠቃለሉ ይችላሉ በግለሰቦች ላይ የሚካሄዱ ውሳኔዎች /ግምገማዎች/ና በፕርግራሙ ላይ የሚካሄዱ ውሳኔዎች /ግምገማዎች/ ተብለው። በግለሰቦች /individuals/ ላይ የሚካሄዱት ውሳኔዎች እንደገና በሁለት ይከፈላሉ። በተግሪዎች ላይ የሚካሄዱና በአስተግሪዎች ላይ የሚካሄዱ በመባል። በተግሪዎች ላይ የሚካሄዱትን ውሳኔዎች /ግምገማዎች/ አላማዎች ከፈተና አይነቶች እንዥር ይገልጿቸዋል - ድክመትና ጥንካሬን

ለመለየት /diagnosis/ ስላላቦት ዕድገት /progress/ መረጃ ለማግኘት፣ ችሎታቸውን ለመመዘን... እያሉ (ባቱማን 1995፣ 54 - 61) ።

ናስር (1979) እንዲሁ የቋንቋ ፈተናዎች ለግምገማ ጎላማ እንደሚያገለግሉ ያስረዳሉ። አላቸው እንደሚሉት የተግሪዎች ስራና ዕድገት (work and progress) በየጊዜው የግድ መገምገምና መለካት ይኖርበታል። ድክመትን ለማረም፣ ካስተማሪው የሚፈለጉ ዋረቶችን /efforts/ ለመጨመር፣ የተማሪዎችን ጥናት በተገቢ መንገድ ለመምራት፣ ተገቢ የሆኑ የማስተማሪያ ሙሳሪያዎችንና ዘዴዎችን ለመምረጥ የሚቻለው ተገቢነት ባላቸው ፈተናዎች የተማሪዎችን ስራና በመማር ማስተማር ሂደት ያሳዩትን ዕድገት መገምገምና መለካት ሲቻል ነው። ስለዚህ ለነዚህ አላማዎች ሲባል የቋንቋ ፈተናዎች ይሰጣሉ (ናስር 1979፣ 174)።

ብዙዎቹ ተመራማሪዎች ደግሞ የፈተናን አላማ ከፈተና አይነቶች ጋር አያይዘው ነው የሚገልፁት። የችሎታ መለኪያ ፈተና የራሱ የሆነ አላማ፣ ሌሎችም እንደዚያው የየራሳቸው የሆነ አላማ ያላቸው እንደሆኑ አድርገው። በተወሰነ ገፅታው ከላይ የቀረበው የባችማን (1995) አገላለፅ የሀን አተያይ የሚጋራ ይመስላል።

ብዙዎቹ ተመራማሪዎች ስለቋንቋ ፈተና ሲያነሱ ሳይገልፁት የማያልፉት ሌላው መሰረታዊ ጉዳይ የቋንቋ ፈተና የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ያሉት መሆኑን ነው። ማንኛውም የዕውቀትና የምርምር መስክ ከጊዜ ጊዜ፣ ከዘመን ዘመን እያደገ፣ እየተሻሻለ፣ እየተለወጠ ... ሄዶ ዛሬ ከደረሰበት ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ሁሉ የቋንቋ ፈተናም በረጅም ዘመን ታሪኩ የራሱ የሆኑ የዕድገት ደረጃዎች ያሉት የትምህርትና የምርምር ዘርፍ መሆኑን በመስክ የተካሄዱ ጥናቶች የሚያመለክቱት ዕውነታ ነው።

በርግጥ እነዚህን የዕድገት ደረጃዎች በመከፋፈሉ በኩል በተመራማሪዎቹ መካከል አንድ ወጥ የሆነ አተያይ የሚታይ አይመስልም። በተለይ የመጨረሻዎቹን (የቅርቦቹን) ደረጃዎች በማሳየት ልዩነት ይታይባቸዋል። ይሁን እንጂ ልዩነቶቻቸው መሰረታዊ የሆኑ ናቸው የሚባሉ አይደሉም። በአያሚ አስጣጥና በደረጃዎቹ አከፋፈል ቴዮር ላይ የሚታይ ልዩነት ነው ማለት ይቻላል።

በላይኛው አንቀፅ እንደተገለፀው የተለያዩ ተመራማሪዎች የቋንቋ ፈተና የዕድገት ደረጃዎችን ለመከፋፈልና የእያንዳንዱን የዕድገት ደረጃ መለያ ገፅታዎች ለማሳየት ሞክረዋል። ከነዚህ ውስጥ የአልደርሰን፣ ክሊፓምናዎል (1995)፣ ብራውን (1994)፣ ሂተን (1991)፣ ዌየር (1990)፣ ግድሰን (1983)፣ ሲፓልስኪ (1976) አከፋፈሎች ይገኙበታል።

ዌየር (1990) ለምሳሌ በሦስት ደረጃዎች በመከፋፈል ይገልጿቸዋል። አንደኛውን የ'ሳይኮሜትሪክ' መዋቅራውያን ዘመን /The Psychometric structuralist era/ሁለተኛውን የሥነ ልቡናዊ ሥነልሳንና ማህበረሰባዊ ስነልሳን ዘመን ፣ ሦስተኛውን የተግባቦታዊ መንገድ /The Communicative Paradigm/ በማለት።

ከታሪክ አቅጣጫ የቋንቋ ፈተና የተለያዩ ስርአታዊ ቅደም ተከተል ያላቸው ዘመናትን ያለፈ እንደሆነ የሚያስረዱት ብራውን (1994፣ 261 265) እንዲሁ ቀደምት የቋንቋው ፈተና ተመራማሪዎችን እነ ደቪስ (1990)፣ አልደርሰን (1991)፣ ስፖልስኪ (1978 b)፣ ስኪሽን (1988፣ 1989 b)ን አከፋፈል ለማድረግ የሞከሩ መሆናቸውን በክለሳ ድርሳናት መልክ ከገለፀ በኋላ ከነዚህ ምሁራን ሀሳብ በመነሳት በራሳቸው መንገድ በሶስት በመክፈል ያቀርባሉ።

የመጀመሪያውን ደረጃ ከሳይንስ በፊት ያለ ጊዜ የቋንቋ ፈተና አይነት በማለት ይጠሩታል። ጊዜው ቅድመ 1950ዎቹ ያለው ነው። የቋንቋ ፈተና ምርምር ያልነበረበት ዘመን ስለሆነ ነው ይህ ስያሜ የተሰጠው። በዚህ ዘመን የቋንቋ ፈተና የሚከተለው አጠቃላይ የፈተና መርሆዎችን ነበር። መምህራን የክፍል ፈተና የሚያዘጋጁት የሚጠቀሙባቸውን ሰዋስው ቅንርንም ወይም ንባብ ተኮር ዘዴዎችን መሰረት በማድረግ ነበር።

ሁለተኛው ዘመን /The second period / የመዋቅራውያን ዘመን በመባል የሚለየው ነው። ከ1950ዎቹ መጀመሪያ እስከ 1960ዎቹ መጨረሻ ያለውን ጊዜ የሚመለከት ነው። ንቃቃራዊ ስነልሳን የንነበት፣ መዋቅራዊ ስነልሳንና ባህሪያዊ ሥነልቡና ተዳምረው በቋንቋ ማስተማር የሳይንስ አየር የረጨበት ዘመን ነው። በዚህ ወቅት የቋንቋ ፈተና አሰጣጥ ድምፀ ልሳንን፣ ሰዋሰውንና ቃላትን እየነጣጠሉ በመፈተን ላይ ያተኮረ ነበር። በዚህ ዘመን የፈተና አሰጣጥ ምርምር የላዶ (1961) ስራ ተጠቃሽ ነው።

በዚህ ነጣጥሎ መፈተን ባህሪው ከቀጣዩ ከውሁዳዊ /integrative approaches/ ስልቶች የለያል።

ሦስተኛው ዘመን /The 3rd period/ ከ1960ዎቹ መጨረሻ እስካለንበት አስካሁን ያለው ነው። ውሁዳዊ - ማህበረ ልሳናዊ ዘመን /Integrative sociolinguistic period/ በመባል የጠራል/ይታወቃል።

በዚህ ስነስተኛው ዘመን የቋንቋ ፈተና አቀንቃኝ ምሁራን አተያይ ትኩረት የሚሰጠው ጠቅላላ የተግባቦታዊ ገፅታ ነው እንጂ ለቋንቋው ሥነልሳናዊ ክፍሎች ድምር አይደለም።

ተመራማሪዎቹ እነ ባችማን (1991) የተግባቦታዊ ችሎታን በትክክል ለመለካት የሚያስችሉ የፈተና ዘዴዎችን ፍለጋ ጥናትና ፍትነታቸውን ቀጥለዋል (ብራውን 1994፣ 261 - 265) ።

ከነዚህ እስካሁን ከቀረቡት በመጠኑ ለየት ባለ መልክ ባራት በመከፋፈል የያንዳንዱን ዘመን ያፈታተን ዘዴ ካሀርያት ሂተን (1991) ለማሳየት ሞክረዋል። በርግጥ ከብራውን (1994) የሚለዩት በተወሰነ ሁኔታ ብቻ ነው ማለት ይቻላል። ብራውን (1994) በሦስተኛ ደረጃ ባንድነት የጠቀሏቸውን በሁለት ከፍለው በማየታቸው።

አከፋፈላቸውም በሚከተለው መንገድ ነው።

1. ድርሰት ወትርጉም ስልት /The Essay Translation Approach/
2. የመዋቅራዊያን ስልት /The Structuralist Approach/
3. ውሁዳዊ ስልት /The Integrative Approach/
4. የተግባቦታዊ ስልት /The Communicative Approach/

ሂተን (1991) እንደሚያስረዱት እነዚህ የፅድገት ደረጃዎች በጊዜ ቅደም ተከተል የቀረቡ እንጂ እንዱ ከሌላው የሚጋራው የለም ለማለት አይደለም።

ጥቅል የሆነ መለያቸው እንደኖው አዘገጃጀቱ ለመምህሩ ሀሊናዊ ዳኝነት /subjective judgement/ የተተወ ነው። ጥያቄዎቹ ድርሰት መጻፍ፣ መተርጎምና የሰዋስው ትንተና ላይ የሚመሰረቱ ናቸው።

በሁለተኛው የፈተና ዝግጅቱ የሚከተለው ላይንሳዊ መንገድ አለው። ስፋ ባለ ናሙና ያምናል። የቋንቋ ክፍሎቹን እየንጣጠለና ያለአውድ የሚያቀርብ ነው።

ሦስተኛው የሁለተኛውን ስልት በመቃወም የተፈጠረ ነው። ስለዚህ ነጣጥሎ መፈተንን አያቀበልም። ለፍተና ላጠቃላይ የንግግር /discourse/ ውጤት ትኩረት ይሰጣል። ጥያቄዎችን እውናዊ ግድረት መለያ ባህሪው ነው።

አራተኛው ከሦስተኛው ይዛመዳል፣ ከትርፅና ከመዋቅር ይልቅ ላጠቃላዩ የቋንቋው ተግባቦታዊ ገፅታ ትኩረት ይሰጣል። በፈተና ስልት ከሦስተኛው የሚለየው ተማሪው በተግባቦት ሂደት ቋንቋውን እንዴት እንደሚገለገልበት መመርመር ላይ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ነው (ሂተን፣ 1991፣ 15 - 24) ።

እኔህ ተመራማሪ (ሂተን፣ 1991) የያንዳንዱን ያፈታተን ስልት በስፋት ካስረዱ በኋላ በግጠቃለያቸው የሚመክሩት ከየስልቶቹ ጠቃሚ የሆኑ የፈተና ዘዴዎችን ሁሉ በመጠቀም ተገቢ ፈተና ለማዘጋጀት መሞከሩ ተመራጭነት ያለው መሆኑን ነው።

የሆን ክፍል በንእልደርሰን (1995) ትንታኔ እናጠቃል። እነዚህኞቹ (እነ ኦልደርሰን 1995) ደግሞ እስካሁን ከቀረቡት ለየት በሚልና በተጨመቀ/ዋቅል በሆነ/ አገላለፅ ከቅርብ አመታት ወዲህ በተለያዩ የቋንቋ ማስተማር፣ የቋንቋ መማር፣ የተግባራዊ ሥነልሣን፣ የቋንቋ ፈተና፣ 'ጆርናሎች' ከሚወጡ መጣጥፎች /አርቲክሎች/ አዲስ አተያይ ጋር ይበልጥ በሚጣጣም፣ መጓኢውንም በሚያመለክት መንገድ የፅድጎት ሂደቱን ይገልፀልናል።

እንደተባለው እነዚህ የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች /ኦልደርሰን፣ ክላፓምናዎል፣ 1995/ ጥቅል በሆነ አገላለፅ እንደሚያስረዱት፣ ባለፉትሰላሳ ዓመታት የቋንቋ ማስተማርና መፈተን፣ የስነልሳንና የተግባራዊ ስነልሳን ላይ የተከሰተ አንድ ግልፅ የሆነ እውነታ አለ። ያም ፅውነታ ሁሉም ያለማቋረጥ እየተለዋወጡ የመጡና የቀጠሉ ጉዳይ ነው። እነዚህ የሚለዋወጡ ሁሉም ስለቋንቋ ተፈጥሮ፣ ስለቋንቋ ችሎታ፣ ስለቋንቋ መማር፣ ስለቋንቋ ማስተማር ያሉ እመለካከቶችና የትኞቹ ናቸው የበለጠ የቋንቋ መማሪያ የስነልሳን ችሎታ መፈተኛ መንገዶች ለሚለው ጥያቄ ሙሉ ፍለጋ የሚፈጠሩትን መላምቶች የሚያጠቃልሉ ናቸው (ኦልደርሰን ክላፓምና ሾል 1995፣ 225)።

የለውጥ ሂደቶቹም በሥነልሳን ከደረቅ የቋንቋ ስርአት ትኩረት ወደ የተለያዩ የቋንቋ አቅጣጫዎችን /dimensions/ ማወቅ መሻገርን ይመለከታል። ይህም የትርጉምን ባህረ፣ በፅረፍተ ነገሮችና በአውድ መካከል ያለን ግንኙነት፣ በቋንቋ ያለን የተጠቃሚዎችና ያጠቃቀም ልዩነትና የመሳሰሉትን መገንዘብን ይጠይቃል። በዚህም የተነሳ ስነልሳን እየሰፋ ሄዶ የተግባቦትን ማህበረልሳናዊ ገፅታዎችን የሚያቅፍ፣ የስነልሳን ውስጣዊ ችሎታ /competence/ ከተግባቦታዊ ኮምፒተንስ አኳያ እንደገና የበየነ፣ የቋንቋ ችሎታ ሞዴሎችን ከሰዋሰው ውስጣዊ ችሎታ ያሰፋና ሌሎች ኮሚፒተንሶችን (በባችማን 1995 የቀረቡትን) የጨመረ መሆኑን ያስገነዝባሉ።

ይህ ሰነልሳን ጠርፍ ያለው ለውጥና ፅድጎት በዚያው የተገታ እንዳልሆነና በተመሳሳይ ሁኔታ የቋንቋ ማስተማር፣ የትምህርት ግላግ /goal of instruction/ና መማርም እየሰፉ ሄደዉ የቋንቋን መዋቅሮችና ቃላትን ብቻ ሳይሆን ተግባርንና /function/ ሀሳቦችን /notions/ የመማርና የተግባቦት ጀዲዎችን /strategies/ ከክህል አኳያ ተገቢነት ያለው ባህሪንና ሌሎችን የሚያቅፍ እየሆነ መምጣቱን እንነህ ተመራማሪዎች ይገልፃሉ።

አሁን ያለውን ሁናቴ ሲገልፁ እንደሚሉትም ተቀባይነት አግኝቶ የነበረው የተግባቦታዊ አብሶት በተራው ተግራዎች ስለቋንቋው ማወቅ አለባቸው ስለቋንቋው ማወቅ

ተፈላጊ ጉዳይ ነው የሚለው አስተሳሰብ አቀንቃኝ /advocote/ መሆኑ እያደገ ነው። እናም የሰዋሰው ተፈላጊነት እንደገና ስር እየሰደደና ቦታውን እየያዘ እየተሸመ ነው። እነዚህ ተመራማሪዎች አክለው እንደሚገልፁት በማንኛውም የትምህርት ግቦችና ዝርዝር አላማዎች ትርጉሚ በሰፋት እየተገለፀ ነው ሰዋሰው።

እነ አልደረሰን (1995) ከዚሁ ጋር አያይዘው እንደሚያስረዱት የቋንቋ ፈተናም ከነዚህ የለውጥ (የልደገት) ሂደቶች የተለየ ሊሆን አይችልም። 1980ዎቹ የፈተና ይዘት ታላላቅ፣ የፈተና ዘዴ መጠነኛ ለውጦች የታየባቸው ወቅት ነው። በስነ ልሳን፣ በማስተማርና በመማር የተከሰቱትን አዳዲስ ትኩረቶችና ሀሳቦች ለማንፀባረቅ ነጣጥሎ የመፈተን መንገድ ይበልጥ ግብር ተኮር ለሆነ ፈተና /task based test/ ይበልጥ ውሁድ ለሆኑ ቲክኒኮች መንገድ እየለቀቀ ነው፤ ከዋኔን /performance/ መፈተን ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠበት ጊዜ ነው። በዘዴ በኩል የምርጫ ፈተናዎች /multiple choice tests/ በሌሎች ዘግ ('እብጀግቲቭ')ና ክፍት ('ኅብጀግቲቭ') ስልቶች እየተሟሉ (እየታገዙ) ነው። በዚህ ሁኔታ ይበልጥ ተገቢ የሆኑ የቋንቋ ችሎታ መመርመሪያ መንገዶች /more valid ways of assessing language proficiency/ እየተፈጠሩ ነው። መፈጠራቸውም የሚቀጥል ይሆናል።

ስለዚህም ይላሉ እነ አልደርሰን (1995) የፈተና አዘጋጆች /test developers/ ሁልጊዜ ስለፈተና የሚነሱ ጠቃሚና ተፈላጊ ጉዳዮች እንዲሁም የሚመዘኑ ችሎታዎችና ይዘቶች እንዴት ይመዘኑ በሚሉት ላይ ለሚነሱ አዳዲስ ሀሳቦች ክፍት የሆነ አዕምሮ ሊኖራቸው ይገባል /Thus test developers will always need to be open to new ideas about what it is important and relevant to test, and how those abilities and content, should be measured.) (አልደርሰን፣ ኦሊቫሞናሞል 1995፣ 226)።

2.2. የቋንቋ ፈተና አይነቶች

በቋንቋ (ፈተና) የተለያዩ የፈተና አይነቶች መኖራቸውን ከተለያዩ ፈተና ነክ የምርምር ስራዎች የምንረዳው ነው። ነገር ግን ከነዚህ ውስጥ በብዙዎቹ ተመራማሪዎች ስራ ውስጥ ተደጋግሞው ሲገለፅ የምናገኛቸው ከአራት የማይበልጡ ናቸው ማለት ይቻላል። የችሎታ መለኪያ ፈተና /Achievement test/፣ የብቃት መለኪያ ፈተና /Proficiency test/፣ የዋንኳሬና ድክመት መለኪያ ፈተና /Diagnostic test/፣ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና /Aptitude test/ የሚባሉት።

እያንዳንዳቸው ስለያዙት ትርጉም፣ እንዲሁም ስለአላማቸውና መለያ ባህሪያቸው በትንሹ (1988 እ.አ.አ) የቀረበ ስለሆነና ከላቸው ጥናት ወዲህ ይህንኑ የሚመለከትና ለዚህ ጥናትም ሊያግዝ የሚችል አዲስ ግኝት ስላላጋጠመ በቀዋታ ጥናቱ በሚመለከተው የፈተና

እይንት ላይ ብቻ እንወያያለን፣ ማለትም፣ በችሎታ መለኪያ ፈተና ላይ። ምክንያቱ ከኦልደርሰን፣ ክሊፓምና ቃል (1995፣ 12)፣ ሂዩዝ (1995፣ 10 - 11)፣ ባችማን (1995፣ 60 - 61፣ 70፣ 71)፣ ዌየር (1993)፣ ገለፃና ማብራሪያ እንደምንረዳው በትምህርት ቤት ደረጃ በክፍል የተሰጠን ትምህርት መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን የችሎታ ደረጃ ለመገምገም፣ በሴሚስተር ወይም በጭቱ መጨረሻ የሚሰጡ ፈተናዎች በዚህ በችሎታ መለኪያ ፈተና ስር የሚታቀፉ በመሆናቸውና ይህ ጥናትም ለመመርመር የሚሞክረው የዚህ አይነት ፈተናዎችን ስለሆነ ነው።

2.3 የችሎታ መለኪያ ፈተና

የችሎታ መለኪያ ፈተናን ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም ተመራማሪዎች ከተለያየ አቅጣጫ በተለያየም ሆነ በተመሳሳይ መንገድ ይገልፁታል። የቋንቋ ፈተና በሚለው ክፍል የቀረቡት አብዛኞቹ ጉዳዮችም የችሎታ መለኪያ ፈተናን የሚመለከቱ ናቸው ማለት ይቻላል። በቀጥታ "የችሎታ መለኪያ ፈተና" የሚለውን ብቻ ካነሱት ውስጥ ጥቂቶችን ብንመለከት፣ ለምሳሌ ሀይዩዝ (1988፣ 36) የተጠቀሱት አንስታዚ (1976፣ 398) የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች " የተወሰነ የትምህርት ፕሮግራምን ወይም ስልጠናን ውጤቶች ለመመዘን የሚሰጡ ናቸው" በማለት ይበይኑታል። አልደርሰን (1988፣ 16) ደግሞ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በሲለበሶች ላይ የሚመሰረቱና አንድን የተለየ ሲለበስ ተግራዎች ምን ያህል እንደተማሩ ለመለካት /ለመመዘን/ ጎላ የሚሰጡ ናቸው፣ ይሏቸዋል።

እንደሌሎቹ ተመራማሪዎች ሁሉ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ስር /root/ ከተወሰኑ አቅጣጫዎች አኳያ በቀደሙ የክፍል ትምህርት ልምዶች /experiences/ ላይ የሚመሰረቱ እንደሆኑ የሚያመለክቱት ዌየር (1993፣ 5) እንደሚሉት የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ቀድሞ በክፍል ከተሰጠው ትምህርት ጋር የማይያያዙ /የማይገናኙ/ ከሆኑ ሁልጊዜም ችግሮች መኖአቸው አይቀሬ ነው (ዌየር 1993፣ 6)።

የዚህ ፈተና አይነት አጠቃላይ አላማም ተማሪዎች በትምህርቱ (በኮርሱ) የተማሩትን ቀጋ በሙሪጻትና በማፍለቅ /receptively and productively/ መጠቀም መቻላቸውን ለማወቅ ነው (ዌየር 1993፣ 5)።

ባጠቃላይ ከላይ የፈተና አይነቶች በሚለው ክፍል ከተጠቀሱት ምሁራን የተለያየ አገላለፅ በተጨማሪ ከሂቀን (1975፣153፣ 1990፣ 14) ቀጥተኛ ማብራሪያ እንደምንረዳው በየጭቱ የሚሰጡ የትምህርት ቤት ፈተናዎች፣ የተወሰነ የትምህርት ዝርዝር መዳበሩን ወይም መጠናቀቁን ለማረጋገጥ በሰፊር አቀፍ ደረጃ የሚሰጡ ፈተናዎች የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ናቸው።

እንዚህ በሂተን (1975፣ 1990) የተዘረዘሩት የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በትምህርት ሚኒስቴር፣ በፈተና ቦርዶች፣ በትምህርት ተቋማቱ አባላት (በመምህራን) ሊዘጋጁ ይችላሉ (ሂዩዝ 1995፣ 11) ። ስለዚህ የእስራ ሁለተኛ ክፍል የሞዴል ፈተናዎች በትምህርት ተቋማቱ አባላት /በትምህርት ቢቶቹ መምህራን/ የሚዘጋጁ ስለሆኑና ሌሎች የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችን ጥልማና ባህርያት የሚያሟሉ ስለሆኑ በዚህ የፈተና አይነት ውስጥ የሚታቀፉ ናቸው ማለት ነው።

2.4 የችሎታ መለኪያ ፈተና ይዘት መስረቶች

በችሎታ መለኪያ ፈተና ምንነትና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ በተመራማሪዎች መካከል ይኽ ነው የሚባል ልዩነት ያለ አይመስልም። ልዩነት ያለው የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ይዘት መስረት ምንድነው? ወይም ምን ይሁን? በሚለው ዙሪያ ነው። በዚህ ጉዳይ ምሁራኑ በሁለት ጎራ የተከፈሉ ነው የሚመስለው። እንደኖው ጎራ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች መስረት ለትምህርት የቀረበው ሙርሀ ትምህርት ይዘቶች መሆን አለባቸው በማለት የሚከራከሩ ክፍሎችን የያዘ ሲሆን ሌላኛው የለም፣ ይዘቶቹ ላይሆኑ የትምህርቱ /የኮርሱ/ ግቦች (አላማዎች) ናቸው መስረት መሆን ያለባቸው የሚል አጽም ይዘው የሚከራከሩትን ያቀፈ ነው።

ኦልደርሰን (1988)፣ ግድሰን (1983)፣ ሀራሰን (1983)፣ ሂተን (1975)፣ ከመጀመሪያው ጎራ ተሰላፊዎች ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ፤ ሂዩዝ (1988፣ 1995)፣ ባችማን (1995)፣ ዊየር (1993)፣ ሂተን (1990) በተቃራኒ ጎራ ተሰልፈው የፈተናዎቹ ተዛምዶ ከአላማዎቹ ጋር መሆን አለበት ከሚሉት ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

ከላይ በጥቅሉ ለመግለፅ እንደተሞከረው በመጀመሪያው ጎራ የተሰለፉት እነ ኦልደርሰንና ሌሎች የተወሰኑ የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች የሚሉት የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ይዘት መስረቶች መሆን ያለባቸው የመርሀ ትምህርት ይዘቶች ካስፈለገም ከመርሀ ትምህርት ይዘቶች በተጨማሪ የመግለያ መፅሐፍትና ሌሎች መሳሪያዎች መሆን ይችላሉ፣ ነው። የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በመርሀ ትምህርት የቀረበ ይዘትን ተማሪው ምን ያህል እንዳወቀ መለያ መሳሪያዎች ናቸው የሚል እንድምታ ያለው ይመስላል። የኦልደርሰን (1988፣ 16) አንድ የችሎታ መለኪያ ፈተና ተገቢ /valid/ ነው የሚባለው የመርሀ ትምህርቱን ይዘት በበቂ ናሙና በማከል ብቃቱ ነው። መርሀ ትምህርቱን በበቂ ናሙና በትክክል ከሸፈነ ያ ፈተና ተገቢ የችሎታ መለኪያ ፈተና ነው ሊባል ይችላል። ካልሸፈነ ተገቢ የችሎታ መለኪያ ፈተና ነው ሊባል አይችልም፣ የሚለው ግብራራያ ይህንኑ የሚያጠናክር ይመስለናል።

በሌላኛው ጎራ ከተሰለፉትና ይህን የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ይዘት መስረት የመርሀ ትምህርት ይዘት ነው የሚለውን አስተሳሰብ ከሚቃወሙት መካከል አንዱ የሆኑት ሂዩዝ (1988) የመርሀ ትምህርት ይዘትን መስረት ማድረግ ተገቢ አለመሆኑን አውስተው በዚያኛው

/በሚቃወሙት/ ነገሩ ያለውን የእንዳንድ ተመራማሪዎች የፈተና ይዘት መሰረት ድንበር ሲገልፁ፤ እንዳንድ የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች እንዲያውም ከዚህም አልፈው /የመርሀ ትምህርት ይዘት ከሚለው/ የፃሑታ መለኪያ ፈተናዎች ይዘት ለትምህርቱ /ለኮርሱ/ በተዘጋጁ መሳሪያዎች ላይ በቀጥታ መመሰረት አለበት የሚል ሀሳብም ያቀርባሉ /Some writers on language testing go further and propose that achievement test content can be based directly on the texts used on the course.) (ገፅ፤ 39) በማለት ከገለፁ በኋላ ነገር ግን የማያሳልፅና ብዙ ጉዳት ሊያመጣ የሚችል እንደሆነ፤ ከዚህ ይልቅ የትምህርቱን አላማዎች መሰረት ማድረጉ እንደሚበጅ ይመክራሉ።

ከዚሁ ጋር አያይዘውም እነ አልደርሰን (1988)ንና ሌሎች የነአልደርሰን ተከታዮችን መርሀ ትምህርት በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት /ኮርስ/ ራሱ ፣ መማሪያ መፅሐፎቹንና ሌሎች መሳሪያዎችን ጨምሮ አላማዎችን ከግብ የማድረሻ መንገዶች /means to an end/ ናቸው። የአንድ የፃሑታ መለኪያ ፈተና አጠቃላይ አላማ ደግሞ የትምህርቱ አላማ ከግብ መድረስ አለመድረሱን ለመወሰን ነው። እናም መሰረት ማድረግ ያለበት የትምህርቱን አላማዎች ነው፤ እያሉ ሲከራከሩ /የሚል አቋም ሲያራምዱ/ የነበሩት ሂዩዝ (1988፤ 40) በ (1989) ሌላ የምርምር ስራቸውም ይህንኑ ጉዳይ በሚመለከት እንስተዋል። በዚህኛው ስራቸው ከቀዳሚው ለዘብ ባለ አገላለፅ እንደሚያስረዱት ፈተና ተማሪዎች ሲማሩ ያጋጠማቸውን ትምህርት ብቻ እንዲይዝ መሆኑ መልካም ነው፤ በተወሰነ ገፅታው ሲታይ ትክክለኛ ፈተና ነው /fair test/ የሚያስብል ነው። ነገር ግን መርሀ ትምህርቱ መጥፎ ሆኖ የተቀረፀ፤ ቢሆን ወይም የመፅሐፎቹና ሌሎች መሳሪያዎች አመራረጥ ጉድለት የሚታይበት ከሆነ የፈተናው ውጤቶች የትምህርቱ አላማዎች ግብ መምታታቸውን ላያሳዩ ስለሚችሉና ወደተሳሳተ አቅጣጫ መምራታቸው አይቀሬ ስለሚሆን ነው የፈተና ይዘትን በመርሀ ትምህርቱ ይዘት ላይ መመሰረቱ የሚጠላው። የመርሀ ትምህርቱ ይዘትን መሰረት አድርጎ ፈተናን ማዘጋጀቱ ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት ለማሳየትም የተለያዩ ምሳሌዎችን አቅርበዋል። ከትምህርቱ /ከኮርሱ/ አላማዎች አንዱ የጭውውት ችሎታን /conversational ability/ ለማዳበር ቢሆን ነገር ግን ትምህርቱና ፈተናው ተማሪዎች በተለያየ ርዕስ ላይ ተዘጋጅተው ንግግር እንዲያደርጉ የሚያደርግ ብቻ ከሆነ የፈተና ውጤቱ የተማሪዎቹን ችሎታ ከአላማዎቹ አንፃር ለማሳየት አልተቻለውም ማለት ነው የሚለው ከምሳሌዎቻቸው አንዱ ነው።

ባንፁሩ፤ እነሀ ተመራማሪ ከዚሁ ጋር አያይዘው እንደሚያስረዱት፤ የፈተናዎቹ ይዘት ባለማ ዎች ላይ የሚመሰረት ከሆነ የተለያዩ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል። ይኸውም - አንደኛ የትምህርቱ ነዳፎች አላማዎቻቸውን በግልፅ እንዲፅፉ ያስገድዳቸዋል። ሁለተኛ ተማሪዎቹ ፈተናውን የሚሰሩት ምን ያህል የተዘረዘሩትን አላማዎች ከግብ እንዳደረሱ ለማሳየት ነው። እንዚህ በተራቸው መርሀ ትምህርት በሚያዘጋጁት፤ መፅሐፍና ሌሎች መሳሪያዎች በሚመርጡት (በእኛ ሀገር ሁኔታ አሁንም በሚያዘጋጁት) ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ ፣ ከአላማዎቹ ጋር የሚጣጣሙ ለማድረግ ማለት ነው።

አላማን መሰረት ያደረገ ፈተና ተፈላጊ የባክዋሽ ውጤቶችን ማስገኘት የሚችል ነው ... መርሀ ትምህርት ለማሻሻል፣ የመማሪያ መፅሐፎችን ለማዘጋጀት፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመቀየር ... በግለት በተግባር ያዩትን የራሳቸውን የቦጋዚ (/Bogazici/ ዩንቨርሲቲ ገጠመኝ በፅሁፍነት በመዋቀስ የሁለተኛው ንራ አመለካከት የተሻለ እንደሆነ የራሳቸውም እምነት መሆኑን በ(1988) ስራቸው (ገፅ 42) ይፋ ያደረጉት ሂዩዝ፣ በዚህኛው መፅሐፋቸውም ይህን ጉዳይ አንስተው በተከራከሩበት ክፍል ግጠቃለያ፣ እንዲሁ "የፈተና ይዘትን በኮርስ (በትምህርት) አላማዎች ላይ መመሰረቱ በጣም ተመራጭነት ያለው መንገድ የመሆኑ ጉዳይ የእኔም እምነት ነው። ስለግላዊና ቡድናዊ ችሎታ የበለጠ ትክክለኛ መረጃ ሊሰጥ ይችላል። መልካም (አዎንታዊ) የሆነ የባክዋሽ ውጤት በማስተማሩ ላይ ሊያመጣ ይችላል።" (It is my belief that to base test content on course objectives is much to be preferred. It will provide group achievement, and it is likely to promote a more beneficial backwash effect on teaching) በግለት ያንኑ አቋማቸውን የሚያጠናክሩ መሆናቸውን ገልፀዋል (ሂዩዝ 1995፣ 11)።

የሂዩዝ (1988፣ 1989)ና የሌሎችን መሰል አተያይ ከሚጋሩት ውስጥ አንዱ የሆኑት ቮይዝማን (1961) እንደሚሉት የችሎታ መለኪያ ፈተናን በይዘት ላይ የመመሰረቱ ስልት ውጤት አልባ የሆኑ ትምህርታዊ አተገባበሮች ባሉበት እንዲዳክሩ /እንዲቀዮሉ/ ማድረግ ነው (The syllabus content approach tends to perpetuate ineffective educational practices)። በተቃራኒው ግብ (አላማ) ተኮር /መራሽ/ ፈተና /goal oriented test/ ከሲለበስ የፀዳ መራቅ ስልት ተቃራኒ የሆነና መግር ማስተግርን ከሰርአተ ትምህርቱ አላማዎች አኳያ በትክክል የሚገመግም ነው፤ ይላሉ (ቮይዝማን 1961፣ 148 በሂዩዝ 1988፣ 40 ውስጥ)።

በተገቢ መንገድ የተዘጋጁ አላማን መሰረት ያደረጉ፣ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በብዙ አቅጣጫዎች አምንታዊ የሆነ የባክዋሽ ውጤቶችን ማስገኘት የሚችሉ መሳሪያዎች ናቸው የሚለውን የነሂዩዝ ሀሳብ ከሚጋሩት ውስጥ ዌየር (1990፣ 1993) ሌላው ናቸው። በ (1993) ስራቸው ለምሳሌ ፈተናዎች በማስተግር ላይ እጅግ በጣም ጠቃሚና ሀይል ያለው የባክዋሽ ውጤት የሚያመጡ ናቸው። ዘመናዊ የመርሀ ትምህርት ስልትን የሚያንፀባርቁ አዳዲስ የማስተግሪያ መሳሪያዎች ቢዘጋጁ፣ መምህራን በአዳዲስ መሳሪያዎችና አዳዲስ ሥነዘዴዎች ቢሰለጥኑ ከነዚህ ሁኔታዎች /ክስተቶች/ ጋር የሚስማሙ ፈተናዎች ከሌሉ ሁሉም ነገር ከንቱ ከመሆን አይዘልም ይላሉ (ዌየር 1993፣ 6)።

ባጠቃላይ ትምህርት መስክ ያለው ፅውንታም ከዚህ የተለየ አይመስልም። ለምሳሌ ግሩላንድ (1988፣ 1) ስለዚሁ ስለችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ሲገልፁ ጥሩ ሆነው የተዘጋጁ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱን የተለያዩ አቅጣጫዎች መደገፍና

ግጠናከር የሚችሉ መሆናቸውን፣ የመምህሩንና የተማሪውን የመማር ዝግጁነት በመመርመር፣ የመማር ፅድንትን በመቆጣጠር፣ ለመማር አስቸጋሪ የሆኑ ክፍሎችን በመጠቆም ... እና የትምህርቱን ግቦች በመገምገም የሚረዱ መሆናቸውን ነው ያመለከቱት።

የፕሎታ መለኪያ ፈተናን የይዘት መሰረት በሚመለከት በስፋት ለመመልከት እንደተሞከረው መታረቅ ያልቻሉ ሁለት ንራዎች /አመለካከቶች/ መኖራቸውን ነው ለመረዳት የተቻለው። ሁለቱም የተለያዩ ምክንያቶችን እያቀረቡ የሚከራከሩ ናቸው። በዚህም የተነሳ በዚህ ጥናት የሞዱል ፈተናዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂሎች የይዘት አግባብነት /content validity/ ከየትኛው ንራ አመለካከት አንፃር ማየቱ ይሻላል? የሚለውን ለመወሰን አስቸጋሪ ሆኖ ነው የተገኘው። ሙህራኑ የሚከተሉት የትኛውን አቅጣጫ እንደሆነም የሚታወቅ አይደለም። እናም አግራጭ ሆኖ የተገኘው ከሁለቱም አመለካከቶች አኳያ ፈተናዎችን ለመመርመር ሙከሩ ነው። ሆኖም ከሁለቱም አኳያ ለማጥናት ሲጀመር ደግሞ ሌላ ችግር ብቅ ማለቱ አልቀረም። ይኸውም የትምህርት መሳሪያዎቹ አላማዎችና ውስጥ ግልፅነት የሌላቸው፣ ከአንብቦ መረዳት ክሂል ጋር ተዛምዶ የሌላቸው፣ ተግባራዊ የማይሆኑ የተካተቱባቸው፣ እንዲሁም አጋዥነታቸው በተለያዩ ጥናቶች የተመሰከረላቸው ነገር ግን በንዚህ መሳሪያዎች (በተለይ በመርሀ ትምህርቱ) ያልታቀፉ ሆኖ መገኘት ዋነኛዎቹ ችግሮች ናቸው (ግስተቸል (1989 እ.ኤ.አ.)፣ ጌታቸው (1986 እ.አ.አ.)፣ በየነ (1985 እ.ኤ.አ.))።

በርግጥ በአላማ አንጻጻፍ በኩል ያለው ችግር የአማርኛ ብቻ አይመስልም። በሌሎች ትምህርት መስኮችም ስር የሰደደ፣ ከዘመን ዘመን ሊወገድ ያልቻለ ሀገራዊነት ያለው ነው የሚመስለው። ይህን እውነታ ግረው (1992) አበበ (1974፣ 1986) ጠቅሰው ያለውን፣ ሊወገድ ያልቻለ ችግር ከገለፅልንበተጨማሪ በሌሎች የትምህርት መስኮች (በታሪክ፣ በሳይንስ) የይዘት አግባብነትን /content validity/ ያጠኑ ኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች የነብሉም (1956) የባህሪ ከፍፍል /taxonomy/ ለመጠቀም መገደዳቸው ሌላው ምስክር ነው። ከተለያዩ ሌሎች ጥናቶች ር ቱዓና አረ ቱዕ አንሳልፅ መረዳት እንደሚቻለው ችግሩ በሌሎች ሀገሮችም የሚታይ ይመስላል።

በዚሁ ጥናት የይዘት አግባብነት በሚል ርዕስ ከቀረበው ክለሳ ድርሳን ነክ ምላሌዎች መረዳትም እንደሚቻለው በቋንቋም የአንድን ፈተና የይዘት አግባብነት ለመመርመር (አንብቦ መረዳትን ጨምሮ) በተመራማሪዎች የወጡ ሞዴሎችን /ቸክሊስቶችን/ መጠቀም የተለመደ ነው። ስለዚህ ይህ ጥናትም ይህን ያላማዎችን አጠቃላይ መሆን ችግር ለመፍታት የሚሞክረው በተለያዩ ተመራማሪዎች የቀረቡ በአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ሊመዘኑ የሚችሉ ክሂሎች ቸክሊስቶች /ሞዴሎች/ ውስጥ ከአማርኛ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎች ጋር በማገናዘብ ለፈተናዎቹ መመርመሪያ "ቸክሊስት" በማዘጋጀት ይሆናል።

ከይዘት አኳያ ለሚካሄደው ምርመራ ግን የመርሀ ትምህርቱን የአንብቦ መረዳት ይዘቶች ከመጠቀም ሌላ ሌላ እግራጭ ያለ አልመከለንም። በዚህም የተነሳ ምርመራው በቀጥታ የፈተናዎቹን ጥያቄዎች ከመርሀ ትምህርቱ የአንብቦ መረዳት ይዘቶች ጋር በማዛመድ የሚከናወን ይሆናል ማለት ነው።

2.5 አግባብነት /Validity/

አልደርሰን፣ ክላፓምና ፆል (1995)፣ ባችማን (1995) ሂዩዝ(1995)፣ ዴቪስ (1988) እና ሌሎችም እንደሚያስገነዝቡት በቋንቋ ፈተና ተሟልተው ሊገኙ የሚገባቸው በጣም ጠቃሚ፣ አስፈላጊና መሰረታዊ ባህርያት ህያውነት (reliability)፣ ተተግባሪነትና (practicality) አግባብነት ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ የአግባብነት ጥያቄ ቀዳሚውና ዋነኛው ነው።

በሌሎች የፅሁፋት መስኮች የተሰማሩ ተመራማሪዎችም ቢሆኑ ከዚህ የተለየ አተያይ ሲያራምዱ አይታዩም ግለት ይታላል። ለምሳሌ በግሩላንድ (1988)፣ አንስታንዚ (1982)፣ ላትሪል (1994) ስራዎችም አግባብነት ከፈተና ዋና ዋና ባህርያት ውስጥ አንዱና ዋነኛው እንደሆነ ነው ተገልጾ የምናገኘው።

በቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች አተያይ ብንነሳ "ፈተናው እንዲፈትን የታሰበውን ፈትኗል" የሚለው ጥያቄ የአግባብነት ጥያቄ እንደሆነ በሚያመለክቱት አልደርሰን፣ ክላፓምና ፆል (1995፣ 170) የተጠቀሱት ሄኒንግ (1987፣ 89) አግባብነትን የበየኑት በጥቅሉ የአንድን ፈተና ትክክልነት ወይም እምንጻፍ የፈተናው ክፍል እንዲመዝን የታለመውን መመዘኑን የሚመለከት እንደሆነና አንድ ፈተናም ተገቢ /valid/ ነው የሚባለው እንዲመዝን የታሰበውን በመመዝበት መጠን ነው በማለት ነው።

እንደ ባችማን (1995፣ 25) አተያይ ደግሞ ፈተናን ለመተርጎም (ለመተንተን) /interpretation/ ወይም ለመጠቀም ትልቁና የመጀመሪያው ብቃት አግባብነት ነው። ይህም በፈተናው ውጤቶች ትርጉም ለጭነት /meaningfullness/፣ ተገቢነትና /appropriateness/ ጠቃሚነት /usefulness/ ላይ ተመስርተው የሚሰጡ ግጠቃለያዎች /inferences/ ወይም ውሳኔዎች /decisions/ ላይ መድረስን የሚያጠቃልል ነው። በግሩላንድ (1988፣ 136) ና በራሳቸው በባችማን የተጠቀሰው የአሜሪካ የሳይኮሎጂ ማህበር /American Psychological Association/ ብያኔም በባችማን ከተገለፀው ጋር አንድ አይነት ይዘት ያለው ነው።

ቤክርስን (1994፣ 2) የተገለፀው የአግባብነት ምንነት ከላይ ከተመለከቱት ለየት የሚለው ከግብር አኳያ ጭምር የተብራራ በመሆኑ ነው። እንደላቸው አተያይ አግባብነት ተማሪውን ለመመዘን በቀረበው ግብር /task/ መመዘን የሚገባቸው ክሂሎች፣ ዕውቀት፣ ዝንባሌና /attitude/ ሌላ ሊመዘን የታቀደ ችሎታ ምን ያህል በበቂ መንገድ ተንፀባርቀዋል የሚለውን የሚመለከት ነው።

ባጠቃላይ ፈተና፣ መስኩ በሚመለከታቸው የሙያ /professional/ ድርጅቶች በአሜሪካ የትምህርት ምርምር ማህበር፣ በአሜሪካ የሳይኮሎጂ ማህበርና በትምህርት ምዘና ብሔራዊ 'ካውንስል' ብለው በዘረዘሯቸው ከፍሎች አተረጓጎም መሰረት አግባብነት የሚከተሉትን ፍች የያዘ እንደሆነ ግሩላንድ (1988፣ 136) ይገልፃሉ።

1. አግባብነት በቀላሉ ከሚገኝ መረጃ የሚደረስ መደምደሚያ ነው።
2. አግባብነት በብዙ የተለያዩ የመረጃ አይነቶች ላይ የተመሰረተ ነው።
3. አግባብነት በደረጃ/ዲግሪ/ የሚገለፅ ነው /ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ/ ተብሎ
4. አግባብነት ለተለየ ጥቅም የተለየ /የተወሰነ/ ነው።
5. አግባብነት ፈተናውን ራሱን ሳይሆን ከፈተናው የሚገኙትን ማጠቃለያዎች /መደምደሚያዎች/ የሚመለከት ነው።
6. አግባብነት አንድ ውህድ ፅባቤ ነው።

የተለያዩ ተመራማሪዎችን ብያኔና ማብራሪያ በዋቢነት በመጥቀስ ለመመልከት ከተሞከረው መረዳት እንደሚቻለው አግባብነት ከፈተና ዋና ዋና ባህርያት ውስጥ አንዱ ሆኖ ፈተናው እንዲመዝን የታሰበውን መመዘን መቻል አለመቻሉን የመመለስ ጥያቄን የሚመለከት ነው። ቃላትን ለመመዘን የታቀደ የቃላትን ችሎታን እንጂ ሌላ ፅውቀት ወይም ክሂልን የሚመዝን መሆን የለበትም ማለት ነው።

የፈተና ውጤቶች፤ ትርጉም የሚሰጡ፣ ተገቢነት ያላቸው፣ ጠቃሚ የሆኑ የመሆን አለመሆናቸው ውሳኔዎችና መደምደሚያዎችም የሚመሰረቱበት ነው።

2.6 የአግባብነት አይነቶች

ከፍ ብሎ በግሩላንድ የአግባብነት ፍች እስማት በተራ ቁጥር ስድስት የተጠቀሰውና የህ ንዑስ ርዕስ የሚዳሩ ሊመስል ይችላል። አግባብነት "አንድ ውህድ አሳቤ ነው" ብሎ የአግባብነት "አይነቶች" ማለቱ። ነገር ግን ባችማን (1995) ና ግሩላንድ (1988) በስፋት እንደሚያስረዱትና እነ አልደርሰን (1995)ም እንደሚደግፉት የሚዳረር አይደለም። በርግጥ ከነዚህ ምሁራን የቀደምት ጥናቶች ከለላ ማስተዋል እንደሚቻለው ቀደም ሲል የአግባብነት አይነቶች ሲባል የተለያዩ የአግባብነት አይነቶችን የሚመለከት ነበር። በዘመናችን የቋንቋም ሆነ የሌላ ፅውቀት መስክ ፈተና ተመራማሪዎች አተያይ የአግባብነት አይነቶች ሲባል የዚያው የአንዱ ውህድ የአግባብነት ፅባቤ የተለያዩ የመረጃ አይነቶች ላይ የሚመሰረት አይነትነት ነው።

በዚሁ መነሪት በዘመናችን የፈተና ሊቃውንት አተያይ የይዘት አግባብነት ጥናት ሲባል ለምሳሌ ከፈተናው ይዘት አቅጣጫ የአግባብነት ማስረጃን ማጥናትን የሚመለከት ነው ማለት ነው (ባችማን 1995፣ 237፣ ግሩላንድ 1988፣ 136)።

አሁን የሚታመንበትን የቋንቋ ፈተና አግባብነት አይነቶች የተለያዩ ተመራማሪዎች በተመሳሳይም መጠነኛ ልዩነት በሚታይበት መንገድም ለመከፋፈል ሞክረዋል። ከነዚህም ውስጥ በሂዩዝ (1995) ስራ የይዘት፣ 'የክራይቴሪያ' ጠቀስ፣ 'የኮንስትራክት'ና የላህይ አግባብነት በመባል በአራትኧ በዌየር (1990) የኮንስትራክት፣ የይዘት፣ የላህይ፣ የ'ምሽባክ'ና የክራይቴሪያ ጠቀስ አግባብነት በመባል በአምስትኧ በባችማን (1995) የይዘት፣ የክራይቴሪያን፣ የኮንኮረንት፣ የተንባይ፣ የኮንስትራክትና የላህይ አግባብነት በመባል በስድስትኧ በዴቪስ (1988) የይዘት፣ የላህይ፣ የኮንስትራክትና የተንባይ (ኮንኮረንት) በመባል በአራት ተከፍለው እናገኛቸዋለን።

በንኦልደርሰን (1995) አከፋፈል መሰረት ደግሞ ዋና ዋናዎቹ ውስጣዊ /internal/ ና ውጫዊ /external/ አግባብነት በመባል በሁለት ዘርፍ ተጠቃለዋል። የመጀመሪያው (ውስጣዊ አግባብነት) በፈተናው ይዘትና በይዘቱ ውጤት ላይ ከሚካሄዱ ጥናቶች ጋር የተያያዘ ሲሆን ሁለተኛው የተግሪዎችን የፈተና ውጤቶች /scores/ ከፈተናው ውጭ ካሉ የችሎታዎቻቸው መለኪያዎች ጋር ከግወጻጸር ጋር የተያያዙ ጥናቶችን የሚመለከት ነው። ራሳቸው (እነ ኦልደርሰን) እንደሚጠቁሙት ሁለተኛው የአግባብነት አይነት በሌሎች ተመራማሪዎች "ክራይቴሪያ" በመባል የሚጠራው ነው።

በዚህ በንኦልደርሰን (1995) ጥናት መሰረት በውስጣዊ ስር የይዘት፣ የላህይና የምላሽ /response/ አግባብነት ሲታቀፉኧ ኮንኮረንትና ኮንስትራክት አግባብነት በውጫዊ አግባብነት ስር ተጠቃለዋል።

ከነዚህ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የይዘትና የላህይ አግባብነት ይህ ጥናት የሚመለከታቸው ናቸው። ስለዚህ ሁለቱን በተለይ ዘርዘር አድርጎ መመልከት አስፈላጊ ሆኖል።

2.6.1 የይዘት አግባብነት

ከኦልደርሰን ክሊፖርና ፆል (1995) ሂዩዝ (1995)፣ ባችማን (1995) ዌየር (1990)፣ ዴቪስ (1988)፣ ግሩላንድና ሮበርት (1990)፣ ብራውን (1994) ግሩላንድ (1988) ሀሪሊን (1994)፣ ሆፕኪንስና እንቴስ (1989)ና ከሌሎችም የቋንቋ፣ የሥነልቡናና የሥነትምህርት ፈተና ነክ ተመራማሪ ሊቃውንት ገለፃና ማብራሪያ እንደምንረዳው በተለይ በችሎታ መለኪያ ፈተና የይዘት አግባብነት ዋናው የአግባብነት ክፍል ነው።

ምንኑቴን፣ በውስጡ የሚያቅፋቸውን ጉዳዮችና ሌሎች ገፅታዎቹን ቀጥሎ በቅኝት መልክ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

ቡዬና (1990፣ 25) የተጠቀሱት አንስታንዚ (1982፣ 131) ለምሳሌ የይዘት አግባብነትን የበየኑት የፈተናው ይዘት የሚመዘኑትን የባህሪ ክፍሎች በትክክል መሸፈን አለመሸፈኑን ለመወሰን የሚደረግ ስርአታዊ ምርመራ /systematic examination/ እንደሆነ በመግለፅ ነው።

በቂንቋ ፈተና ተመራማሪዎች የሚሰጠው ብያኔም ከዚህ የተለየ አይደለም። ለየት የሚልበት አቅጣጫ ቢኖር የሚወክለው ባህሪ ክሂል፣ አገባብ፣ ... እየተባለ የሚጠራ ከመሆኑ ላይ ነው ማለት የሚቻል ይመስላል። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን የሂዩዝ (1995፣ 22) አገላለፅ ነው። እንደላቸው አንድ ፈተና የይዘት አግባብነት አለው ሊባል የሚችለው የፈተናው ይዘት መያዝ የሚገባውን ክሂሎች፣ አገባብ ... ወዘተና ሌሎች ክፍሎች ተመጣጣኝ (ወካይ) በሆነ ናሙና ያቀረበ ሆኖ ሲገኝ ነው።

የይዘት አግባብነት የይዘት ተገቢነትና (content relevance) የይዘት መሸፈን (content coverage) የሚባሉ ሁለት መሰረታዊ መልኮች ያሉት፣ በአጠቃላይ በውስጡ የይዘት ወይም ቱሉታ ክፍሎች የፈተና ዘዴዎች (facets) ልየታ (specification) እንዲሁም በፈተናው የሚካተቱት ግብሮች /tasks/ የክፍሎቹ (የዶሚኖቹ) ወኪል መሆናቸውን ማሳየትን የሚይዝ መሆኑንና በቂንቋ ፈተና ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻው እንደሆነ የሚያስገነዝቡት ባቻማን (1995) በፈተና ውስጥ የይዘት አግባብነትን ደረጃ እንደሚያመለክቱት ከሆነ አንድን ፈተና ለመጠቀም መጀመሪያ የሚመረመረው ይዘቱ ነው። ለማዘጋጀትም /developing a test/ የመጀመሪያው ተግባር የይዘት ወይም የቱሉታ ዶሜኑን መበየን ነው ። ጥያቄዎቹ ወይም የፈተናው ግብሮች የሚፈልቁበትን (ባቻማን 1995፣ 244)።

ስለዚህ በሁለቱም ግለትም በፈተና ለመጠቀም ሲፈለግም ሆነ አዲስ ፈተና በሚዘጋጅበት ጊዜ ለፈተናው ይዘት አግባብነት ትኩረት የመስጠቱ አስፈላጊነት ከፍተኛ ነው ግለት ነው፤ ላፍታም ቢሆን ሊዘነጋ የማይገባው።

አንድን ፈተና በአምንታዊነት የሚፈረጅ የይዘት አግባብነት ያለው እንዲሆን አድርጎ ማዘጋጀቱም ሆነ የተዘጋጀውን መርምሮ የይዘት አግባብነት ደረጃው ከፍተኛ መሆን አለመሆኑን ግራጋንጩ ቀላል እንዳልሆነ ግን ተመራማሪዎቹ ላያስገነዝቡ አልቀሩም። ይሁን እንጂ ይህን ተግር ለግቶለል የሚያግዙ ስልቶችንም እየፈለጉና እያመለከቱም ነው ማለት ይቻላል። ከነዚህ ስልቶች ውስጥ ቡዬና (1990) ስራ ተዘርዝረው የምናገኛቸውን የአንስታዚ ጠቃሚ መመሪያዎች መጥቀስ ይቻላል። ቄየር እንደሚያስረዱት እነዚህ የሚከተሉት የአንስታዚ መመሪያዎች የይዘት አግባብነትን ለግግኘት የሚያስችሉ ናቸው። እነሱም ፦

1. ሁሉም መፈተን የሚገባቸው ዋና ዋና ክፍሎች በፈተናው ጥያቄዎች እንዲሸፈኑና ተመጣጣኝ ውክልና እንዲያገኙ የሚመዘኑት የባህሪ ክፍሎች ስርአታዊ በሆነ መንገድ የግድ መተንተን አለባቸው።

('the behaviour domain to be tested must be systematically analysed to make certain that all major aspects are covered by the test items, and in the correct proportions',)

2. ትኩረት የሚሰጠው ዶሜን በሚገባና በተሟላ መልክ በቅድሚያ መገለፅ አለበት . ፈተናው ከተዘጋጀ በኋላ አይደለም።

('the domain under consideration should be fully described in advance, rather than being defined after the test has been prepared',)

3. የይዘት አግባብነት የሚመሰረተው የየግለሰብ /የየተማሪው/ ፈተና መልሶች ከ፣ ትኩረት ከተሰጣቸው የባህሪ ክፍሎች ጋር ባለው ተገቢ ዝምድና /ግንኙነት/ ላይ ነው።

('content validity depends on the relevance of the individual's test responses to the behaviour area under consideration, rather than on the apparent relevance of item content.') (ቺየር1990፣ 25)።

የይዘት አግባብነት ፈተናው ተገቢ የሆነ /relevant/፣ መሆኑንና የቋንቋ ክሂሎችን ወካይ በሆነ ናሙና የመሸፈን ብቃቱን የሚመለከት ነው የሚሉት እነ አልደርሰንም አንድ ፈተና መመዘን የሚገባቸውን ክሂሎች በወካይ ናሙና መመዘን መቻል አለመቻሉን ለማረጋገጥ ወይም ለማየት /to see/ የፈተናውን ይዘት ተጠየቅን /logic/በተከተለ ስልት መተንተን ላይ የተመሰረተ መሆኑን በመግለፅ መላ ያመለክታሉ (አልደርሰን፣ ክላፓምና ዎል 1995፣ 171)።

ለማጠቃለል፣ እስካሁን ከተነሱት የቋንቋ ፈተና ተመራማሪ ሊቃውንት ሰራዎች ብየና ገለፃና ግብራብያ መረዳት የተቻለው በቋንቋ ፈተና የይዘት አግባብነት የአንድ ፈተና ናሙና ተመጣጣኝነት (proportional)፣ ወካይነት (representativeness) በቂነትና (adaquacy) ሊመዝኑ የሚገባቸው የክሂልና የፅሁፍ ክፍሎች የመሸፈን ብቃት (quality) ላይ የተመሰረተ (የሚያጠነጥን) መሆኑን ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት የተለያዩ የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች በተጨማሪ በይዘት አግባብነት ቁልፉ አካል (key element) የናሙናው በቂነት ነው የሚሉት ግሩላንድ (1988፣ 138)፣ የይዘት አግባብነት የፈተናው ዋያቄዎች ለመለካት የተፈለጉትን የዶሜን ክፍሎች በመወከል የሚገለፅ ነው ባዩ ሳትርል(1994፣ 65)፣ በክፍል ፈተና (in a class-room test) የይዘት አግባብነት ደረጃ (degree) ለትምህርት የቀረቡት ይዘቶችና (subject-matter content) ባህሪዎች (behaviours) እንዴት ባለ ጥሩ መንገድ ቀርበዋል? ከሚለው ዋያቄ ጋር የተያያዘ

እንደሆነ፤ አንድ ፈተናም ከፍተኛ የይዘት አግባብነት አለው ሊባል የሚችለው ሊመዘኑ የሚገባቸውን ይዘቶችና ባህሪዎች በወካይ ጥያቄዎች፣ ግብሮችን ማቅረብ በመቻሉ እንደሆነ የሚገልፁት ሆንኪንስና እንቴስ (1989፣ 16) እና ሌሎች ተመራማሪዎችም የይዘት አግባብነት በተለይ በፃሎታ መለኪያ ፈተና በጣም አስፈላጊውና ጠቃሚው መሆኑን ይገልፃሉ።

የአንድ ፈተና የይዘት አግባብነት ከፍተኛ መሆን የሚያስገኘው ጥቅም አገላለፁ እንዳንዴ አርቲፅ ይሁን እንጂ ከፍ ብሎ የተወሳ ይመስላል። አስካሁን ከተወሳው አገላለፅ ከምንረዳው በተጨማሪ የይዘት አግባብነት ጠቀሚታዎች በማለት ሂዩዝ(1995) የሚጠቅሷቸው ሁለት መሰረታዊ ነጥቦችም አሉ። አንደኛው የአንድ ፈተና የይዘት አግባብነት ከፍተኛ ሲሆን ለመለካት የታሰበው ጉዳይ በትክክል እንዲለካ ያስችላል የሚል ነው። በሌላ አገላለፅ ዝቅ ብለን በምንወያይበት በልየታው የተለዩት /የተዘረዘሩት/ የክሂል ወይም የፅውቀት ወይም የክሂልና የፅውቀት ክፍሎች በዝቅተኛ ደረጃ የተወከሉ ወይም ሜራሽ ያልተወከሉ (under-represented - or not represented at all) ከሆኑ ትክክለኛ (accurate) መመዘኛ ሊሆን አይችልም ማለት ነው።

ሁለተኛው የጣቅሻ ውጤትን የሚመለከት ነው። የይዘት አግባብነቱ ከፍተኛ ከሆነ ግለትም መመዘን የሚገባቸው ክፍሎች (areas) ሁሉ በወካይ ናሙና ከተሸፈኑ ባክዋሹ አምንታዊ ይሆናል። መመዘን የሚገባቸው ክፍሎች ሁሉ የማይመዘኑ ከሆኑ ብዙ ጊዜ እንደሚስተዋለው ለፈተና የሚቀርቡት ይዘቶች የሚወሰኑት መመዘን የሚገባቸው ስለሆኑ ሳይሆን ለመመዘን ቀላል ስለሆኑ /ስለሚያመቹ/ ከሆነ ባክዋሹ አሉታዊ ይሆናል። እንደሂዩዝ ተጨማሪ ማብራሪያ ከሆነ ደግሞ በፈተና የማይሸፈኑ /የሚዘነጉ/ ክፍሎች በማስተማርና በመማር መዘንጋታቸው አይቀሬ ነው። /'Areas which are not tested are likely to become areas ignored in teaching and learning'/ (ሂዩዝ 1995፣ 23)።

ከቀንዲ ፈተና ተመራማሪዎች ውስጥ አንዱ የሆኑትና አስካሁን ያልተጠቀሱት ዴቢስም እንዲሁ በፃሎታ መለኪያ ፈተና የይዘትና የላህይ አግባብነት ጠቃሚና የግድ መኖር ያለባቸው እንደሆኑ ካመለከቱ ተመራማሪዎች ውስጥ አንዱ ናቸው (ዴቪስ፣ 1988፣ 30)።

ከነዚህና ከሌሎች ወደፊት የሚነሱ ምሁራን አተያዮች አኳያ የአማርኛን የአንብቦ መረዳት ከሂዎች አፈታትን የይዘት አግባብነት ደረጃ መመርመር የዚህ ጥናት አንዱ አላማ ነው።

የይዘትአግባብነት የማጥኛ ስልቶች

የይዘት አግባብነቱ ከፍተኛ የሆነ ፈተና የማዘጋጃና የተዘጋጁ ፈተናዎችን የይዘት አግባብነት ደረጃ የመመርመሪያ /የማጥኛ/ መንገዶች እስከተወሰነ ደረጃ ተመሳሳይ አካሄድን

የሚከተሉ ናቸው። ለምሳሌ በሁለቱም ልየታ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ይህንኑ ማለትም የይዘት አግባብነቱ ከፍ ያለ ፈተና የማዘጋጀትንና የተዘጋጀን ፈተና የይዘት አግባብነት በአዎንታዊነት የሚፈረጅ መሆን አለመሆኑን የማረጋገጫ ስልቶችን በተመለከተ የተለያዩ ተመራማሪዎች በተለያዩ ሰራዎቻቸው ያሉ ቢሆኑም ይኸ ነው የሚባል ጉልህ ልዩነት አይታይባቸውም። በዚህ ጥናት የተጠቀሱት ተመራማሪዎች ሁሉ ማለት ይቻላል የሚሉት የፈተናን የይዘት አግባብነት ሲያዘጋጁ ከፍ ለማድረግ፣ የተዘጋጀውን ለመገምገም /ለማጥናት/ የመጀመሪያውና ቁልፉ ልየታ ነው። የዶሚን ልየታ፣ የክሂል ልየታ፣ የግብር ልየታ ... ነው።

ይህን መሰረታዊ መርህ ከሚያራምዱት ተመራማሪዎች ውስጥ በሌሎች የፅሁፋት መስኮች ሀርሊን (1994)፣ ግሩላንድና ሮቨርት (1990)፣ ሆንኪንስና አንቴስ (1989)፣ ግሩላንድ (1988) በቋንቋ አልደርሰን ክላፓምና ፆል(1995)፣ ባችማን (1995)፣ ሂዩዝ (1995)፣ ክላፓም (1997)፣ ዌየር (1993፣ 1990፣ 1988)፣ ዴቪስ (1988) ይገኙበታል።

ቨርጎ ከፍ ብሎ በቀዳሚው ክፍል ለመጠቆም እንደተሞከረው ዝርዝር ውስጥ ሲገባ የቋንቋ ፈተና ለማዘጋጀት ወይም የተዘጋጀውን ለመመርመር /ለመገምገም/ የሚያስፈልግ ልየታና የሌላ ትምህርት አይነት ለምሳሌ የጅኦግራፊ ፈተና ለማዘጋጀት (ለመመርመር) የሚደረግ ልየታ መቶ በመቶ የሚመሳሰል እይደለም ልዩነት አለው።

በአብዛኛው መልኩ ለቋንቋም ሊያገለግል ቢችልም በሌላ የትምህርት መስኮች የሚካሄደው ጥናት "ኤክስፔክታንሲ" ሰንጠረዥ (expectancy table) የሚባለውን በመጠቀም ባንዱ አቅጣጫ የሚጠበቀውን ባህሪ (ዓላማ)፣ በሌላኛው የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥለማስገኘት የተመረጡትን የትምህርት ይዘቶች በመለየት (በመዘርዘር)ና ውክልናቸውን በመቶኛ በመግለፅና ይህንኑ በመተንተን ነው። በትምራም በተግባራዊ ጥናቶችም የተደገፈ የይዘት አግባብነት ከፍ ግድረጊያ ወይም ማጥኛ ስልት ነው።

በእኛ ሀገር የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ በመጠቀም አንድ፣ በቀጥታ በትወራ የተነደፈውን ሰንጠረዥ ሁለት ክፍል በመጠቀም አይነት አንድ ጥናት በሳይኮሎጂ ትምህርት ክፍል ተካሂደዋል። የመጀመሪያው ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ በ12ኛ ክፍል የታሪክ ፈተና የይዘት አግባብነት ላይ ሁለተኛው ለሁለተኛ ዲግሪ በሣይንስ ትምህርት የስድስተኛ ክፍል ፈተና ላይ የተካሄዱ ናቸው። ሁለቱም የተጠቀሙባቸው የባህሪ ዶሚን ክፍሎች በነብሎም (1956) የቀረቡትን ነው። ሁለተኛው አጥኝ እንደተባለው ከባህሪዎች በተጨማሪ ከመርህ ትምህርቱ ይዘቶች አኳያም የይዘት አግባብነቱን ደረጃ ለመመርመር ሞክረዋል።

በቋንቋ ፈተናዎች የይዘት አግባብነትን ለማጥናት የተለያዩ ተመራማሪዎች የሚቀበሉትና ተቸኒት ያለው መሆኑን ላይገልፁት የማያልፉት በባችማን (1990) ስራ የተነደፈውን ባለሁለት

ገፅታ ልየታ ነው። ተግባቦታዊ የቋንቋ ችሎታና የፈተና ዘዴዎች በማለት የገለጿቸውን። እያንዳንዳቸው ባለብዙ ፈርጆች ሲሆኑ ዋና መለያቸው ግን፣ የመጀመሪያው በቋንቋ ፈተና የሚፈተነው ችሎታ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ችሎታዎች (abilities) የቀረቡበት ነው። ሁለተኛው የቋንቋ ፈተና እንዴት መቅረብ እንዳለበት መንገዶችን የሚያሳይ ልየታ ነው። ከነዚህ ውስጥ ለእንብቦ መረዳት ከሂሎች አፈታተን የሚሆኑም የማይሆኑም አሉ። የሚሆኑት ለዚህ ጥናትም እጋዥ ይሆናሉ።

ብዙዎቹ ትምራዊ ይሁኑ እንጂ በተለይ የእንብቦ መረዳት ክሂሎች ፈተናዎችን ለማዘጋጀትም ሆነ ለመመርመር የሚያስችሉ በተለያዩ ተመራማሪዎች የቀረቡ የተለያዩ ልየታዎችም አሉ። በስፋት በሌላ ክፍል የሚቀርብ ቢሆንም በሂዩዝ (1995)፣ ዌየር(1997፣ 1993፣ 1990፣ 1988)፣ አልደርሰንና ላክሚኒ (1989) የቀረቡት ልየታዎች ለተነሳው ሀሳብ ምላሽ ሊሆኑ ይችላሉ።

በሂዩዝ (1995) የእንብቦ መረዳት ክሂሎች ፈተና ልየታ መሰረት ለምሳሌ ልየታው ከሚያቀፋቸው ክፍሎች ይዘት ልየታ የመጀመሪያው ነው። በይዘት ልየታ ስር ከሚካተቱት ውስጥም የክሂሎች ልየታ ቀዳሚው ነው። በሳቸው ልየታ መሰረት አራት ዋና ዋና ክሂሎች (Macro-skills)ና አምስት ንዑሳን ክሂሎች (Micro-skills) ተዘርዝረዋል። ቀጣዩ የይዘት ልየታ ክፍል የምንባብ አይነቶች /types of text/ ልየታ ነው። በዚህ ልየታ ስር ምንባቦች ከመማሪያ መፅሐፍ፣ ከልቦለድ (novel) ከመፅሔት፣ ከጋዜጦች፣ ከ'አካዳሚክ ጆርናል' ፣ ከግጥም ... ለመረጡ ይችላሉ።

በዌየር የተለያዩ ስራዎችና በሌሎችም የምናገኘው የእንብቦ መረዳት ክሂሎች ፈተና ለማዘጋጀትም ሆነ ለመመርመር (የይዘት አግባብነቱን) የሚያገለግለው ልየታ እንዲሁ እንደሂዩዝ (1995) ከምንባቦች አመራረጥና ከሊፈተኑ ከሚገባቸው ክሂሎች ላይ ያተኮረ ነው። ክሂሎችንም ሆነ ምንባቦቹን በሚመለከት ወደኋላ ስለምንመለስበት ወደጀመርንው አጠቃላይ ጉዳይ እንመለስ።

በዚህ በልየታ ሂደት ሁለት ሁናቴዎች መኖራቸውን የሚያመለክቱ የፈተና ተመራማሪዎች አሉ። ለውጭ (External) ፈተና የሚደረግና ለውስጥ (internal) ፈተና የሚደረግ ልየታ የሚባሉ። የውጭ የሚባለው በቀጥታ ትምህርቱን በሚሰጡት (በመምህራን) ላይሆን በሌላ (በውጭ ሀይል) የሚዘጋጅን የሚመለከት ነው። የውስጥ የሚባለው ደግሞ በቀጥታ ትምህርቱን በሚሰጡት መምህራን በዚያው በትምህርትቤቱ ደረጃ የሚዘጋጅን የሚመለከት ነው። በሁለቱም መልክ የተዘጋጀን ፈተና ራሳቸው አዘጋጅቱ ያወጡትን ወይም ሌላ በማዘጋጀት ወይም በሌላ የተዘጋጀን ልየታ (ቾክሊስት) በመጠቀም የይዘት አግባብነት ደረጃውን መመርመር እንደሚቻል ትምራዎችም ተግባራዊ ስራዎችም የሚያመለክቱት ጉዳይ ነው።

በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ግን በእኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ሲታይ ብሔራዊ ፈተናዎች የውጭ ፈተና፣ በየመንፈቀ ዓመቱ መጨረሻ የሚሰጡት የክፍል ፈተናዎች የውስጥ ለሚባለው ምሣሌ ሊሆኑን ይችላሉ።

የልየታ አዘገጃጀት ሁለት መልክ እንዳለው የሚገልፁት ራሳቸው ስለአያንዳንዱ ከሚገልፁት መረዳት እንደሚቻለው በሁለቱ መካከል የሚኖረው ልየታ ልዩነት በጣም ጠባብ መሆኑን ነው። ይኸውም በግዕከል (በውጭ) የሚዘጋጀው በስርአተ ትምህርቱ፣ በመርሀ ትምህርቶቹ፣ በመግሪያ ግዕሐፎቹና በሌሎች መሳሪያዎች ላይ የሚመሰረትና አጠቃላይነት የሚንፀባረቅበት ሲሆን በመምህራን በትምህርት ቤት ደረጃ የሚዘጋጀው ከነዚህ ከተዘረዘሩት መሳሪያዎች በተጨማሪ የዕለት ተለት የክፍል ውስጥ ትምህርት ዝርዝር አላማዎችን፣ ከንውኖችን ... ሊያካትት ስለሚችል ይበልጥ ዘርዘርና ሰፋ ያሉ ባህሪዎችን (ዓላማዎችን)ና ዶዘቶችን የሚዳስስ ይሆናል።

በሁለቱም የልየታ አስፈላጊነት ከፍተኛ መሆን ሊላውና ይበልጥ አንድ የሚያደርጋቸው ነው። የፈተናዎች አዘገጃጀት ሁለት መልክ ያለው መሆኑን የሚያስረዱት ራሳቸው በሁለቱም፣ የአዘገጃጀት ሂደትም ሆነ የተዘጋጀውን በመመርመር የልየታን መሰረታዊነት አጠንክረው ነው የሚገልፁት። የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች ዕምነትም ይኸው ነው የሚመስለው። ለምሳሌ ዌየር (1990፣ 26) ፈተናን ሊፈተኑ በሚገባቸው የተወሰኑ ክሂሎች (specific enabling skills) ላይ መመሰረቱ ቁልፍ (crucial) ጉዳይ እንደሆነ ከመግለፃቸው በተጨማሪ በ(1993) ስራቸው ውስጥ ከራሳቸው ምንባብና የክሂል አይነቶች ልየታ ዝርዘራ በፊት አንተ በምትጠቀምበት ውስጥ ያሉትን በቅድሚያ ዘርዝራቸው.. እያሉ በሳቸውና በአንባቢው ልየታ መካከል የሚኖረውን ልዩነት እንዲያንፀባርቅ መጋበዛቸው በሁሉም አቅጣጫ የልየታን መሰረታዊነት የሚያሳይ ይመስለናል።

የዶዘት አግባብነትን ለመመርመር /ለመገምገም/ የሚረዱ ሦስት ያጠናን ስልቶች (Procedures for Evaluation) መኖራቸውን አልደርሰን፣ ክላፓምና ዎል(1995፣ 193) ያመለክታሉ። እንደኖው የፈተናውን ይዘት ከልየታዎች (ከመርሀ ትምህርቱ) ጋር በማነፃፀር ስልት ነው (compare test content with specifications/syllabus) ሁለተኛው መጠይቆችን፣ ቃለመጠይቆቹን በማዘጋጀት ባለሙያዎች (experts) ማለትም መምህራን፣ በትምህርቱ የላቀ ዕውቃ ያላቸው የመስኩ ምሁራን፣ የተግባራዊ ስነልሣን ሊቃውንት መጠይቆቹን እንዲሞሉ፣ ለቃለመጠይቆቹ ምላሽ እንዲሰጡ በማድረግ ነው (questionnaires to, interviews with 'experts' such as teachers, subject specialists, applied linguists.) ሦስተኛው በፈተናው ጥያቄዎችና ፅሑፎች (texts) ላይ የባለሙያዎችን ዳኝነት (ፍርድ) (Expert judgment) መጠቀም ተደጋፊነት ያለውና በተግባርም እየተሰራበት ያለ ዋነኛ ስልት ነው። በአብዛኛው የሚሰራበት

የአተገባበር ሂደትም መመዘን የሚገባቸውን የክሂልና /የዕውቀት/ ዝርዝሮች ጋር እንዲጣጣሙ ወይም እያንዳንዱ ጥያቄ የትኛውን ክሂል /ዕውቀት/ እንደሚመዝን እንዲገልፁ በማድረግ ነው። ከትምራ አንዣርም በብዙ ተመራማሪዎች ድጋፍ ያለው የይዘት አግባብነት መመርመሪያ መንገድ ነው። ለምሳሌ አልዶርሰን፣ ክላፓምና ዎል (1995፣ 173) የይዘት አግባብነት ጥናት በቀናነት የባለሙያዎችን ስርአታዊ መንገድ የተከተለ ዳኝነት ያቀፈ እንደሆነ፤ ከዚህ ከባለሙያዎች የዳኝነት መንገዶች ውስጥም የተለመደው የፈተናውን ይዘት ሙተንተንና የተተነተውን የፈተና ይዘት መሆን ካለበት የይዘት ዝርዝር ጋር ማነፃፀር እንደሆነ፣ ('A common way is for them to analyse the content of a test and to compare it with a statement of what the content ought to be') ከገለፁ በኋላ ይህም የይዘት ዝርዝር ለመፈተን የተዘጋጀው ልየታ (the test's specifications) ወይም መደበኛው የማስተማሪያ መርሀ ትምርት ወይም ስርአተ ትምህርት፣ ('it may be a formal teaching syllabus or curriculum') ወይም የጾሚን ልየታ (it may be a domain specification) ሊሆን እንደሚችል ይገልፃሉ።

የእንብቦ መረዳት ክሂሎች ፈተናዎችን የይዘት አግባብነት የማጥኛ (የመገምገሚያ) ስልቶችም ከላይ ከቀረቡት መንገዶች ጋር የሚመሳሰል ነው። ከተለያዩ በእንብቦ መረዳት ክሂሎች አፈታተን ዙሪያ የቀረቡ ትምራዎችና ተግባራዊ የምርምር ስራዎች እንደምንረዳው የእንብቦ መረዳት ክሂሎችን ፈተና የይዘት አግባብነት የመመርመሪያ (የማጥኛ) መንገዶችን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ የሚችሉ ይመስለናል። እንደኛው በአልዶርሰን፣ ክላፓምና ሮል(1995) ስራ ተጠቅሶ የምናገኘው ክላፓም (1992) የባችማን(1990)ን የፈተና ዘዴዎች ገፅታዎች (Test Methods Characterstics) ' ስኬል' ለእንብቦ መረዳት ክሂሎች ፈተና ምርመራ እንዲስማማ በማድረግ ሦስት የእንግሊዝኛ ለተለየ ዓላማ (EAP) መምህራንን የሦስት እንብቦ መረዳት ክሂል ፈተናዎችን ይዘት ጥያቄዎቹንና ምንባቦቹን (items and reading passages) ደረጃ (rate) በተሰጣቸው እስኬል መሰረት እንዲገልፁ በማድረግ የተጠቀመበት መንገድ ነው።

ሁለተኛው (የእንድን እንብቦ የመረዳት ክሂሎች ፈተና የይዘት አግባብነት ለማጥናት የሚሰራበት ስልት) አልደርሰንና ላክሚኒ (1989) በተግባር ሞክረው ያወጡት ነው። የጥናቱ አካሄድ እንደ ክሊፓም (1992) የባለሙያዎችን ዳኝነት የሚጠቀም ቢሆንም የሚለይበትም አለው። ይኸውም በዚህኛው በእንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ሊመዘኑ የሚገባቸው ክሂሎች ዝርዝር /ፕሮሲስት/ ይዘጋጅና ለባለሙያዎቹ ከሚጠናው ፈተና (ፈተናዎች) ጋር ይሰጣል፤ ባለሙያዎቹም በሚሰጣቸው መመሪያ መሰረት እያንዳንዱ ጥያቄ የትኛውን ክሂል እንደሚመዝን ያመለክታሉ፤ አጥኝውም ከባለሙያዎቹ ያገኘውን መረጃ በመተንተን የይዘት አግባብነቱን ደረጃ ይገልፃል ማለት ነው።

ክሊፓም (1997) እንደሚሉት አንድ ጥያቄ የትኛውን ክሂል እንደሚመዝን በባለሙያዎች መካከል ስምምነት ካልተፈጠረ ጥያቄው ችግር ያለበት ነው ማለት ነው። እንዲህ ያለው ጥያቄ

ዝቅተኛ የይዘት አግባብነት (low content validity) ያለው ነው የሚሉት እነ አልደርሰን (1995) ደግሞ እንዲህ ያለ (በባለሙያዎች መካከል ያለመግባባት) አጋጣሚ ከተፈጠረ ባለሙያዎቹ በአስተያየቶቻቸው ላይ እንዲወያዩ በማድረግ የልዩነታቸውን ስፋት ለማጥበብ /ለማስወገድ/ እንደሚቻል መላ ያመላክታሉ (አልደርሰን፣ ክላፓምና ቻል፣ 1995፣ 176)።

ከነአልዶርሰን (1989) በኋላ የነሱን መንገድ በመከተል የራሳቸውን 'ቸክሊስት' በማውጣት ለምሌ (1993) በዚሁ በአንብቦ መረዳት ክሂሎች ፈተና ላይ የባለሙያዎችን ዳኝነት ተጠቅሙዉ አንድ ጥናት አካሂደዋል።

ይህ ጥናትም የሞዴል ፈተናዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ፈተና የይዘት አግባብነት ለመመርመር የሚከረው ሁለተኛውን መንገድ (የነአልደርሰን፣ 1989)ን በመከተል ይሆናል።

2.6.2 የላሀይ አግባብነት/Face Validity/

ብዙዎቹ ተመራማሪዎች እንደሚገልፁት የላሀይ አግባብነት አንድ ፈተና በላዕላይ /surface/ ገፅታው የሚኖረውን ተቀባይነት የሚመለከት ነው። ሂዩዝ (1995፣ 27) ለምሳሌ አንድ ፈተና የላሀይ አግባብነት አለው የሚባለው እንዲመዝን የተፈለገውን የሚመዝን መስሎ ከታየ ነው፤ ካሉ በኋላ ለምሳሌ የንበትን ችሎታ ለመፈተን የታቀደ ፈተና ተፈታኙ እንዲናገር ፅሁል የማይሰጥ ከሆነ የላሀይ አግባብነት ሊታጣ እንደሚችል በማለፅ ያስረዳሉ።

የላሀይ አግባብነት የአንድን ፈተና የላዕላይ ተአማኒነት /surface credibility/ ወይም የህዝብ ተቀባይነት /public acceptablity/ የሚመለከት እንደሆነ ኢንግራም (1977፣ 18)ን ጠቅሰው የሚያስረዱት አልደርሰን፣ ክላፓምና ቻል (1995፣ 172) ይህ በላዕላይ ገፅታው ሲታይ ተገቢ ፈተና የመምሰሉ ጉዳይ ለግንኙውም (ባለሙያ ለሆነ) ሰው ሁሉ ሳይሆን ለተወሰኑ ክፍሎች እንደሆነ ያብራራሉ እነዚህ ክፍሎች ወይም ሰዎችም ' ተራ' ሰዎች /Lay people/ የሚባሉት ሲሆኑ በዝርዝር የሚጠቀሱት አስተዳዳሪዎች፣ ባለሙያ ያልሆኑ ተጠቃሚዎችና /non-expert users/ ተማሪዎች ናቸው። አገላለፃቸው ይለያይ እንጂ ሌሎች ተመራማሪዎችም ከዚህ የተለየ አተያይ የላቸውም። በርግጥ በአብዛኛው ወደተማሪዎች አስተያየት (ፍርድ) የማተኮር ዝንባሌ የሚታይ ይመስላል። ምክንያቱም በብዙዎቹ አገላለፅ በተለይ በተግባቦታዊ የቋንቋ ፈተና አቀንቃኝ ምሁራን የፈተናው በተማሪዎች ተገቢ መስሎ የመታየት አስፈላጊነት ትኩረት ሊያገኝ የሚገባው እንደሆነ ነው የሚወሳው። ተገቢ መስሎ ሊታይ የሚችለው ደግሞ ትክክለኛ /authentic/ (የገሀዱ ዓለም የቋንቋ አጠቃቀም) ንፀብራት አይነት ሆኖ ሲዘጋጅ እንደሆነ ያስረዳሉ።

ከላይ የተጠቀሱት ተመራማሪዎች እንደሚያስገነዝቡት ምንም እንኳ ደካማ በሆኑ ጥያቄዎች፤ ግልፅ ባልሆኑ ትዕዛዞች /መመሪያዎች/ /instruction/ ወይም ተገቢ ባልሆነ የጊዜ መጠን ላይ የተለየ ትኩረት የሚደረግ ቢሆንም የሚሰጠው አስተያየት /ፍርድ/ በፈተናው አጠቃላይ /holistic/ ገፅታ ላይ ነው የሚሆነው።

የላሀይ አግባብነት በተግባቦታዊ የቋንቋ ፈተና አቀንቃኞች ዘንድ ከፍ ያለ ቦታ የተሰጠው እንደሆነ እነ አልደርሰን (1995) ሲገልፁ፤ ባችማን (1995) ደግሞ የላሀይ አግባብነት የተለያየ ትርጉሜ በተለያየ ጊዜ የተሰጠው ቃል ቢሆንም ረጅም ዕድሜ ያለው እንደሆነ ያወሳሉ። እንደላቸው አገላለፅ ከላቸው የ1990 ስራ አርባ ዓመት በፊት ምስር (1947)፤ ሃያ ዓመት በፊት ካቴል (1964)፤ በቅርቡም ዴቪስ (1977)፤ ክሮንባክ (1984)፤ የአሜሪካ የሳይኮሎጂ ማህበር (1974፤ 1985) ያንኑት (አንስተው የተወያዩበት) አሳቢ ነው የላሀይ አግባብነት።

ብዙዎቹ ተመራማሪዎች ደጋግመው እንደሚያወሱት የላሀይ አግባብነት ሳይንሳዊ ዕሳቤ /Scientific concept/ እይደለም። ነገር ግን በዊየር (1990) የተወሱት ላዶ (1961)፤ ዴቪስ (1965)፤ ኢንግራም(1977)፤ ፓልመር (1981) ና ባችማንና ፓልመር (1981)ዘቅ ያለ ዋጋ /ዋጭ/ /value/ ቢሉኩትም ከፍ ብሎ ለመግለፅ እንደተሞከረው አብዛኞቹ የዘመናችን የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች ለምሳሌ አልደርሰን፤ ክላፓምና ፓል(1995)፤ ሂዩዝ (1995)፤ ዊየር (1990)፤ ዴቪስ (1988)፤ ከሌላ መስክም አንስታዚ (1982) በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ የአግባብነት አይነት መሆኑን ነው አፅንኦት ሰጥተው የሚያስገነዝቡት። በተለይ ከተማሪው አኳያ አስፈላጊነቱ የጎላ እንደሆነ ነው የሚገለፀው። ምሁራኑ እንደሚሉት ተማሪዎች የሚፈተኑት ፈተና የላሀይ አግባብነት ያለው መሰሉ ካልታያቸው መሰረት የሚገባቸውን በሚገባ እንዳያሳዩ መሰናክል ሊሆንባቸው እንደሚችል ነው። ለአብነት ያህል በዊየር (1990፤ 26) የተጠቀሱት አንስታዚ (1982፤ 136) የፈተና ይዘት ተገቢነት የሌለው፤ የማይመጥን፤ የማይረባ፤ ወይም የልጅ ስራ /ፍሬቪስ/ መሰሉ ከታያቸው ውጤቱ ደካማ፤ ትክክለኛ የፈተና አግባብነት የማይንፀባረቅበት ሊሆን እንደሚችል ሲያስገነዝቡ፤ እነ አልደርሰንም ተፈታኞች የሚፈተኑት ፈተና የላሀይ ተገቢነት ያለው እንደሆነ እድርገው ከተገነዘቡት በተቻላቸው መጠን፤ ያላቸውን ችሎታ ሁሉ ተጠቅመው ለመስራት እንደሚጥሩና ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ እንደሚሞክሩ፤ ይህም የላሀይ አግባብነት በምላሽ አግባብነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑን እንደሚያሳይ ያስረዳሉ (አልደርሰን፤ ክላፓምናምል 1955፤ 27)።

የአንድን ፈተና የላሀይ አግባብነት ለማጥናት ጠንክሮ ያሉ ችግሮች እንዳሉ የሚገልፁት ባችማን (1995) በተለይ የሚመለከታቸው ክፍሎች ናቸው ተብለው የተዘረዘሩት አካላት ስለአንድ ፈተና ያላቸውን አስተያየት፤ ስሜት _ ለመመርመር በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ነው ለማመልከት የሚሞክሩት። ይኸውም በባለሙያዎች /experts/ መካከል እንኳ ያለመግባባት

የሚፈጠር መሆኑን እየገለፅን፤ ባለሙያ ባልሆኑ /በ 'ተራ' ሰዎች/ መካከል ደግሞ ይህ ያለመግባባት ሁኔቴ የባሰ መሆኑ ግልፅ ሆኖ እያለ ይህን የተለያየ አስተያየት እንዴት ማጥናት ይቻላል? ወይስ የየትኛውን አስተያየት መቀበል ይቻላል? የሚለውን ለመመለስ ስለማይቻል አስቸጋሪ ነው ባይ ናቸው። በተለይ የብዙ ሰዎችን አስተያየት ተቀብለን የምንወስን ከሆነ አስቸጋሪነቱ ከፍ ያለ እንደሚሆንም ያወሳሉ።

ትግሩ መኖሩን ባያስተባብሉም ሌሎቹ ግን ከዚህ የተለየ አቋም ያላቸው ነው የሚመስለው። ለምሳሌ አልደርሰን፤ ኩሊፓምናዎል (1995፤ 173) የላህይ አግባብነትን ማጥናት እንደሚቻል፤ መረጃም ተግሪዎች ስለተፈተኑት ወይም ስለተመለከቱት /looked at/ ፈተና ያላቸውን አመለካከት /attitude/ ፣ አፀፋና /reaction/ ስሜቶች /feelings/ ለቃለ መጠይቅ መልስ እንዲሰጡ፤ መጠይቅ እንዲሞሉ በማድረግ መሰብሰብ እንደሚቻል፤ የተሰበሰበውን መረጃም በመጠናዊ /statistically/ ወይም በሌላ መንገድ መተንተን እንደሚቻል፤ በትንተናውም የላህይ አግባብነት ደረጃው ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚቻል ያስረዳሉ።

ይህ ጥናትም የሞዴል ፈተናዎቹን የአንብቦ መረዳት ክሂሎች የላህይ አግባብነት ለመመርመር በነዚህ ተመራማሪዎች ከተጠቆሙት ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱን (መጠይቅን) በቀናነት በመጠቀምና የተገኘውን መረጃ በመተንተን የሚካሄድ ይሆናል።

2.7 አንብቦ መረዳትን መፈተን

ከብዙዎቹ ተመራማሪዎች የአንብቦ መረዳት ፈተና ነክ ጥናቶች ትኩረቶች በመነሳት በዚህ ርዕስ ላይ የሚነሱ ዋና ዋና ጉዳዮችን በሁለት ከፍሎ ማየት የሚቻል ይመስለናል። አንደኛው በአንብቦ መረዳት ፈተና ምንድነው የሚመዘነው? የሚለውን ይበልጥ የሚመለከት ሲሆን ሌላኛው የሚመዘነው /የሚጠየቀው/ ጉዳይ እንዴት ይቅረብ? በሚለው፤ በዘዴ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው።

በዚህ ክፍል፤ ሁለቱን ጉዳዮች፤ ተራ በተራ፤ የመጀመሪያውን፤ በአንብቦ መረዳት ፈተና የሚመዘነው ችሎታ(ክሂል) ምንድነው? ሁለተኛውን፤ የአንብቦ መረዳትን ለመፈተን ይበልጥ ተስማሚነት ያላቸው የምንባባት አመራረጥና ያጠያየቅ ዘዴዎች የትኞቹ ናቸው? ከሚሉት ንፅፅሮች አኳያ ለመመልከት ነው የሚሞከረው።

2.7.1 በእንብቦ መረዳት ፈተና ጥያቄዎች ሊመዘኑ የሚችሉ ክሂሎች

ቀደም ብሎ የደዘት እግባብነት በሚለው ክፍል በስፋት እንደተገለፀው በቋንቋም ሆነ በሌሎች የትምህርት መስኮች የፅሁፍቶችና የክሂል ዘርፎች ፈተና ለማዘጋጀት ወይም የተዘጋጁ ፈተናዎችን ብቃት /ተገቢነት/ ለመመርመር በፅሁፍቶችና/በክሂል ዘርፎች ውስጥ የሚገኙ ንዑሳን የፅሁፍቶችና/ የክሂል ክፍሎች የሚያሳይ ልየታ ቀዳሚውና መሰረታዊ የሆነው ጉዳይ ነው። የእንብቦ መረዳት ፈተና አዘገጃጀትም ሆነ አገማገም ከዚህ ፅሁነታ ውጭ ሊሆን አይችልም። አይደለምም። ምክንያቱም ባጠቃላይ መልኩ ሲታይ አንብቦ የመረዳት ክሂል ያላል እንጂ ዝርዝር ውስጥ ሲገባ የተለያዩ ንዑሳን ክሂሎችን በውስጡ የያዘ ዘርፈ ብዙ የሆነ ክሂል ስለሆነ እያንዳንዱ ንዑስ ክሂል በተገቢ ናሙና ሊወከል የሚችለው በቅድሚያ ክ ሂሉ ተለይቶ ሲታወቅ ነው። ቀጥሎ የሚቀርቡት የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ልየታዎችም ይህንኑ የሚያስገነዝቡ ይመስሉናል።

ከዚህ ጥቅል አስተያየት በመነሳት በቀጥታ በእንብቦ መረዳት ፈተና ጥያቄዎች የሚመዘነው ምንድነው? ተፈታኞቹ ምን ባህሪ (ችሎታና/ፅሁፍቶች) ማዳበራቸውን ለመለየት ነው ፈተናው የሚሰጠው? ምን አይነት የባህሪ ፣ የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ መገኘቱን ለማረጋገጥ ነው የሚፈለገው? የሚሉትን፣ የምናተኩርበት ነው የተባለውን የእንብቦ መረዳት ባህሪ/ፅሁፍ ጠቃቂ ጥያቄዎች መልስ ፍለጋ ስናመራ ሂዩዝ (1995) ከእንብቦ መረዳት ፍላጎት ወይም ኮርስ አላማዎች (directly related either to needs or to course objectives) ጋር የተያያዙ እንደሆኑ፣ በመግለፅ ሌሎች በተለያየ ወቅት የራሳቸውን ሰያሚ በመስጠት ወደጠረጴዛቸው በእንብቦ መረዳት ፈተና ሊመዘኑ የሚችሉ ንዑሳን ክሂሎች እነማንነት ልየታ ዝርዝር ጥናት ቅኝት እንድናመራ ይመሩናል።

እንደተባለው ከምሁራኑ ዝርዝር ልየታና ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው ይህ የክሂል አይነት ባጠቃላይ መልኩ ሲታይ አንብቦ የመረዳት ክሂል እየተባለ ይጠራ እንጂ ዝርዝር ውስጥ ተንብቶ ሲመረመርና ለትምህርት ሲቀርብ በውስጡ ብዙ ንዑሳን ክሂሎችን የያዘ ነው።

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ንዑሳን የእንብቦ መረዳት ክሂሎችን እነማንነት ዝርዝራ ጅማሬ ቀደም ያለ ነው። ከነ ብሎም (1956) የትምህርት አላማዎች ክፍፍል (taxonomy) በፊት የተጀመረ ተግባር ነው።

ከነዚህ ቀደም ያሉ እንብቦ የመረዳት ክሂሎች ዝርዝሮች /ልየታዎች/ ውስጥ ለምሌይ (1993)፣ አልፎርስንና ላክሚኒ (1989)፣ ደጀኔ (1994) የጠቀሏቸው በነ ሉንዘርና ጋርድነር (1979) ስራ ውስጥ የተጠቀሱት የኒውዎርክ ከተማ፣ ትምህርት ቦርድ ለይቶ የዘረዘራቸው 36 ክሂሎች፣ ዲቪስ (1944) ያመለከቷቸው ዘጠኝ የተለያዩ እንብቦ የመረዳት ክሂሎች፣ ይገኙበታል።

ስለዚሁ ጉዳይ ግሪሌትና ስዋን (1991፣ 3) ሲገልፁ፡- ማንም ቢሆን በአፍ መፍቻው ቋንቋ ቢሆንም እንኳ በእግባቡ /effectively/ የሚያነብ የለም። ይኸ አንብቦ የመረዳት ችግር የሚፈጠረው ደግሞ በትንሽ ምክንያት ሊሆን ይችላል ። የቃልን ትርጉም ባለማወቅ፣ ነገር ግን ያንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የንዑሳን አንብቦ የመረዳት ክሂል ችግር ካለበት ደግሞ ችግሩ የከፋ ይሆናል፤ በግለት ካስገነዘቡ በኋላ ለዚህ ችግር ማስወገጃ መፍትሄ የሚሆነው፣ ለየንዑሳን ክሂሎች ማስተግሪያ የሚያገለግሉ መልመጃዎችና ምንባቦች በማዘጋጀት ለማስተማሩ አስፈላጊነት ከብደት የሚሰጠው ሊሆን እንደሆነ አድርገው ያወሳሉ።

በፈተናውም /በአንብቦ መረዳት/ ለትምህርት አስፈላጊ ናቸው ተብለው የቀረቡት ወይም የሚቀርቡት ንዑሳን ክሂሎች በዝርዝር መጠየቅና ተማሪው በትክክል ክሂሎቹን ያዳበረ መሆን አለመሆኑ መለየት እንዳለበት የቅርቦቹ ሊቃውንት ሂዩዝ (1995)፣ ዌየር (1988፣ 1990፣ 1993)፣ ጊተን (1990፣ 1991)፣ አልደርሰንና ለክሚኒ (1989) እና ሌሎችም ያመለክታሉ።

ይህን ሀሳብ በተመለከተ ለምሌይ (1995፣ 129)፣ ዌየር (1994፣ 8) ንባብን ባላንድ አቅጣጫ አድርገን ለማየት የምንሞክር ከሆነ እንዴት መፈተን እንደምንችል፣ ምን አይነት ፅሑፎችን እንደምንጠቀም፣ ወይም የትኞቹን ክሂሎች ለመመርመር /ለመመዘን/ እንደምንሞክር አያሳስበንም ማለት ነው((weir 1994፣ 8) warns us against : 'If reading is unidimensional, it should not really matter how we test it, what texts we use or what operations we try to assess.') በማለት በንዑሳን ክሂሎች አከፋፈል ጉዳይ የሚከራከሩ ተመራማሪዎችን ፣ እላቸውን (ለምሌይን)ና ሌሎችን የመከሩበትን ዐረፍተ ነገር በመዋቀስ የክርክሩን መኖር ባይጠሉትም በዌየር ሀሳብ የሚስማሙ መሆናቸውን ይገልፃሉ።

በተግባቦታዊ የቋንቋ ፈተና ውልደትና ፅድገት ሂደት እንዲህ የንባብ ንዑሳን ክሂሎች ተለይተው በፈተና በመቅረባቸው ጉዳይ ላይ በተመራማሪዎቹ መሀል ይኸ ነው የሚባል ልዩነት ያለ ባይመስልም አንድ ወጥ የክሂሎች ክፍፍል በማውጣቱ በኩል ግን የሚስማሙ አይደሉም። ያለመስማማታቸው አንዱ ምክንያት የተለመደውና ጠናማ የሆነው በምሁራን መካከል የሚኖረው የሀሳብ ልዩነት ያመጣው ይመስላል።

ሊላው በክሂሎች ዝርዝር አውጭ ምሁራን መካከል የዝርዝሮቹ መውጣት አላማ መለያየት የሚያመጣው ልዩነት ነው። የቀለም ትምህርት ለመማር አላማ የሚያስፈልጉ የንባብ ክሂሎችና ለተግባቦት አላማ የሚያስፈልጉት የንባብ ክሂሎች አንድ ያለመሆን የሚያመጣው ልዩነት አይነት ማለት ነው።

ለምሌይ (1993) እንደሚሉት ደግሞ ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ በተወሰኑ ንዑሳን ክሂሎች መካከል ለምሳሌ ትንተና /analysis/፣ ግንባታ /synthesis/ና ግምገማ /evaluation/ በሚሉት አይነት ያሉ ልዩነቶችን መግለፅ አስቸጋሪ መሆን ያመጣው ችግርም ይገኝበታል።

ከነዚህ በተለያዩ ጊዜያት፣ በተለያዩ ተመራማሪዎች ከወጡ ንዑሳን የንባብ ክሂሎች መካከል በመንቪዶ (1978) ስራ ከተገለፁት 54 የቋንቋ ክሂል ክፍፍሎች /taxonomy/ ውስዋ 19 የንባብ ንዑሳን ክሂሎች ዝርዝር በኋላ ላንዘር፣ ዌይትና ዶላን (1979)፣ እንግሊዝኛ ያፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ማውጫ የሚያገለግሉ 8 ንዑሳን ክሂሎችን ለመለየት ያደረጉት ሙከራ አንዱ ነው።

እነዚህ ሊፈተኑ የሚገባቸው ክሂሎች ተብለው የተዘረዘሩትና በኦልያርሰንና ላክማኒ (1989፣ 259) ተጠቅሰው የምናገኛቸው፡- የቃል ትርጉም /word meaning/፣ ቃላት በአውድ ውስጥ /words in context/፣ ቃል በቃል የመረዳት ችሎታ (literal comprehension)፣ ካንድ ክፍል በሙነላት ግጠቃለያዎችን (እንፈረንሶች) ማውጣት /መስጠት/፤ /Drawing inferences from single strings /sentences/፣ ከተለያዩ ክፍሎች (ዐረፍተ ነገሮች) በመነሳት ግጠቃለያዎችንና መደምደሚያዎችን ማውጣት (Drawing inferences from multiple strings (sentences)፣ ዘይቤን ሙተርንም /Interpretation of metaphor/፣ ጎላ ጎላ ብለው የሚታዩትን ወይም ዋና ሀሳቦችን መፈለግ /Finding salients or main ideas/፣ አስተያየቶችን መስጠትና /Forming judgments/፣ የሚሉት ናቸው።

አዳም ስሚዝ (1981) ደግሞ የብሉሚያንን ክፍፍል /taxonomies/፣ መሰረት በማድረግ በንባብ ክሂል ግስተግርና መፈተን ሂደት ለማዋል ብለው የዘረዘሯቸውን '7' ክሂሎች በጥናታቸው አቅርበዋል። "ግስታወስ (Memory)፣ ትርጉም /Transilation/፣ ግብራራት /Interpretation/፣ ወደተግባር መለወጥ /Application/፣ ትንተና /Analysis/፣ ግንባታ /Synthesis/ና ግምገማ /Evaluation/" በሚል መጠሪያ የተሰየሙ ናቸው። በደረጃም hierarchy/ በሦስት በመክፈል ለመለየት ተሞክሯል። ነገር ግን ደረጃ ተብለው በተዘረዘሩበት ቅደም ተከተል መሰረት በተግባር ግላየት ስላልተቻለ ሌላ ክፍፍል ፍለጋው ሊቀጥል መቻሉን እነ ኦልያርሰን (1989) ያመላክታሉ።

በዚሁ በቀጠለው የክፍፍል ፍለጋ ምርምር መሰረት የካሮልን (1980፣ 32) 11 ለፈተና የሚቀርቡ ክሂሎች ዝርዝርና የቹየር(1988)ን አልፈን (1989) ስንያርስ በይዘት አግባብነት ልየታ ምህላኑት የቀረበውን የሂዩዝ (1989) ለፈተና የሚቀርቡ የእንበቦ መረዳት ክሂሎች ዝርዝርና የነ ኦልያርሰን (1989፣ 260) በእንብቦ መረዳት ፈተና ጥያቄዎች ሊፈተኑ የሚችሉ ክሂሎች በሚል ርዕስ ስር የወጡ '8' ክሂሎች እናገኛለን።

በነኦልያርሰን የተመለከቱት '8' ክሂሎች በውስጣቸው ባንደኛው ስር ሁለት፣ በሌላኛው ሦስትና በሶስተኛው ሁለት የንዑስ ንዑሳን ክሂሎች የተጠቀሱበት ዝርዝር ነው።

ስምንቱ ዋና ዋና ዝርዝሮች "1. ቃላትን መገንዘብ (Recognition of words) 2. መለየት (Identification) 3. ማስተዋል (Discrimination) 4. ትንተና (Analysis) 5. ትርጉም (Interpretation) 6. መረዳት /መደምደሚያ ላይ መድረስ (Inference)፣ 7. ግንባታ(synthesis) 8. ግምገማ (Evaluation)" የሚሉት ናቸው።

ይኸኛውን ከሌሎቹ (ከቀደሙት) ለየት የሚያደርገው ትምራዊ ብቻ ባለመሆኑ ነው። አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ተዘጋጅተው እንደኛ በላንካስተር ዩንቨርሲቲ የቋንቋ መምህራን የሆኑ አሰተያየት (judgment) እንዲሰጥበት ተደርጎ፣ ሁለተኛ አንድ መቶ የቦንቢ ዩንቨርሲቲ የተግባራዊ ክሂሎች ቡድን ተማሪዎች ተሞክሮ የወጣ ዝርዝር /ልየታ/ ነው።

ከንሉልደርሰን (1989) በኋላ በብሩተን፣ ፖርክንስና አንቨር (1991) የተካሄደ ሌላ ጥናት ሙኖሩን የሚጠቁሙት ለምሌይ (1993)ም "The Notion of Subskills in Reading Comprehension Tests" በሚል ርዕስ ያወጡት መጣጥፍ ሌላው ባንብቦ መረዳት ፈተና ንውላን ክሂሎች እንማንነት ዙሪያ የሚሽከረከር የቅርብ ጊዜ ጥናት ነው። የጥናቱ አካሄድ ከንውላን ክሂሎች ዝርዝር ጋር ጥያቄዎችን በማዛመድ ስልት ነው። ፈተናው ከሁለት 1500 ቃላት አካባቢ ያላቸው ምንባቦች የተዘጋጀ ነው። 58 ጥያቄዎች ያሉት ነው።

በብዙ የተለያዩ ጥናቶቻቸው የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ለይተው ለማመልከት በሙከራ የቀጻሚነቱን ስፍራ የያዙት የሚመስሉት ዊየርም በ (1988፣ 1990፣ 1993፣ 1997) ስራ ዎቻቸው ለፈተና ሊቀርቡ የሚገባቸውን የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ዘርዝረው /ለይተው/ አሳይተዋል።

ከነዚህ ውስጥ በ(1993) ስራቸው ያቀረቡትን ለአብነት እንመልከት።

ዊየር በዚህ መፅሐፋቸው በአንብቦ መረዳት ፈተና ሊመዘኑ የሚገባቸው ክሂሎችን በሁለት ከፍለው በተለያዩ ሰንጠረዦች አቅርበዋል። የመጀመሪያው ቡ"አካዳሚ" መስክ ሊመዘኑ የሚገባቸውን፣ ሁለተኛው በተግባራዊ ትምህርት አላማ /በኢአካዳሚያዊ ትምርት/ ሊመዘኑ የሚገባቸውን ክሂሎች የያዙ ናቸው። በርግጥ ከሰንጠረዦቹ ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው በመካከላቸው ይኸ ነው የሚባል የነላ ልዩነት የሚታይባቸው አይደሉም።

ለማንኛውም ከዚህ ጥናት ጋር ይበልጥ ግንኙነት የሚኖረው በኢአካዳሚያዊ የቋንቋ ትምህርት መስክ ሊመዘኑ የሚገባቸው ክሂሎች ብለው የለዩአቸውን የያዘው ሰንጠረዥ ስለሆነ በኔ ላይ እናተኩራለን።

ይህ በሁለተኛው ሰንጠረዥ የቀረበ የተባለው፤ ልየታ ሦስት ዋና ዋና ክሂሎችና በእያንዳንዱ ዋና ክሂል ስር ሊሎች ንውሳን ክሂሎች ያሉበት ነው።

አንደኛው አሰሳ ነው . ፅሑፍን በፍጥነት እነባበብ እያነበቡ። (Skimming: going through a text quickly.)

- መለየት:- ለሚፈለገው ጉዳይ የተወሰነ ክፍል ወይም ሁሉም ተፈላጊ መሆን አለመሆኑን መለየት (Identifing: which part, or whether part or whole, is relevant to an established need.)
- ዋናውን ሀሳብ ለማግኘት መቃኘት (Surveying for gist.)
- በተኮላ መልክት መልክት በማድረግ የተለየ መረጃን ማመልከት (Scanning to locate specific information.) የሚሉትን ክፍሎች የያዘ ነው።

ሁለተኛው ዋና ዋና ሀሳቦችንና ዝርዝር መረጃዎችን ለመረዳት በጥንቃቄና በጥልቀት ማንበብ (Reading carefully to understand main ideas and important detail.) የሚልሲሆን በውስጡም የሚከተሉትን ክሂሎች የያዘ ነው።

ዋና ሀሳቦችንና ጠቃሚ ዝርዝር መረጃዎችን ለመለየት በጥንቃቄ ማንበብን (ይህም የክርክሩን ፅድገት አቅጣጫ ፈልን ማግኘትን፤ ያነበቡትን ፅሑፍ ዋና ዋና ነጥቦችና ዝርዝር መረጃዎች በቢጋር በመግለፅ ፅሑፍን ማሳጠርን ይይዛል።)

(Reading carefully for mainideas and important detail: (might include tracing the development of an argument, reducing what is read to an outline of the main points and important details)

- እውነታን ከአስተያየት መለየትን፤ /Distinguishing fact from opinion,)
- ፀሐፈው ለእንባቢውና ላነሳው ርዕሰ ጉዳይ ያለውን አተያይ መገንዘብን፤ (Recognising attitude to reader and topic) (ምሳሌ አስተሳስብን ለመለወጥ (persuasion) ወይም ለማስረዳት (explanation) መሆኑን።)
- ኢንፈረንሳዊ (ከምንባቡ ውጭ ያለ ፅውቀትን በመጠቀም) ትርጉምን መረዳት - ፅሑፍን ከፅሑፉ ውጭ በመሄድ መረዳት ለምሳሌ የታላት ትርጉምን ከምዕዳድና ከእውደ መረዳት፤ የተግባቦታዊ ተግባራትን ያለ ግልፅ የሆኑ አመልካቾች መረዳት (understanding inferred meaning understanding text by going outside it, e.g. by making inferences, deducing meaning of lexical items from morphology and context, understanding communicative functions without explicit indicators.)

ሥስተኛው የዊየር (1993) የእንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ዋና ክፍል የሚከተሉትን ስነ-ልሳን ነክ ክሂሎች የያዘ ነው።

- ፅንሰ ሀሳቦችን መረዳት (ሰዋስዋዊ ሀሳቦችን) እንደ ምክንያት፣ ውጤት፣ አላማ፣ ንፅፅር ... ያሉትን(understanding concepts (grammatical notions) such as: cause, result, purpose, comparison:)
- የዐረፍተ ነገርንና የሀረግን መዋቅራዊ አገባብ መረዳት (Understanding syntactic structue of sentence and clause.)
- አገባብን አመልካቾች መረዳት፣ /Understanding discourse markers.)
- ቃላዊና/ወይም ሰዋስዋዊ አያያዦችን መረዳት /Understanding lexical and/or grammatical conesion.)
- ቃላትን መረዳት /Understanding lexis.) (ዊየር 1993፣ 73)።

ሊላውና በመጨረሻ የምናነሳው እስካሁን ከተጠቀሱት በብዙ መልኩ ለየት የሚለውን የኑክላንግ (1992) በእንብቦ መረዳት የ'ኢንፈረንሶች' ክፍፍል/taxonomy of inferences/ ነው።

እስካሁን ከተጠቀሱት ተመራማሪዎች ውስጥ ለዚህ ጥናት በተዘጋጀው የክሂሎች ዝርዝር 'ከለሰት' አውድ ፍች ተኮርና ኢአውድ ፍች ተኮር 'ኢንፈረንስ' መባል በሁለት ዋና ዋና ክፍል ስር የተመደቡትንም ሆነ ያልተመደቡትን ንዑሳን ክሂሎች በዝርዝር ያነሳ የለም ማለት የሚቻል ይመስለናል። እኒህ ተመራማሪ ከሌሎች ለየት የሚሉትም በዚህ ሌሎቹ ጥቅል በሆነ ቁንቁ በእንብቦ መረዳት ትምህርት /ፈተና/ ሊቀርብ /ሊመዘን/ የሚችል አንድ ንዑስ የክሂል አይነት እንደሆነ ገልፀውት ያለፉትን በውስጡ የሚያቅፋቸው ንዑሳን ክሂሎች ያሉት እንደሆነ አድርገው፣ አፍታተው በማቅረባቸው ነው ማለት ይቻላል።

በርግጥ እኒሁ ተመራማሪ በክለሳ ድርሳን መልክ ካቀረቡት ዘገባ መረዳት እንደሚቻለው በእንብቦ መረዳት ትምህርት (ፈተና) የኢንፈረንስ ክፍፍል (taxonomy) አዲስ ክስተት ወይም በነሱው የተጀመረ አይደለም። የተለያዩ ምሁራንን ጠቅሰው "ብዙዎች ፀሐፍት ኢንፈረንስ በእንብቦ መረዳት ቁንጮ ነው ይላሉ" (Many writers claim that 'inference' is central to reading comprehension) የሚሉን ራሳቸው ችካላንጋ /1992፣ 697) በዚህ ጥናታቸው የተለያዩ የኢንፈረንስ አይነቶች መኖራቸውን የሚያመለክቱ ጥናቶች በተለያዩ ተመራማሪዎች በ(1976፣ 1979፣ 1980፣ 1981፣) የተካሄዱ መሆናቸውንና ከነዚህ ውስጥ በ(1978) በሁለት፣ በ(1979) በሦስት ተመራማሪዎች የወጡት ክፍፍሎች በተለይ ለሌሎች የኋላ ጥናቶች፣ ለነሱም ጭምር መነሪት እንደሆኑ አድንቀው ይገልጿቸዋል።

ከነዚህ ካደንቋቸው ተመራማሪዎች ክፍፍል/taxonomy) በመነሳትም በሚከተለው ስልት በእንብቦ መረዳት ትምህርትና ፈተና ሊቀርቡ የሚችሉ /የሚገባቸውን/ ክሂሎች ናቸው ያሏቸውን የኢንፈረንስ ክሂሎች በጥናታቸው አቅርበዋል።

ዋና መደብ (Basic category)	አይነት (Specific Types)	የጥያቄና መልስ ግንኙነት (Question-Answer Relationship)
ቃላዊ (Lexical)	ሀ. ወኪላዊ ኢንፈረንሶች (Pronominal Inferences) ለ. የአሻሚ/የእንግዳ ቃላት ፍቺዎች (Ambiguous/Unfamilar word meanings)	በምንባብ የተገለፀ/ያልተገለፀ - መረጃ ተኮር Textually/Scriptally Implicit
አውዳዊ ፍቺዊ (Propositional)	ሀ. ተጠይቃዊ መረጃዊ /logical informational/ . የተለዩ መረጃዊ /referential/ . (የተለዩ ሰዎችን፣ መላሪያዎችን፣ ዕቃዎችን) . ቦታ . ጊዜያዊ/Spatio - temporal) (ቦታዎችን፣ ጊዜያትንና የሁነቶችንና የድረጊቶችን አውድ የሚይዙና ለማን? ለምን? የት? መቼ? ጥያቄዎችን መልስ የሚሆኑ ናቸው።) ለ. ተጠየቃዊ ገላጭ /Logical Explanatory) . መቀስቀሳዊ/motivational/ . መነሳሳትን . ምክንያታዊ/causative) የሁነቶችንና የድርጊቶችን ምክንያቶችና ውጤቶች) . አመቻኝት/enablement/ሁነቶች እንዲፈጠሩ (እንዲከሰቱ) ያለ የሁኔታዎች አመቻኝት)	ምንባብ ተኮር (Textually implicit)
አውዳዊ ፍቺዊ የለሆኑ (pragmatic (scriptal) (እነዚህ ኢንፈረንሶች የሚመነረቱት በአብዛኛው በቅዱሩ ውስጥ ከነፈሩ መረጃዎች ውጭ ነው፤ በአንባቢው የቀደመ ዕውቀት (The reader's store of prior knowledge (schemata). ላይ የሚመነረቱ ናቸው)።	ሀ. አብራሪያዊ መረጃዊ /Elaborative informational) . የተለዩ መረጃዊ . ቦታ . ጊዜያዊ ለ. አብራሪያዊ ገላጭ/Elaborative Explanatory) . መቀስቀሳዊ . ምክንያታዊ . አመቻኝት ሐ. ግምገማዊ/Evaluative/ (በዚህ የኢንፈረንስ አይነት የተፈታኞቹ ስሜት፣ ዕውቀትና ዕምነት ቦታ የሚያገኝበት ነው።)	ኢምንባብ ተኮር (Scriptally Implicit)

(ቱኩለንግ፣ 1992፣ 705)

ከነዚህ እስካሁን ከተጠቀሱት በተጨማሪ "Royal Society of the Arts" የሚባለው ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተግባቦታዊ ተግባር ፈተና የሚውሉ በማለት በሦስት ደረጃ /level/ በመከፋፈል ያወጣቸው፤ በደረጃ አንድ ስር"6"፣ በደረጃ ሁለት ስር "2" ፣ በደረጃ ሦስት/Advanced level/ ስር "5" ከሂሎች፤ ለ "IELTS reading tasks and texts" 7 የክሂል አይነቶች ተለይተው (ተዘርዝረው) እናገኛለን። በሌሎቹ የቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ለምሳሌ እንደ ኢ.ኤል.ቲ /E.L.T./ ባሉትና በተለያዩ የፈተና ቦርዶች የወጡ ሌሎች ዝርዝሮችም አሉ (ዶጀኔ፣ (1994)፣ አልደርሰንና ለክሚኒ (1989)፣ አልደርሰንና አርካርት፣ (1984)፣ ለምሊይ (1993)፣ ዌየር (1990) ከ

ለዚህ ጥናት ከነዚህ ቦርካታ የንባብ ክሂሎች ክፍፍል ውስጥ በይበልጥ በመነሻነት የሚያገለግሉት፣ ሀዌየር (1993፣ 1990)፣ ሂዩዝ (1995)፣ አልደርሰንና ለክሚኒ (1989)፣ ሂተን (1990)፣ ፑካላንግ (1992) የተመለከቱት ናቸው።

2.7.2 በአንብቦ መረዳት ፈተና የምንባቦችና የአጠያየቅ ዘዴዎች አመራረጥ

ባንብቦ መረዳት ፈተና አዘገጃጀት ሂደት የችሎታዎቹ አይነት ከቋንቋው ትምህርት አላማ ወይም ከመርሀ ትምህርቱና/ከሌሎች መሳሪያዎች ይዘት ከተለየ በኋላ ቀጣዩ ተግባር እነዚህን ችሎታዎች እንዴት እንፈትን? ለሚለው ሞጋች ጥንቃቄንና ማስተዋልን ጠያቂ ጥያቄ ተገቢ ትኩረት ሰጥቶ ለየክሂሎቹ የሚስማሙ፣ አምንታዊነት ያለው የይዘት አግባብነትና ሀቀኝነት፣ ማንፀባረቅ የሚችላቸውን ምንባቦችና ያጠያየቅ ዘዴዎች መምረጥ ይሆናል።

ከዌየር (1990፣ 1993)፣ ሂዩዝ (1995)፣ ሂተን (1990፣ 1991) እና ከሌሎችም ይህን ጉዳይ ያነሱ የቋንቋ ፈተና ተመራማሪ ሊቃውንት ገለፃና ማብራሪያ እንደምንረዳው ለምንባቦችና ለጠያየቅ ዘዴዎች ተገቢ ትኩረት አለመስጠት ማለት ፈተናው አግባብነት validity/፣ ሀቀኝነት /reliability/፣ አጠቃላይነት /Comprehensiveness/ እና በጎ ተፅዕኖ beneficial backwash/ እንዳይኖረው መንገድ እንደመዋረግ የሚቆጠር ነው።

2.7.2.1 የምንባቦች አመራረጥ

ከላይ እንደተገለፀው አንብቦ በመረዳት ችሎታ ፈተና ዝግጅት ከይዘት (ባህሪ) መረጣ (ንዑሳን ክሂሎች ልየታ) ቀጥሎ ከሚመጡ ተግባራት አንዱ ለየንዑሳን ክሂሎቹ መለኪያ ጥያቄ መጠየቂያ የሚያገለግሉ የተለያዩ የፅሑፍ አይነቶችን መምረጥ ነው። ከሁለቱ፣ ፈጠራዊና አፈጠራዊ /literal and non-literal) በመባል ከሚታወቁት አቢይ ዘርፎች ስር ከሚታቀፉት

የተለያዩ የፅሑፍ አይነቶች ውስጥ ተግሪውን በገሀዱ ዓለም የሚያጋዮሙትን የፅሑፍ አይነቶች የሚወክሉ፣ የሚሰቡ፣ በክፍል ትምህርት የተዋወቋቸውን የሚያንፀባርቁ ፅሑፎችን መፈለግና መምረጥ ነው (ሂዩዝ (1995)፣ ተስፋዩ (1981 እ.ኢ.አ.)፣ ባችማንና ፓልመር (1997) ካንድሊን (1994)).

ዓላማው ተደጋፊነት ያለው የምንባቦች አመራረጥ አጠር አጠር ያሉና ብዙ እንዲሆኑ የሚገለፀው ነው (ሂዩዝ (1995)፣ ተሾመ (1995)፣ ማድሰን (1983)፣ ተስፋዩ (1981) ካንድሊን (1994)).

እነዚህ አጠር አጠር ያሉና ብዙ ምንባቦች የተለያዩ የፅሑፍ አይነቶችን የሚወክሉ፣ በደራት የተለያዩ፣ ትክክለኛ /Authentic/ የሆኑ መሆን እንዳለባቸው ምሁራኑ ያስገነዝባሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ከፍ ብሎ እንደተወሳው ለየክሂሎቹ የሚስማሙ ምንባቦችን ለመምረጥ ጥረት ማድረግም ያስፈልጋል። ለምሳሌ በአስላ ንባብ የተለዩ መረጃዎችን የማመልከት ክሂልን ለመሙዘን የሚያስፈልጉ ምንባቦችና ለዚህ ጥናት በተዘጋጀው ቸክሊስት በተራ ቁጥር አራት ስር የተዘረዘሩትን የጥልቅ ንባብ /Detailed reading/ ክሂሎች ለመመዘን የሚያስፈልጉ ምንባቦች ተመሳሳይ አይደሉም። ሂዩዝ (1995፣ 119) እንደሚያስረዱት የመጀመሪያውን ለመፈተን የተለያዩ ቁርጥራጭ መረጃዎችን የያዙ ምንባቦችን መፈለግ ያስፈልጋል (look for passages which contain plenty of discrete pieces of information)። እስከ 2,000 እና ከዚያም በላይ ቃላት ያሏቸው ምንባቦች ሊፈለግ ይችላል። በሁለተኛው ስር ያሉትን ግን ጥቂት ዐረፍተ ነገሮች በተካተቱባቸው ምንባቦች መመዘን ሊቻል ይችላል።

ለግጠመለል የምንባቦቹ አመራረጥ፣ የይዘት አግባብነትን፣ ህያውነትንና አምንታዊ የባከኖች ውጤትን ከፍ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል። ከምንባቦቹ የሚወጡት ጥያቄዎች ቁጥርም በተመራማሪዎቹ ጥናት የተመለከቱትንና የቋንቋውን ባህሪ ያገናዘበ ቢሆን መልካም ነው።

2.7.2.2 ያጠያየቅ ዘዴዎች

ለየንዑሳን ክሂሎች መመዘኛነት የሚሰማሙ፣ የይዘት አግባብነትን፣ ህያውነትን፣ ኢጠቃላይነትንና አምንታዊ የባከኖች ውጤትን ግምት ውስጥ ያስገባ የምንባቦች አመራረጥ ከተከናወነ በኋላ ለተለያዩ ክሂሎች መለኪያነት የሚሰማሙ፣ (የተለያዩ ተፈታኞችን የተለያየ ባህሪ ግምት ውስጥ ያስገባ) የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ ጥያቄዎችን ማውጣትም እንዲሁ የፈተና አዘጋጅ ሊሳሙ ተግባር ነው። የቋንቋ ፈተና የዕድገት ደረጃዎች በተነሱበት

ጠቀሜታ አፅንኦት ሰጥተው ከገለፁ ተመራማሪዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። የተለያዩ ክሊኦትን ለመመዘን የሚያስችሉ የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎች መኖራቸውን የሚያመለክቱት አነዚህ ተመራማሪዎች እንደሚያስገነዝቡን አንብቦ መረዳትን ለመፈተን ተስማሚ የሆኑ ዘዴዎች አሉ። ከነዚህ ለአንብቦ መረዳት ፈተና ተስማሚ ናቸው ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ በዌየር (1990፣ 42.5፣ 1993፣ 77.97) ሂቶን (1990፣ 79.92፤ 1991፣ 105.133)፣ አልደርሰን፣ ክላፓምናዎል (1995፣ 15. 16)፣ ሂዩዝ (1995፣ 120.129) ተዘርዝረው የምናገኛቸው ብዙ ጊዜ የሚሰራባቸው እንደሆኑ የዘረዘሯቸው ምሁራን ይመሰክራሉ።

ከነዚህ ውስጥ በብዙዎቹ ሰራዎች የተደጋገሙትን በቅኝት መልክ በመመልከት ይህን ክፍል እናጠቃልላለን። ጓላም ፈተናዎቹን ለመመርመር እንገለገልባቸዋለን።

1. ምርጫ ሰጭ ጥያቄዎች /Multiple choice items/

አንብቦ መረዳትን ለመፈተን ከሚያገለግሉ ዘዴዎች አንዱ ምርጫ ሰጭ ዘዴ እንደሆነ ሂቶን (1990)፣ ዌየር (1990)፣ አልደርሰን፣ ክላፓምና ዎል (1995)፣ ሂዩዝ (1995) ይገልፃሉ። በዚህ ዘዴ የተለመደው የአግራጮች መጠን አራት ነው። ሶስት አሳሳች፣ አንድ ትክክለኛ መልስ የሚገኝበት ነው። ሦስትም፣ አምስትም አማራጮች የሚኖሩበት አጋጣሚም አለ።

እነዚህ ተመራማሪዎች እንደሚያመለክቱት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሚያስከትላቸው ብዛት ያላቸው ጉዳቶች የተነሳ አንብቦ መረዳትን ለመፈተን ብቃት የሌለው ዘዴ እንደሆነ እየተቆጠረ መጥ ደል።

እንደተባለው ከሚያስከትላቸው በርካታ ጉዳቶች የተነሳ ከትምራ አንፃር የሚነቀፍ ዘዴ እየሆነ ከመምጣቱም በተጨማሪ በተለይ ዌየር (1993) እንደሚያስረዱት በተግባር አንብቦ መረዳትን ለመፈተን በሚጀጋጁ የብዙ ሀገር ፈተናዎችም ሲጠቀሙበት መታየቱ እየቀረ ነው። ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተፈታኝ ያለባቸው አገሮች ለምሳሌ እነቻይና ሳይቀሩ በዚህ ዘዴ መጠቀሙን እየተው ነው ('Multiple choice is not longer employed ... even in countries with infinitely grater numbers of candidates and logistical problems, e.g. China', --) (ዌየር 1993፣ 82)።

በሌላ አኳያ በጥንቃቄ መዘጋጀት ከቻለ፣ በባለሙያዎቹ ከተመረመረ፣ በቅድመ መከራ (Pre testing /pilot test) ያልፀበትን ችግሮች መቀነስ ከተቻለ የተወሰኑ የአንብቦ መረዳት ክሊኦትን ለመፈተን እንደሚያስችል ከሂቶን 1990) ና ስፕራት (1988) ማብራሪያ እንረዳለን።

2. እውነት/ሀሰት ዋያቄዎች /True/False Items/

ይህ የአጠያየቅ ዘዴ ለተፈታዮቹ "ዐረፍተ ነገሮች ቀርበውላቸው ዐረፍተ ነገሮቹ የያዟቸው ሀሳቦች ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ዐረፍተ ነገሮቹ ራሳቸው /በቋንቋ ፈተና/ ትክክል ወይም ስህተት መሆናቸውን እንዲለዩ የሚጠይቅ ነው።" /ተስፋዬ፣ 1981፣ 125/፣ ሂተን (1990)ና ሌሎች ተመራማሪዎችም እንደሚያስረዱት የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ለመመዘን የሚያስችል ነው። ሀያውነት ያለውም ነው። በርግጥ እንደምርጫ ሰዳው ሁሉ ያዝየውም ብዙ ድክመቶች ያሉበት ነው። ድክመቶችን ለመቀነስ ግን የተለያዩ መፍትሄዎች እየተሰነዘሩ ነው። ከድክመቶቹ አንዱ የሆነውን የ50ፀ የግምት ዕድል ለመቀነስ ለምሳሌ አማራጮቹን ወደ ሰባት ከፍ ማድረግ ተጀምሯል ። መልሱ አልተሰጠም /መረጃ አልቀረበም የሚል አማራጭ በመጨመር ማለት ነው (ሂዩዝ (1995)፣ ሂተን (1990)፣ አልደርሰን፣ ኦሊፖምናምል (1995))።

ምንባቦቹና ዋያቄዎቹ ለተፈታዮቹ በጣም የሚከብዱ እንዳይሆኑ ማድረጉ ሌላው መፍትሄ ነው (ሂተን 1990) ተፈታዮቹ እውነት/ሀሰት ላሉበት ምክንያት /ማስረጃ/ ከምንባቡ እንዲሉ እያደረጉ መጠየቅም የተለመደ እየሆነ የመጣ የዘዴው ድክመቶች ቀነሽ ሌላው ሰልት ነው ማለት ይቻላል። ስለተማሪዎች የተወሰነ ችሎታ ለማወቅ ከተፈለገ የዋያቄዎቹን ቁዋር ከፍ ማድረግም ጥሩ ነው። (አልደርሰን፣ ኦሊፖምና ምል 1995፣ 51) እንደተባለው ይህ ዘዴ በፐንቶቁ የተዘጋጀ ከሆነ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን በተለይም የደራሲውን አላማ ... መንገዘብን፣ የተለያዩ የ'ኢንፈረንስ' ክሂሎችን፣ ለመፈተን ተስማሚነት ያለው ነው (ስንፈቱት፣ 1988፣ 67) ሀረሰና ግከሳን (1994፣ 36)።

3. ግዛመድ /Matching/

በአልደርሰን ኦሊፖምና ምል (1995፣ 51) ትርጓሜ መሰረት ግዛመድ ሲባል ተማሪዎች ሙለስ ለሙ የሚገቡ ዝርዝሮች ተሰጥተዋቸው እነዚህን (መልስ ሊሆኑ የሚችሉትን) ከሌሎች የቃላት፣ የሀረጋት፣ የዐረፍተ ነገሮች፣ የእንቀጾች ወይም ምስላዊ ፍንጮች (Visual clues.) ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግን የሚመለከት ነው። ተስፋዬ (1981፣ 126) የነአልደርሰንን ሀሳብ ከሚጋሩት ውስጥ አንዱ ናቸው። እነዚህና ሌሎች የፈተና ባለሙያዎች እንደሚመክሩት የሁለቱን ዝርዝር ቆጵል ማድረግ ተገቢ እይደለም። የአማራጭ ክፍሉን ዝርዝር ከዚያኛው በዛ ያለ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ዘዴ ፈተና ሲዘጋጅ በመጀመሪያው ረድፍ (column) ያሉት እያንዳንዳቸው በረድፍ ሁለት ካሉት ውስጥ ካንዱ ጋር ብቻ የሚዛመዱ መሆናቸውን በቅድሚያ ማረጋገጥ ይገባል።

ይህ ዘዴ በእንብዐ መረዳት ፈተና ሂተን (1990) ይበልጥ የቃላት ችሎታን ለመመዘን የሚያገለግል እንደሆነ አፅንኦት ሰጥተው ቢገልፁም ሌሎች ግን ለምሳሌ ሳንራት (1988፣ 67) የአሰላ ንባብ ክሂሎችንም ለመመዘን እንደሚያስችል ነው የሚያመለክቱት።

4. ባዶ ቦታዎችን መሙላት

ይህ ዘዴ በጽንቂ ፈተና ተመራማሪዎች በሶስት የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴነት የሚጠሩትን ቀመር መራሽ /ስርአታዊ/ የቃላት ግድፈትን (cloze)፣ ኢቀመር መራሽ/ሆን ተብሎ፣ ተመርጦ፣ የተገደፈን ባዶ ቦታ ሞሟላትን /Selective deletion gap filling)፣ በፅሑፍ ውስጥ ግማሽ የመነሻ /የመድረሻ/ ፊደሎቹ የተገደፉበትን እያንዳንዱ ሁለተኛ ቃል በተገደፉት ፊደላት ሞሟላት /C - Test/ በመባል የሚጠሩትን በጋራ የሚመለከት ነው። ሦስቱም፣ በመካከላቸው በትርጉማቸው የተገለፀው አይነት መጠነኛ ልዩነት ይታይባቸው እንጂ ተመሳሳይ ክሂሎትንና ችሎታን ለመለካት የሚያገለግሉ ናቸው። የሚገደፉትም በመጀመሪያም፣ ሁለቱ ቃላት፣ በሦስተኛው የቃል መነሻ /መድረሻ/ ግማሽ ፊደሎች ናቸው።

ሦስቱም ዘዴዎች ሥነልሳን ነክ የሆኑ የእንብዐ መረዳት ክሂሎችንና አጠቃላይ እንብዐ የመረዳት ችሎታን ለመለካት የሚያገለግሉ ናቸው። (ቄየር 1990፣ 46-49)፣ አልያርሰን ኮሊፖምናፖል (1995፣ 55-56) በተለይ ቄየር (1993) እንደሚያመለክቱት እነዚህ ሦስት ዘዴዎች በነየው የ(1993) ስራ ገፅ (73) የእንብዐ መረዳት ልየታ በተራ ቁጥር ሦስት ስር የተዘረዘሩትን ንቃላን የሰነልሳን ክሂሎች ለመፈተን /For testing microlinguistic skills -) ይበልጥ የሰማሚነት ያላቸው ናቸው። (ቄየር 1993፣ 96)።

5. ቅደም ተከተልን መለየት /identifying order/

በዚህ ዘዴ ተፈታዮች እንድን ሁናቴ፣ ወይም ክስተት፣ ወይም ድርጊት የሚያሳዩ በቅደም ተከተላቸው መስረት ያልተቀመጡ /የተዘበራረቁ/ ዐረፍተ ነገሮችንና (አንቀፆችን) እንዲያስተካክሉ ይጠየቃሉ። በዚህ ያጠያየቅ ዘዴ በዐረፍተ ነገሮችና አንቀፆች መካከል ያለን ዝምድና /ግንኙነት/፣ የፅሑፍ አደረጃጀትን፣ አያያዦችን (ተውላጦችን፣ አገባብ አመልካቾችን...) የመረዳት ክሂሎችን ለመመዘን ይቻላል። ስንራት (1988፣ 67) ሄዩዝ (1995)፣ ዐረብና ሚከሳን (1994፣ 36) ።

6. መረጃ ግኽጋገር /information transfer/

ይህ ያጠያየቅ ዘዴ እንብዮ መረዳትን ለመፈተን እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነ፣ ብዙ ጊዜም (ተዘውትሮም የሚሰራበት እንደሆነ ከዌየር (1990፣ 1993) አልደርሰን፣ ከላፓምናዎል (1995)፣ ስፕራት (1988)ና ሂዩዝ (1995) ግብራሪያ እንረዳለን።

እኒህ ተመራማሪዎች እንደሚያስረዱት አተገባበሩ በአብዛኛው ተፈታኞች በምንባብ ውስጥ በፈደል የቀረቡ መረጃዎችን ኢፈደላዊ /non-verbal/ ወደሆኑ ወደቻርት፣ ሰንጠረዥ፣ ወዘተ.. ለውጠው እንዲያቅረቡ በማድረግ ነው። በተቃራኒ መልኩ በኢፈደላዊ ስልት የቀረቡ መረጃዎችን ወደ ፈደላዊ መለወጥም ሊሆን ይችላል።

እነ አልደርሰን (1995) ከዚሁ ጋር አያይዘው እንደሚገልፁት ይህ አይነት ተግባር በገሀዱ ዓለም ተግባራዊ ክንውኖች ውስጥ የሚዘወተር ነው። ስለዚህ በፈተና መንፀባረቁ አግባብነት ያለው ነው ማለት ነው።

ከላይ የተጠቀሱት ተመራማሪዎች እንደሚያስረዱት ይህ ዘዴ ብዛት ያላቸው ጥያቄዎች ሊጠየቁበት፣ የተለያዩ የእንብዮ መረዳት ክሂሎችን ለመሸፈን የሚያስችል ነው። በተለይም ዋና ሀሳብን በፍጥነት ንባብ መገንዘብን፣ የተለየ መረጃን በፍጥነት ንባብ መለየትን፣ ዋና ዋና ሀሳቦችንና ጠቃሚ ዝርዝር ሀሳቦችን አሳጥሮ መግለፅን፣ ባጠቃላይ በዌየር (1993፣ 95) በአጠቃላይ አሳማ ሊመዘኑ የሚችሉ ተብለው ከተለዩት ክሂሎች ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ስር የታቀፉትን ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ለመመዘን የሚያገለግል ያጠያየቅ ዘዴ ነው።

አስተራረሙ እንዳንድ ጊዜ የሚሰጠው መልስ ሰሞችን፣ ቁጥሮችን፣ ... የሚይዝ ስለሆነ አድሏዊነት ሳይታይበት ሊታረም ይችላል። (---- can be marked objectively) አንዳንድ ጊዜ ሰሪፈንትና በአጫጭር አረፍተ ነገሮች የሚመለስም ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ እንደ የአጭር መልስ የጥያቄ አይነቶች አድሏዊነት /subjectivity/ የሚታይበት ሊሆን ይችላል። (አልደርሰን፣ ኦፓፓምናዎል 1995፣ 52)።

ከዚህ በቀር ዌየር (1993) እንደሚያስረዱት ባዶ ቦታዎችን በመሙላት ስር በተጠቀሱት ሶስት ያጠያየቅ ዘዴዎች ሊመዘኑ የማይችሉ የንባብ ክሂሎችን ለመመዘን አይነተኛው ዘዴ የ ንየው ነው። ዌየር ከዚሁ ጋር አያይዘው እንደሚገልፁት በዚህ ዘዴ የሚቀርቡ ጥያቄዎች የተፈታኞቹን የንባብ ችሎታ በሚመለከት ሀያው የሆነ መረጃ የሚሰጡ ናቸው።

7. ባለአጭር መልስ ጥያቄዎች /Short Answer Items/

እንደ መረጃ ማቀጋገር ሁሉ በብዙ ተመራማሪዎች አንብቦ መረዳትን ለመፈተን ተመራጭነት ያለው መሆኑ የተመሰከረለት ያጠያየቅ ዘዴ ነው። ባጠቃላይ አጭር መልስ ጠያቂ ጥያቄዎች የሚባሉትም በአብዛኛው፣ ተፈታኞች መልሶቻቸውን በፈተና ወረቀቱ ውስዋ በተሰጠ ክፍት ቦታዎች ላይ በመጻፍ እንዲያሳዩ የሚጠይቁ አይነት ጥያቄዎች ናቸው። አቀራረባቸው ለተፈታኞች የሚገባውን ያህል ክፍት ቦታ በመተው ወይም ሊመለሱ የሚገባቸውን ቃላት በመግደፍ የተገደፉትን እንዲያስገቡ ባዶ ቦታዎችን በመተው ወይም በሌላ መንገድ ሊሆን ይችላል።

ይህ ያጠያየቅ ዘዴ ተመራማሪዎቹ እንደሚያስገነዝቡት አንብቦ መረዳትን ለመፈተን ከሌሎች ዘዴዎች ሁሉ በተለይም ከምርጫ፣ እውነት/ሀሰት፣ ማዛመድ እጅግ በጣም የተሻለ ከግምት ምላሽ የራቀ፣ የተግራምቹን እውነተኛ ችሎታ የሚያመለክት ዘዴ ነው። ዌየር (1993፣ 68) ይህንኑ ብቃቱን በማስመልከት ሲገልፁ ያሉትም "ይህ ዘዴ አንብቦ መረዳትን ለመፈተን በጣም፣ በጣም ጠቃሚ የሆነ ዘዴ ነው" /'The technique is extremely useful for testing reading comprehension') ነው።

በዚህ ያጠያየቅ ዘዴ በሚዘጋጁ ጥያቄዎች አንድ ፅሑፍ /text/ ውስዋ ያሉ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሸፈን ይቻላል። ይህ ዘዴ በተለይ አጠቃላይ ሀሳብን /overall gist/ ፣ ዋና ሀሳቦችንና ጠቃሚ ዝርዝር መረጃዎችንና እነዚህን የሚያስተላልፉትን /የሚሸከሙትን/ መዋቅሮችንና ቃላትን መረዳትን /understanding of structures and lexis that convey this.) ለመፈተን ተመራጭነት ያለው ይሁን እንጂ ባጠቃላይ በዌየር (1993፣ 73) በሰንጠረዥ 3.3 በቀረቡት ዮስት ዋና ዋና ክፍሎች ውስዋ የሚገኙ የተለያዩ ንዑሳን ክሂሎችን ሁሉ ለመገምገም የሚያስችል ዘዴ መሆኑን ዌየር (1993) ና ሀረስናግክካን (1994፣ 36) ያስረዳሉ።

የዚህ ዘዴ ድክመት እንደሆን የሚገለፀው በተግረው መልስ አሰጣዋ ላይ የፅሕፈት ክሂል ጎልቶ የሚንፀባረቅ መሆኑና ስፋ ያለ መልስ ጠያቂ ጥያቄዎችና የኢንፈረንስ ክሂሎችን የሚለኩ ጥያቄዎች መልሶች አስተራረም ላይ ሊከሰት የሚችለው አድሏዊነት (subjectivity) ነው።

ምዕራፍ 3

3. የአጠናን ዘዴ

3.1 ተጠኝዎች

ለሌላ አላማ በሌላ ክፍል እንደተገለፀው በዚህ ጥናት ተጠኝዎች ከ1987 - 1990 የተሰጡት የአስራ ሁለተኛ ክፍል የሞዴል ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ክፍሎች ናቸው። በመነሻ ላይ የ1986 ዓ/ምህረትንም ለማካተት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ለጥናት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የዚህን ዓመት ፈተናዎች ለማግኘት ባለመቻሉ በቀሩት አራት ዓመታት /1987 - 1990/ በተሰጡት ፈተናዎች ላይ ብቻ ጥናቱን ማካሄድ ግድ ሆኗል። እነዚህ የቅርብ ዓመታት ፈተናዎች የተመረጡበት ምክንያትም እንደኛ በምዕራፍ አንድ 1.1 እንደተገለፀው አዳዲስ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ተዘጋጅተው በስራ ላይ የዋሉት ከ1984 ወዲህ ስለሆነ ከነሱ ጋር በተገናዘበ መንገድ ለመመርመር ስለሚያመች ነው። ሁለተኛ የፈተናዎቹ አዘገጃጀት ንድለቶች የሚታዩበት ሆኖ ቢገኝ ንድለቶቹን ለማረም ሊያስችል ስለሚችል ነው።

3.2 ናሙና /Sampling/

3.2.1 የፈተናዎች፣ የክልልና የባለሙያች አመራረጥ

የሚጠኑት ፈተናዎች ዓመተ ምህረቶችና የክፍሉ ይረጃ፣ ጥናቱ የሚካሄድበት ክልልና የፈተናዎቹን ጥያቄዎች የሚከፋፍሉ ባለሙያዎች /experts/ በይሁንነ ናሙና /purposive sampling/ ስልት ተመርጠዋል። ለነዚህ ክፍሎች በተለይ ይህ የናሙና ስልት የተመረጠው በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ነው። የፈተናዎች በ3.1፣ የክልሉ፣ በ1.4 ስር የተዘረዘሩት ናቸው።

ባለሙያዎቹ በዚህ የናሙና አይነት የተመረጡበት ምክንያት ደግሞ ከንባብ ክሂል ጋር የቆየ ቅርርብ ያላቸው፣ ከአጥኝው ጋር በየጊዜው ለመገናኘት የሚያስችል አካባቢ ላይ የሚገኙ ቀንቀውን በማስተማር እገልግሎት ያላቸው፣ ለመተባበር ፈቃደኛ የሆኑ ቢሆኑ የተሻለ ስለሚሆን ነው።

በዚሁ መሰረት ሁለት የመመረቂያ ፅሑፋቸውን በንባብ ክሂል ላይ የሰሩ የኤም.ኤ.ዲግሪ ያላቸውና አንድ የቢ.ኤ.ዲግሪ ያለው ቢጠቅላላው ሦስት አማርኛን ያስተማሩ መምህራን እስከ መጨረሻው በክፍለጣው ተግባር ተሳትፈዋል። በመጀመሪያ ወቅት በጥናቱ ታቅፈው የነበሩት ሦስት ኤም.ኤ ዲግሪና ሁለት ቢ.ዲግሪ ያላቸው አምስት መምህራን ነበሩ። ነገር ግን እስከመጨረሻው የተሳተፉት እንደተባለው ሦስቱ ብቻ ናቸው።

ሁለቱ በልዩ ልዩ ምክንያት ተሳትፏቸውን አቋርጠዋል። በዚህ የተነሳ ትንተናው የተካሄደው ሦስቱ መምህራንና አጥኝው ባደረጉት የዋያቄዎች ክፍፍል ላይ ነው። ከአራቱ ሦስቱ ብቻ የተሰማሙበትም አራቱ ከተስማሙበት ጋር አብሮ ተተንትኗል። ማለትም አንድ ጥያቄ አንድን ንዑስ ክፍል የሚመዝን ነው ለመባል የሦስቱን ስምምነት ካገኘ በትንታኔው ይታቀፋል፤ ስምምነቱ ከሶስት በታች ከሆነ በቸከሊስቱም ሆነ በመርሀ ትምህርቱ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክፍሎች ዝርዝር ውስጥ ባንዱም ሊታቀፍና ሊተነተን አይችልም ማለት ነው።

3.2.2. የትምህርት ቤቶችና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

3.2.2.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን ለመምረጥ ተራ የዕጣ ናሙና /Simple Randon Sampling/ ስልት ከተራ የዕጣ ናሙና አይነቶችም የዕጣ ቁጥሮች ሰንጠረዥ /a randon number table/ በመባል የሚጠራውንና እንደ ባቤ (1992)፣ ኩዋል (1996) ይበልጥ ተመራጭነት ያለውን በመጠቀም ለዋናው ጥናት 12 (50%) ለመከራው ሦስት ትምህርት ቤቶችን ለመምረጥ ተችሏል።

አመራረጡም ከክልሉ ትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሰረት አምስት አመትና ከዚያ በላይ 12ኛ ክፍልን ያስፈቱት 24 የመንግስት ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ፊደል ተራ ቅደም ተከተል ከ01 - 24 በመጻፍ በባቤ (1992)ና ኩዋል (1996) ማብራሪያና ምሳሌዎች መሰረት የዕጣ ቁጥሮች ሰንጠረዡን በመጠቀም በወጡበት ቅደም ተከተል መሰረት በመደርደር ነው። ይህ አይነቱ አመራረጥ እንደተመራማሪዎቹ ለትምህርት ቤቶቹ ሁሉ ዕኩል ዕድል የሚሰጥ ነው።

በዚሁ መሰረት ለዋናው ጥናት 1. 23 (ምኒልክ)፣ 2.09 (አየር ጤና) 3.13 (እንጦጦ)፣ 4.19 (ኮከብ ቆጣሪ)፣ 5.24 (ጥቁር አንበሳ)፣ 6.18 (ኮልፌ)፣ 7.20 (ወንዲራድ)፣ 8.04 (ከፍተኛ 20)፣ 9.10 (አዲስ ከተማ)፣ 10.16 (ከፍተኛ 4)፣ 11.06(ንፋስ ስልክ) እና 12.17 (ከፍተኛ 12) ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል።

በነዚህ ትምህርት ቤቶች ከ1986 - 1990 ባለው ጊዜ ውስጥ 12ኛ ክፍል ያስተማሩና ተቀጻሚ መምህር ሆነው የሰሩ የአማርኛ መምህራን መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል።

3.2.2.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በተመረጡት 12 ትምህርት ቤቶች የደረጃና /stage/፣ ተራ የዕጣ ናሙና በመጠቀም በየትምህርት ቤቶቹ ሰላሳ፣ ሰላሳ ተማሪዎች የላህይ አግባብነትን ለማጥናት የተዘጋጀውን መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል።

3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት የተተነተነው መረጃ የተሰበሰበው በጥናቱ በታቀፉት ትምህርት ቤቶች ከ1987 - 1990 በተሰጡት የሞዴል ፈተናዎች፣ በተለያዩ ተመራማሪዎች በአንብቦ መረዳት ፈተና ጥያቄዎች ሊመዘኑ የሚችሉ ከሂሎች በሚል ርዕስ የወጡ ሞዴሎችን/ቸክሊስቶችን እና የአማርኛ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን መሰረት በማድረግ አጥኝው ባዳበረው ቸክሊስት፣ በመጠይቅ፣ በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መርሀ ትምህርትና የመማሪያ መፅሐፍ ነው።

3.3.1 ቸክሊስት

በክለሳ ድርሳን ክፍል እንደተገለፀው ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተዘጋጁት መርሀ ትምህርቶች የተጠቀሱት የአንብቦ መረዳት ከሂል አላማዎች በጣም አጠቃላይ የሆኑ ናቸው። የንቁላን ከሂሎቹን ውክልና በነዚህ በጣም አጠቃላይ የሆኑ አላማዎች መሰረትነት መመርመር የሚቻል አልሆነም። ከዚህ የተነሳ ሌሎች ጥናቶች ለምሳሌ ዩሱፍ (1976)፣ ተሰፋሁን (1997)፣ አለሙ(1983) ኑሩ (1992) እንዳደረጉት በዚህ ጥናትም የተለያዩ ትምራዊና በተግባር የተሞከሩ ሞዴሎችን እንዲሁም የአማርኛን የንባብ ከሂል አላማዎች መሰረት በማድረግ በአንብቦ መረዳት ፈተና ሊመዘኑ የሚገባቸውን ከሂሎች የያዘ ቸክሊስት (የማረጋገጫ ዝርዝር) ከነ መፍቻው ለማዳበር ተሞክሯል (አባሪ 'ሀ'ን ይመለከቷል)።

ቸክሊስቱ ከተዘጋጀ በኋላ በአራት ለከሂሉ ቅርበት ያላቸው (በከሂሉ ላይ ምርምር ያደረጉ) ሞሁራን እንዲገመገም ተደርጓል። በሞሁራኑ የተሰጡትን አስተያየቶች መሰረት በማድረግ አስፈላጊው ማሻሻያ ከተደረገበት በኋላ በመከራው ጥናት /pilot study/ በዋናው ጥናት ባልታቀፉ ትምህርት ቤቶች ፈተናዎች የከሂሎች ውክልና መመርመሪያነት ተፈትሿል። ከመከራ ጥናቱ በኋላም ጥያቄዎችን በቸክሊስቱ ከተለዩት ከሂሎች ጋር በማዛመድ የተሳተፉት ባለሙያዎች የሰጡትን አስተያየት በማከል ማሻሻያ ከተደረገበት በኋላ ለዋናው ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት እንዲውል ተደርጓል። በመዳቢዎቹ በተደረገው ክፍፍል በቸክሊስቱ በ237 በመርሀ ትምህርቱ በ252 ጥያቄዎች ላይ ልዩነት ታይቶ የነበረ ሲሆን በ2.6.1 በተገለፀው መሰረት በተደረገው ውይይት ከቸክሊስቱ 168 ከመርሀ ትምህርቱ 214 ልዩነቶች በመቀነሳቸው

በየክሊስቱ መሰረትነት 1118፣ በመርሀ ትምህርቱ 1139 ጥያቄዎች ላይ ጥናቱ እንዲካሄድ ሆኗል።

3.3.2 የ12ኛ ክፍል የእግርኛ መርሀ ትምህርትና የመማሪያ መፅሐፍ

3.3.2.1 መርሀ ትምህርቱ

የመርሀ ትምህርት ይዘት የአንድ የችሎታ መለኪያ ፈተና ይዘት መሰረት ሊሆን እንደሚገባ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል። ከዚህ አኳያ ፈተናዎቹ ያላቸውን ዝምድና ለመመርመር ሲባልም በአንብቦ መረዳት ክሂል ነክ ሁለት ዝርዝር አላማዎች ይዘት ስር የተዘረዘሩ የክሂሉ ይዘቶችን በሙሉ በመውሰድ በመከራው ጥናት ለማዛመድ ተሞክሮ ነበር። ነገር ግን የመከራው ጥናት ውጤት እንዳመለከተው ባንድም ጥያቄ ሊወከሉ ያልቻሉ ክፍሎች ተሰተውለዋል። ካልተወከሉት ውስጥ በርግጥም ባለንበት ወቅትና ደረጃ ሊወከሉ የማይችሉ ዝርዝሮችም ያሉ ይመስላሉ (አባሪ ለ ተራ ቁጥር 13.6.1ንና 13.6.2ን ይበልጥ ይመለከቷል)።

በዚህና በመሳሰሉት ችግሮች የተነሳ ዋናውን ጥናት ለማካሄድ በአማራጭነት የተወሰደው በመከራ ጥናት በተወሰኑ ጥያቄዎች በአምስቱ አመታት ፈተናዎች ባንድ ጥያቄ የተወከሉትን ላይቀር በማካተት ሌሎቹን ግን "ሌሎች" በሚል አምድ ስር ባንድ በማጠቃለል ግዘጋጀቱ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ምሁራን የአንብቦ መረዳት ክሂሎች እንደሆኑ የገለፁት ነገር ግን በመርሀ ትምህርቱ ያልታቀፉ በፈተናዎቹ ጥያቄዎች ሲጥኑ የሚመደቡበት አንድ ሌላ ክፍል (አምድ) እንዲሁም የትኛውን ክሂል እንደሚመዝን ለመለየት ያስቸገረ ጥያቄ የሚመደብበት አንድ ክፍል በመመደቢያው ዝርዝር ውስጥ በየክሊስቱ እንደተደረገው ሁሉ እንዲጨመሩ ተደርጓል።

ይህ መሳሪያ በዚህ መንገድ ከተዘጋጀ በኋላ ቀደም ሲል የክሊስቱን የገመገሙ ምሁራን አደተቀቱት ተገቢው መሻሻያ ከተደረገበት በኋላ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት እንዲያገለግል ተደርጓል። በደሁኑና ናሙና የተመረጡት ባለሙያዎች የፈተናዎቹን ጥያቄዎች ያዛመዱትም ከየክሊስቱና ከዚህኛው በአባሪ ለ ከቀረበው የመርሀ ትምህርቱ የአንብቦ መረዳት ክሂል ይዘት ዝርዝሮች ጋር ነው ማለት ነው።

3.3.2.2 የመማሪያ መፅሐፉ

የ12ኛ ክፍል የእግርኛ መማሪያ መፅሐፍ በውስጡ የያዛቸው ምንባቦችና ያጠያየቅ ጀዎች ሌሎቹ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ናቸው።

3.3.3 መጠይቆች

3.3.3.1 የመምህሩ መጠይቅ

አራት ክፍሎች ያሉት መጠይቅ ተዘጋጅቶ በ3.2.2 እንደተገለፀው በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራንና በትምህርት ክፍሉ ተቀዳሚ መምህራን እንዲሞላ ተደርጓል። በርግጥ መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ ተቀዳሚ መምህር ሆነው 12ኛ ክፍል የማያስተምሩ የከፍተኛ 12ቱና የንፋስ ስልክ ብቻ ናቸው።

እንደተባለው መጠይቁ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ክፍል አንድ የመምህራኑን ዳራ፣ ክፍል ሁለት ለመፈተኛ መሳሪያነት የሚጠቀሙባቸውን ምንባቦች እንዴት እንደሚመርጡና የደብተ አግባብነትን ከፍ ለማድረግ የሚረዱ ስልቶችን ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆን አለመሆናቸውን የሚያሳውቁ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው።

ክፍል ሦስትና አራት ተመሳሳይ ጥያቄዎችን የያዙ ሲሆኑ የሚለያዩት በመመሪያና በአማራጮቻቸው ነው። የመጀመሪያው ከ1 - 20 የተዘረዘሩት የአንብቦ መረዳት ክሂል ክፍሎች በነሱ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አሰጣጥ የመካተት ደረጃቸው ምን ያህል እንደሆነ እንዲያመለክቱ የሚጠይቅ ነው። "በጣም ከፍተኛ"፣ "ከፍተኛ"፣ "መጠነኛ"፣ "ዝቅተኛ"ና "በጣም ዝቅተኛ" በማለት ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ አሰራራቸውን የሚያመለክተውን እንዲመርጡ የሚጠይቅ ነው። ክፍል አራት ደግሞ እነዚሁ ከ1 - 20 የተዘረዘሩ ክሂሎች መምህራኑ በሚያዘጋጇቸው ፈተናዎች ያላቸውን ውክልና የሚጠይቁ ናቸው።

በትንሹኔው ሂደት ግን በክፍል ሦስትና አራት የተጠየቁት 20 ጥያቄዎች ከባለሙያዎቹ ለየት ያለ ውጤት ትንተና ጋር ለማገናዘብ እንዲያስችልና የይዘት አግባብነት ደረጃውን ለመመርመር በሰባት ቁና ቁናና በ14 ንዑሳን ክፍሎች እንዲካተቱ ተደርጓል።

የዚህ መጠይቅ አቢይ አላማ መምህራኑ የሚያስተምሯቸውንና የሚፈትኗቸውን የአንብቦ መረዳት ክሂሎች፣ እንግንጉት ለመለየትና የይዘት አግባብነትን በተለይም የንዑሳን ክሂሎቹን ውክልና ለማስተማር ከተሰማቸው ትኩረት አኳያ ለመመርመርና ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት ነው።

ከመርሀ ትምህርቱና ከመግሪያ መፅሐፉ አኳያ የይዘት አግባብነትን ለማጥናት ቢሞከር ምናልባት የይዘት መጀፈን /content coverage/ አለመሸፈንን ለማጥናት ሊቻል ይችል ይሆናል። ብቁ የመሰኩ ተመራማሪዎች እንደሚያስረዱት ለተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚዘጋጁ መሳሪያዎች ለመምህሩና ለተማሪው በናሙናነት እንዲያገለግሉ እንጂ በራሳቸው በቂ እንዲሆኑ በማሰብ

አይደለም። ከዚህ አተያይ በተጨማሪ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው መሳሪያዎቹ ብዙ ጉድለት የሚታይባቸው ስለሆኑ በነሱ መነሻነት ብቻ የፈተናዎቹን የይዘት አግባብነት ለመመርመር ሙከሩ መታየት ያለበትን እውነተኛ ገጽታ በጥናቱ ማሳየት የሚቻል አይሆንም። ለምሳሌ የትኛው ክፍል በስፋት እንደቀረበና የትኛው አነስተኛ ቦታ እንደተሰጠው እነዚህ መሳሪያዎች አያመለክቱም። ነገር ግን ከመርህ አንፃር አንድ ትምህርት ለምን ያህል ጊዜ መሰጠት እንዳለበት አንድ መርህ ትምህርት ማመልከት ነበረበት፣ መርህ ትምህርቱና መማሪያ መፅሐፉ፣ ተገቢ ቅንጅት የሌላቸው ሆነው መገኘታቸውም ሌላው ችግር ነው፤ ባንዱ እያለ በሌላው የሌለው ትምህርት ብዙ ነው። በሳምንት...ቀርቶ በሴሚስተር የሚሰጠው ትምህርት እንኳ ተለይቶ አይታወቅም።

ስለዚህ ይህን ችግር ለማቃለል እንደ መፍትሄ የተወሰደው መምህራኑ ለየትኞቹ ክሂሎች ሰፊ ጊዜ፣ ለየትኞቹ ጥቂት ጊዜ ... እንደሚመድቡላቸው እንዲገልፁ ጠይቆ በማረጋገጥ የክሂሎቹን የውክልና ደረጃ ለመመርመር መሞከሩ ነው። ከፍ ብሎ እንደተወሳው ተገቢ ስልጠና ያገኙ መምህራን የተዘጋጁ መሳሪያዎች አገልጋይ መሆን እንደሌለባቸውና የራሳቸውን ጥረት በማድረግ በናሙና መሳሪያዎች ላይ ተጨማሪ ዝግጅት እያደረጉ የማያስፈልገውን በሌላ አስፈላጊ ይዘት እየተኩ (ካላማው ሳይወጡ) የማስተማር ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው በተለያዩ የመስኩ ተመራማሪዎች ተደጋግሞ የሚገለፅ ከመሆኑም በተጨማሪ የሚጠቀሙባቸው መርህ ትምህርቶችም ፡

> ... የሴሚስተር አከፋፈሉም የግሻሻያ ሐሳቦች ከሚያስፈልጋቸው ጥና ጥና ጉዳዮች እንዱ በመሆኑ መምህራን ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው ለአከፋፈሉ የሚሰግግውን ሁኔታ እንዲጠቀሙ ይጠበቃል። በተጨማሪም 1. በሲለበሱ ውስጥ ከበድ ከበድ ለሚሉትና ተጨማሪ መልመጃ ለሚያስፈልጋቸው ርዕሰ ትምህርቶች መምህሩ ልዩ ትኩረት መስጠት አለበት። 2. መምህሩ በሲለበሱ ውስጥ በተጠቀሱት "የክፍል ውስጥ ግስተማር ሥራ ክንውኖች" ላይ ብቻ ሳይወሰን እንዳለው ጉልታ፣ እንደ ተግሪዎቹ የፅድሚና የእካባቢ ሁኔታ እንዲሁም በቅርብ እንደሚያገኘው የማስተማሪያ መሳሪያ ወዘተ. ሌሎች ዘዴዎችን ለመመርመርና ከተዘረዘሩትም ውስጥ ለእካባቢ /ሁኔታ/ የማያመቸውን በሌላ ለመተካት ወይም ቅደም ተከተሉን ለመለወጥ ጥረት ግድረግ አለበት። እንዲሁም ሲለበሱ አጠቃላይ መምሪያ መስጠት እንጂ የየእካባቢውን የቋንቋ ችግር ሙኖታት አለመያሉ መጤን ይኖርቢታል።" ስለዚህ መምህሩ የዝግጅቱን ጫማ በመከተል በየእካባቢው ያሉ ተማሪዎች ያልባቸውን ችግር እየመረመረ ማስተማር ይጠበቅበታል። የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ /1984፣ መግቢያ/ 9-12/ በማለት መርሆውን አጠናክርላቸዋል።

እናም ከዚህ እውነታ ስንነሳ መምህሩ የትምህርቱን አላማዎች ሳይለቅ ከሚያቀርበው ትምህርት አንፃር የክሂሎቹን የውክልና ደረጃ ለመመርመር መሞከሩ ተገቢነት ያለው ነው ማለት ነው።

ለተጠቀሱት አላማዎች ከላይ የተዘረዘሩትን ክፍሎች የያዘው ይህ መጠይቅ በአጥኝው ከተዘጋጀ በኋላ በሦስት ባለሙያዎች እንዲገመገም ተደርጎ አስፈላጊው ማሻሻያ ከተደረገበት በኋላ በጨከራው ጥናት በጥናቱ ባልታቀፉ ትምህርት ቤቶች 10 መምህራን እንዲሞላ በማድረግ ተፈትሿል። በጨከራ ጥናቱ ከተፈተሸ በኋላም ከመምህራኑ መልሶችና አስተያየቶች በመነሳት አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበት ለቀናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት እንዲውል ተደርጓል። /ዝርዝሩን በአባሪ ሐ ይመለከቷል/።

ከላይ በተገለፀው መንገድ የተዘጋጀው መጠይቅ በጥናቱ ከታቀፉት 12 ትምህርት ቤቶች የ12ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ተሰራጭቶ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ በተመለከቱት የመምህራን ቁጥር ተሞልቶ ተመልሷል።

ሰንጠረዥ 1፤ የመምህራን መጠይቅ ስርጭት፣ ተሞልተው የተመለሱ ቁጥርና መቶኛ፤

የት/ቤቱ መለያ ቁጥር	የትምህርት ቤቱ ስም	የተሰራጨው ቁጥር	የተመለሰው ቁጥር	መቶኛ (%)
23	ሚኒሊክ	3	2	66.67
09	አየር ጤና	4	3	75
13	እንጦጦ	4	2	50
19	ኮከበ ፅባህ	2	2	100
24	ጥቁር እንበሳ	4	4	100
18	ኮልፌ	2	2	100
20	ወንዲራድ	4	4	100
14	ከፍተኛ 20	2	1	50
10	አዲስ ከተማ	5	5	100
16	ከፍተኛ አራት	2	2	100
06	ንፋስ ስልክ	2	1	50
17	ከፍተኛ 12	2	2	100
	ድምር	36	30	83.33

ሰንጠረዥ 1 እንደሚያመለክተው በ "12 "ቱ ትምህርት ቤቶች ከተሰራጨው 36 መጠይቅ ውስጥ ተሞልቶ የተመለሰው ሰላሳው ወይም 83.33% የሚሆነው ነው። ይህ ጥናት በመረጃነት የሚገለገልባቸውም እነዚህን ተሞልተው የተመለሱ ሰላሳ መጠይቆች ነው ማለት ነው።

ሰንጠረዥ 2፤ የናሙና መምህራኑን ፆታ፣ የት/ደረጃ፣ የሰለጠኑበትን ትምህርት፣ ያገለገሉበትን ዘመን ወዘተ. የሚያሳይ፤

መለኪያ	ፆታ		የትምህርት ደረጃ				የስልጠናውን የት/ዓይነት							የሰሩ መደብ የነበ			የአገልግሎት ዘመን								አማርኛን የስተማርሁ የው የክፍል ደረጃዎች	
							አዘጋጅ				ንዑስ						አዲሙቀጥ		ከአዲሙዋ			ጠቅላላ አገልግሎት					
መለኪ	ወንድ	ሴት	ዲፕሎ	የመጀ ዲግሪ	የድህ ዲግሪ	ሌሎች	አማ	የን	ሳይ ንስ	የአካ ዳሚ	አማ	ሳይን ስ	ሌሎ ች	አማ	ሳይ	ሌሎ	ከሰባ በላይ	ከ30 እስከ	ከሰባ በላይ	ከ30 እስከ	ከአስ ተማሪ	ከ30 በታች	ከ31 እስከ	ከ41 እስከ	ከአስ ተማሪ	ከ 1 እስከ 12	ከ 13 እስከ 12
መጠኑ	19	1	1	1	17	1	18	2	1	1	1	18	17	18	1	1	15	4	1	15	1	4	4	12	8	19	1
%	95.0	05.0	5.00	5.00	85	5.00	90.0	10.0	5.00	5.00	10	90.0	85.0	90.0	5.00	5.00	75	20	5.0	75.0	05.0	20.0	20.0	60.0	40.0	95	05

ሰንጠረዥ 2 እንደሚያመለክተው መጠይቁን በመሙላት ከተሳተፉት ውስጥ ፃያ አምስቱ /83.33%/ ወንዶች፤ አምስቱ /16.66%/ ሴቶች ናቸው። የትምህርት ደረጃቸው "27 "ቱ /90%/ ቢኢ፤ አንዱ ኤም.ኢ. ዲግሪ አላቸው የቀሩት ሁለቱ 12 + 2 እና 12 + 3 የሚሉትን አማራጮች የመለሱ ናቸው። የነፃ አራቱ የመጀመሪያ ዲግሪ በአማርኛ ሲሆን የሁለቱ ፔዳጎጂ፤ የአንዱ ቲዎሎጂ ነው። የአንደኛው የመጀመሪያ ዲግሪው አልተገለፀም ሁለቱ ዲግሪ አልያዙም። ከነዚህ ውስጥ አስሩ በንፁህ ትምህርትነት እንግሊዝኛን ያጠኑ ናቸው። ቲዎሎጂና ፔዳጎጂ ያጠኑት በንፁህ ትምህርትነት አማርኛን ያጠኑ ናቸው።

የእፍ መፍታ ቂንቂቲው የነፃ አምስቱ /83.33%/ አማርኛ ነው። የአንዱ /3.33%/ እርምኛ ሲሆን የአራቱ /13.33%/ ትግርኛ ነው።

ከ...ዱን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ከ15 - 20 ዓመት 46.66ፐ፣ 21 - 24፣ 13.33ፐ፣ ከ25 - 30 ዓመት 13.33ፐ፣ ከ15 ዓመት በታች 26.6ፐ የሚሆኑት አገልግለዋል።

አዲስ አበባ ውስጥ በማስተማር ከ10 ዓመት በላይ ያገለገሉ 70ፐ ሲሆኑ ከ3-10 ዓመት ያገለገሉት 30ፐ የሚሆኑት ናቸው።

ከዚህም መረጃ መምህራኑ በትምህርት ደረጃ ብዙዎቹ ዲግሪ ያላቸው፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚያስተምሩት ቋንቋ የሆነ፣ በጠቅላላ አገልግሎትም ሆነ አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ በማስተማር ብዙ ዓመት የሰሩ መሆናቸውን እንረዳለን። ስለዚህ የተማሪዎችን ዳራ ለማወቅ ምን ማስተማርና አለማስተማር እንዳለባቸው ለመለየት ... ፈተናዎችን በተገቢ መንገድ ለማዘጋጀት አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ለመፈለግ ለምሳሌ በየቤተ መጻሕፍቱ የተለያዩ ከሂሎችን ለመመዘን የሚያስችሉ ምንባቦችን ከተለያዩ መጻሕፍት፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች ለመፈለግ፣ እንዲሁም እነ ኦልደርሰን (1995)ና ሌሎች ተመራማሪዎች እንደሚመክሩት በፈተናዎች የደበት አግባብነት ደረጃ ላይ ግንቢ አስተያየት ለመስጠት የሚያስፈልጉ የትምህርት ደረጃ፣ የሰራ ልምድና የመሳሰሉት ጠቃሚ ግዕታዎች ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል ማለት ነው።

1.3.3.1 የተማሪው መጠይቅ

ይህ መጠይቅ የላይ አግባብነትን ከተማሪዎች እንግር ለመመርመር አላማ የተዘጋጀ ነው። ጥያቄዎቹ የተመዘኑትን ከሂሎችና ከሂሎቹን ለመመዘን የተመረጡትን ምንባቦችና ያጠያየቁ ጽሁፎች እንዲሁም የተፈቀደውን ጊዜ፣ ትዕዛዞቹንና የመሳሰሉትን የሚመለከቱ ናቸው። ይህ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው የተማሪዎቹን ዳራ ሁለተኛው ተማሪዎቹ በተፈኑት የሞዴል ፈተና የእንብቦ መረዳት ክፍል ላይ ያላቸውን አመለካከትና ስሜት ለማወቅ የተጠየቁ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው። ሁለቱም ምርጫ ሰጭ ሲሆኑ በተለይ ለክፍል ሁለት የእምስት ነጥብ መልስ መስጫ መለኪያዎች /ስኬልስ/ ቀርበዋል። - "በጣም አስማማለሁ፣ አስማማለሁ፣ ለመወሰን እቸገራለሁ፣ አልስማማምና በጣም አልስማማም" የሚሉ /ዝርዝሩ በአባሪ ሙ ይመለከቷል/።

አሞላሉም ቀደም ብሎ ከየትምህርት ቤቶቹ ምክትል ርዕሳነ መምህራን ጋር በተደረገው ውይይትና ስምምነት መሰረት በጥናቱ የታቀፉት ተማሪዎች የአማርኛንና የእንግሊዝኛን ሞዴል ፈተናዎች ተፈትነው እንደጨረሱ ስለአላማውና ስለአሞላሉ መግለጫና ማብራሪያ ከተደረገላቸው በኋላ ነው። ገለፃና ማብራሪያ ከተደረገላቸው በኋላ ሁሉም (360) ሞደዎች በፈቃደኝነት ሞልተው የመለሱ ቢሆንም ከተመለሱት ውስጥ የአራቱ አሞላል የተሟላ ሆኖ ባለመገኘቱ ከጥናቱ ውጭ እንዲሆኑ ተደርገዋል። በዚህ የተነሳ ትንተናው ከ356ቱ መላሾች በተገኘው መረጃ ላይ ብቻ እንዲካሄድ ሆኗል።

በመጠይቁ የመጀመሪያ ክፍል ከቀረበው የተማሪዎችን ዳራ ጠያቂ ጥያቄዎች ከተገኘው መረጃ ማረጋገጥ እንደተቻለው (ሰንጠረዥ 3 እንደሚያመለክተው) መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ ወንዶቹ 203 (57.02%)፣ ሴቶቹ 153 (42.98%) ናቸው።

ሰንጠረዥ 3፣ የናሙና ተማሪዎች ፆታ፣ዕድሜና የእና መፍቻ ቋንቋ የሚያሳይ፤

መለያዎች	ፆታ		ዕድሜ				የእና መናገ ቋንቋ				
መልስ	ወንድ	ሴት	16 እና ከዚ በታች	ከ17 18 ዓመት	ከ19 20 ዓመት	ከ20 ዓመት በላይ	አማርኛ	ኦሮምኛ	ትግርኛ	ጉራጊኛ	ሲዳምኛ
ብዛት	203	153	14	242	88	12	337	6	5	4	1
%	57.3	42.9	3.93	67.79	24.72	3.37	94.66	1.94	2.24	1.12	0.2

ዕድሜያቸው 14ቱ (3.93%) 16 ና ከ16 በታች፤ 88ቱ (24.72)፤ ከ19 - 20 ዓመት፤ 12ቱ (3.37%) ከ20 ዓመት በላይ ሲሆኑ "242 "ቱ (67.79%) ከ17 - 18 ዓመት ባለው አማራጭ ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

እና መፍቻ ቋንቋቸው የ8ቱ (2.24%) ትግርኛ፣ 6ቱ (1.94%) ኦሮምኛ፣ 4ቱ (1.12%) ጉራጊኛ፣ 1ቱ (0.27%) ሲዳምኛ ሲሆን የ337 (94.66%) አማርኛ ነው።

ባጠቃላይ ሰንጠረዥ 3 እንደሚያሳየው በጥናቱ የታቀፉት ከፆታ አንፃር በመጠነኛ ቁጥር ወንዶች ቢበልጡም ልዩነታቸው ያልጎላ ነው። በዕድሜ ብዙዎቹ ከ17 - 18 ባለው ክፍል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። የ94.66% የእና መፍቻ ቋንቋ አማርኛ ነው።

ከዚህም በላይ የሚተነተነውና የሚብራራው መረጃ ሁለቱም ፆታዎች የተወከሉበት፣ የቀረቡ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ፣ የእና መፍቻ ቋንቋቸው በከፍተኛ ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ የጣሪያ የተገኘ ነው ማለት ነው።

፣፩ የመረጃ አተናተን ዘዴ

የመረጃ አተናተን ሂደቱ ሁለቱንም ማለትም እይነታዊንም /qualitative/ መጠናዊንም /quantitative/ በመጠቀም የሚካሄድ ነው። ዝርዝር ሂደቱም ምንባቦችንና ያጠያየቅ ዘዴዎችን መነሻ በማድረግ፣ የፈተናዎቹን ጥያቄዎች መከፋፈል (item classification)ና መጠናቸውን በድግግሞሽና በመቶኛ መግለፅ፣ በመምህሩና በተማሪው መጠይቆች የተገኙ ምላሾችን ወደ ቁጥር በመለወጥ እንዲሁ እንደፈተናዎቹ ጥያቄዎች በግላጭ አስታትስቲክስ (በድግግሞሽና /frequency/ በመቶኛ) በመግለፅ መተንተን ላይ የተመሰረተ ነው።

ምዕራፍ አራት

የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

4.1 የዕዙት አግባብነት

4.1.1 የምንባቦቹ አመራረጥ

አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የሚመረጡ ምንባቦች አግባብነት ያላቸው እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ መርሆዎችና ቴክኒኮች መኖራቸውን በክለሳ ድርሳን ክፍል መገለፁ ይታወሳል። ከነዚህ መርሆዎችና ቴክኒኮች ውስጥ የሚመረጡት ምንባቦች የተለያዩ ከፎሎችን ለመመዘን የሚያስችሉ፣ ተፈታኞቹ ቋንቋውን ሲማሩ የተዋወቋቸው ነፀብራቆች፣ እንዲሁም ከትምህርት ውጭ በገሀዱ አለም ሊያጋጥሟቸው የሚችሏቸው የዕሑፍ አይነቶች መኪሎች ሆነው በዕዙት የተለያዩ እጠር እጠር ያሉና ብዛት ያላቸው (እንደማድሰን 1983፣ ከ1 - 5 የሚሆኑ)፣ ትክክለኛ /Authentic/ ቢሆኑ አግባብነት ያለው ይሆናል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ጊዜዝ (1995) ቱሾመ (1995)፣ ዌየር (1993)፣ ማድሰን (1983)፣ ባችማንና ፖልመር (1997)፣ ካንድሊን (1994)።

ከነዚህ መሰረታዊ የምንባቦች አመራረጥ መመዘኛዎች አኳያ ለጥናት የተመረጡት ትምህርት ቤቶች የሞዴል ፈተናዎች የምንባቦች አመራረጥ ሲመረመር አዎንታዊም አሉታዊም ነጥቦች ያሉትው ሆነው ተገኝተዋል።

ባጠቃላይ በንጠረዥ 4 እንደሚታመለክተው በአራቱ ዓመታት ውስጥ 113 ምንባቦች የተመረጡ ሲሆን በ1987 ዓ.ም. በ10 ትምህርት ቤቶች 26፣ በ1988 ዓ.ም. በ11 ትምህርት ቤቶች 29፣ በ1989 ዓ.ም. በ11 ትምህርት ቤቶች እንዲሁ 29፣በ1990 ዓ.ም. በ12 ትምህርት ቤቶች 29 ምንባቦች አንብቦ መረዳትን ለመፈተናቸው አገልግለዋል።

ሰንጠረዥ 4 ፤ በሞዴል ፈተናዎቹ እንብቦ መረዳትን ለመፈተኛነት የተመረጡ ምንባቦች የጽሑፍ ዓይነት ብዛትና መቶኛ፤

ተ.ቁ	ዓመተ ምህረት	ከፈጠራዊ						ከኢፈጠራዊ		መደቡ ካልታወቀ		ጠቅላላ
		ከዜያካር	ከልቦለድ		ከጉዞም	ድምር	፭		፭		፭	
			ከረጅም	ከአጭር								
1	1978	1		1	10	12	46.2	13	50	1	3.8	26
2	1980	1		7	11	18	62.1	5	17.2	6	20.6	29
3	1980	1		8	11	19	65.5	3	10.3	7	24.13	29
4	1981	1		8	12	18	62.1	5	17.2	6	20.6	29
ጠ/ድምር		4	22	4	44	67	59.3	26	23.0	20	17.7	113

ሰንጠረዥ 4 እንደሚያመለክተው ከጠቅላላው 113 ምንባቦች ውስጥ 59.3፭ ከፈጠራዊ ጽሑፎች 26፭ ከኢፈጠራዊ የተወሰዱ ናቸው። 17.7፭ የሚሆኑት ከየትኛው የጽሑፍ ዓይነት የሚመደቡ እንደሆኑ ለመለየት ያስቸገሩ ናቸው። ከፈጠራዊ የጽሑፍ ዓይነቶች ከተወሰዱት ውስጥ አርባ አራቱ/38.9፭/ ግጥሞች ናቸው።

ቀደም ብሎ ሲገለፅ ለመፈተኛ መሳሪያነት የሚመረጡ ምንባቦች ተማሪዎቹ በክፍል ትምህርት የተቀመጧቸው የጽሑፍ ዓይነቶች ንፅብራቆች ቢሆኑ አግባብነት ያለው እንደሆነ ተገልጿል። ከዚህ አኳያ ሲታዩ የፈተናዎቹ ምንባቦች በተወሰነ ደረጃ አምንታዊ መልክ ያንፀባርቃሉ። ምክንያቱም በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡ ምንባቦችም ከፈጠራዊ ጽሑፍ አይነቶች - ከግጥም፣ ከረጅም ልቦለድና፣ ከአጭር ልቦለድ፤ ከኢፈጠራዊ ፅሑፎች ከለዩ ልዩ መጻሕፍትና ሙጣጥፎች የተወሰዱ ናቸው (የአማርኛ መማሪያ፣12ኛ ክፍል፣1984)። ከነዚህ በፈተናዎቹ ያልተወከለ አጭር ልቦለድ ነው። አሉታዊ ሆኖ የሚታየው የአጭር ልቦለድ አለመወከል ብቻ ነው ማለት ግን አይደለም። በአወካከል አለመመጣጠንም ይታያል። በመማሪያ መጽሐፉ ፈጠራዊ የሆኑትና ያልሆኑት በቁጥር ተቀራራቢ ናቸው። እንዱ ባራት ሌላኛው በአምስት ምንባቦች የተወከሉ ናቸው። በፈተናዎቹ የሚታየው ግን ወደ ፈጠራዊ የማድላት አዝማሚያ ነው። ኢፈጠራዊ ጽሑፎች የተለያዩ የእንብቦ መረዳት ክሂሎችን ለማስተማርም ሆነ ለመመዘን ብቃት የሚያንሳቸው ጊዜ አለ፣ ከሚለው አተያይ የመነጨ አድሏዊነት ቢሆን በተወሰነ መልኩ አምንታዊ የባከቸሽ ውጤት ሊኖረው ይችል ነበር። ነገር ግን ሆነ ተብሎ የተደረገ እንዳይደለ የሚያመለክቱ ሌሎች ሁኔታዎች ስላሉ በታሰበው መልኩ ለመረዳት ያስቸግራል።

ከነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ በተለያዩ የአደራረስ ስልት የተፃፉ ጽሑፎችን አስባጥሮ ለማቅረብ አለመሞከሩ እንዱ ነው። ብዙዎቹ ለመፈተኛነት የተመረጡት ምንባቦች በትረካ

ስልት፤ ጥቂቶቹ በገላጭ የተሣሉ ናቸው። በተለይ በአመዛዛኝ /አከራካሪ/ስልት የተሣሪ ምንባብ በፈተናዎቹ ውስጥ ማግኘት የሚቻል አልመሰለንም። በዚህ ስልት የተሣሉ ጽሑፎች በተለይ ከፍተኛ የማገናዘብ ችሎታን የሚጠይቁ ክሂሎችን ለመመዘን አመች ናቸው። ነገር ግን በፈተናዎቹ ትኩረት አልተደረገበትም። በተራኪና በገላጭ ስልት በተሣሉት ነው ለመመዘን ሊሞከር የሚሰተዋለው። በነዚህ ስልቶች በተሣሉ ምንባቦች ብቻ የተለያዩ ክሂሎችን ለመመዘን፤ በትምህርት ቤት የተቸወደቸውንና በገሃዱ ዓለም ሊያጋጥሟቸው የሚችሏቸውን የጽሑፍ አይነቶች ለመወከልና ቄየር (1993)ና ሂዩዝ (1995) እንዳሉት አምንታዊ የባክዋሽ ውጤት ለማምጣት የሚቻል መሰሉ አልታየንም።

ከዚህ በተጨማሪ አብዛኞቹ ምንባቦች ከተወሰኑ ጽሑፎች ተደጋግመው የሚወሰዱ መሆንም ተገቢነት የሚኖረው፤ ከላይ የተባለውን በጎ ተጽዕኖ ማስገኘት የሚችል አይመስልም። ለምሳሌ በ1988 ከሌዲስ አለግየሁ ፍቅር እስከመቃብር ሁለት፤ ከፍቅረ ድንግል፤ ከቡስካው በስተደርግ፤ሁለት፤ ከፀጋዬ ገብረ መድኅን፤ አሳት ወይ አበባ፤ አምስት፤ ምንባቦች ተመሰደዋል። በተለያዩ ጉዞታት ተደጋግመው የሚወሰዱት ከነዚህና ከደበበ ሰይፉ፤ የብርሃን ፍጥር፤ ከበአሉ ግርማ የተለያዩ ስራዎችና ከጄረዳ ብዕር ነው። ኢልቦለድ የሆኑት ምንባቦች ደግሞ ከአማረ ማሞ ፤ የቁልም ጠብታ፤ከዳኛቸው ወርቁ የጽሑፍ ዋበብ መመሪያና ቀደም ሲሉ ታሪክ ነክ ጽሑፎች ነው። ቀሞሉ ከቀረበው ሰንጠረዥ ማስተዋል እንደሚቻለው ከመጽሔቶች፤ከጋዜጦችና ሌሎች ወንኖና መጣጥፎች ... የተወሰዱት ውሱን ናቸው። ይህም የሚያሳየው አመራረጡ ተገቢነት የሚንድለው፤ የመምህራኑ ሰፊ የሥራ ልምድ ያበረከተው ነገር የለለ የሚመስል መሆኑን ነው።

ሰንጠረዥ 5፤ በሞዴል ፈተናዎቹ እንብቦ መረዳትን ለመፈተሸነት የተመረጡ ምንባቦች የተወሰዱባቸው ምንሬጮች ፤

ሌ	የጽሑፍ ዓይነት	ኢድ ክላ	ኢድ ባሌ	ከኢድ ወይ ፖሊሲ	ከመ ፀ ሌት	ከንባ ክር	ከወግ	ከመሣሪያ መጽሔ	ከሌሎ ሌደ	ከን ጥም	ከኢ.ሌ.ሎ ሌድ መጽሔ	ከሌሎ፣	ጎሌታ ወቀ ምጋጭ
ሰሰ፣	፲፰	፩			፩	፩			፩	፲፬	፪	፩	፱
ሰሰፀ	፲፫	፩							፩	፲፩	፩	፩	፮
ሰሰፀ	፲፩	፩						፩	፩	፲፩	፩		፯
ሰሰፀ	፲፩				፪				፮	፲፪	፩		፮
	ጥም	፩			፭	፩		፩	፳፪	፵፬	፱	፪	፳፰

በየፈተናው የታቀፉት ምንባቦች ብዛትም በ1987 በትምህርት ቤት 19 የተሰጠን ባለአንድ ምንባብ ፈተና ሳይጨምር ከፍተኛው ሶስት ዝቅተኛው ሁለት ነው። በእያንዳንዱ ጉሙት የታየው እውነታ ተመሳሳይነት ያለው ነው። ለምሳሌ በ1987 ሰባት ፈተናዎች ሦስት ሦስት፤ ሁለት ፈተናዎች ሁለት ሁለት፤ በ1988 እና በ1989 በተመሳሳይ ሁናቴ ሰባት ፈተናዎች ሶስት ሶስት፤ የቀሩት አራት አራት ፈተናዎች ሁለት ሁለት ምንባቦችን ተጠቅመዋል። ለየት

የሚለው የ ' 1990' ነው። በዚህ ዓመት ሰባት ፈተናዎች ሁለት ሁለት፣ አምስት ፈተናዎች ሶስት ሶስት ምንባቦችን ነው የተጠቀሙት፤ ሁለት የተጠቀሙት ይበልጣሉ ማለት ነው።

ከትምራሮ መርሆዎችና ከይዘት እግባብነት አኳያ ከታየ በአሉታዊነት ከመፈረጅ የሚድን አይደለም። ከፍተኛው የምንባብ ቁጥር (3) የዝቅተኛው መነሻ የሆነ ነው። ብዙ ምንባቦችን ለማካተት ከሚኖረው የወረቀትና የመሳሰሉት ችግሮች አንፃር ከታየ ደግሞ ለትችት የመጋለጥ ደረጃው ሊቀንስ ይችላል። ሆኖም መምህራኑ እንድም ቦታ ችግር እንዳለባቸው ያወሱት ነገር ስለሌለ ይህን ምክያት እንደምክንያት ማንሳቱ ላያዋጣም ይችላል።

እነዚህ በየትምህርት ቤቶቹ ለመፈተኛ መሳሪያነት በየአመቱ የተመረጡ ከ2-3 የሚደርሱ ምንባቦች በ1990 በትምህርት ቤት 09 ከተመረጡት ሁለት ምንባቦች በቀር በይዘት ከሞላ ጎደል የተለያዩ ናቸው። ነገር ግን አብዛኛዎቹ አጠቃላይ /universal/ ስለሆነ ጉዳይ የሚያነሱ ናቸው። በ1988 የቀረቡት ምንባቦች ለምሳሌ ስለምኞት፣ ፍቅር፣ ጥል፣ ጋብቻ፣ መዘንጋት፣ ችግር፣ ሙሉ ምድራዊ ገጽታ የሚያነሱ ሲሆኑ፣ የ'1989'ኙቹም ስለ ዝሙት፣ ኤድስ፣ ቅናት፣ የንባብ ምንነት፣ ምቾት፣ እውር ልቦለድ፣ራስን ማወቅ፣ ትውፊትና ፈጠራ፣ ምኞት የሚገልጹ ናቸው። የ1990ኙም እንዲሁ ስለሴቶች ባሕሪ፣ ስለእጹ ቴምድርስ ስብዕና፣ ስለጥንቱ ጋብቻ፣ ለአንድ አላማ ሲኖሱ ስለሚታገሙ ችግሮች፣ ስለምኞት፣ ስለኪነጥበብ ሰዎች ድክመት፣ ስለታል ኪዳን፣ ስሊታታሪ ሰዎች፣ ስለሕሊና/እእምሮ/ታላቅነት፣ ስለሃጣብ ያለመለዋወጥ የሚያመጣው ችግር፣ ስለነኑፍ ሰዎች፣ ስለፍቅርና ስለሞት የሚያወሱ ናቸው።

ከርግጥ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው በ1990 በትምህርት ቤት 09 አንድ በግጥም አንድ በዝርው የቀረቡ ምንባቦች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ናቸው። ሁለቱም የሕሊናን/የአእምሮን/ ታላቅነት የሚያመለክቱ ናቸው። ከዚሁ ጋር የሚገናኝ ጥሩ ባልሆነ ተግባርነቱ ግን የሚነሳ በ1989 በትምህርት ቤት 17 በ1988፣ በትምህርት ቤት 14 የተሰጠን የሞዴል ፈተና እንዳለ መጠቀም የተነሳ በዚህ ፈተና ያገለገሉ ሦስት ምንባቦችና ከምንባቦቹ የወጡ ጥያቄዎች እንደገና እንዲያገለግሉ መደረግ ነው። ይህ ዓይነት ተግባር የሚያስከትለው ጉዳት መብራራት የሚያስፈልገው አይደለም፤ ለማንም ግልጽ ሊሆን የሚችል አሉታዊ ነን ያለው ነው። ይኸ ፈተናን የመድገም አባዜ በዚህ የተገታ አለመሆኑ ነው የሚገርመው። በተለይ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የተጠቀመባቸውን ምንባቦችና ከምንባቦቹ የወጡ ጥያቄዎች መልሶ መጠቀም በብዙ ትምህርት ቤቶች የተለመደ ይመስላል። በብዙ ሞዴል ፈተናዎች የታየ እውነታ ነው። ለምሳሌ በ1987፣ትምህርት ቤት 06 በምንባብ ሁለትነት፣ትምህርት ቤት 19፣በምንባብ አንድነት፣ ትምህርት ቤት 14 በምንባብ ሁለትነት፤ በ1988፣ ትምህርት ቤት 17፣ በምንባብ አንድነት፤ 1989፣ትምህርት ቤት 23፣ በምንባብ አንድነት፤በ1990፣ ትምህርት ቤት 13፣ በምንባብ ሁለትነት፣ ትምህርት ቤት 23 በምንባብ ሦስትነት፣ ትምህርት ቤት 06 በምንባብ

ሁለትንት የተጠቀሙባቸው በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና በተለያዩ ዓመታት የተሰራባቸውን ነው። ጥያቄዎቹም ከዚያው የተወሰዱ ናቸው።

በተመራማሪዎቹ ለምሳሌ በሂዩዝ (1995) ከተገለጹት መርሆዎች አኳያ ሲታይም እንዲህ በየቢቱ ጎላ ከሚሉት ፈተናዎች ቀርቶ ተማሪው ቀደም ብሎ ሊያነበው ይችላል ተብሎ ከሚገመት ጽሑፍ እንኳ ለፈተና ምንባብ መምረጥ ተገቢ አይደለም። ለመፈተኛነት የሚመረጡ ምንባቦች ተፈታኞች ሁሉ በፈተናው ላይ በእኩልነት የሚያገኟቸው መሆን ይኖርባቸዋል። ከዚህ አተያይ አኳያ ሲታዩ የሞዴል ፈተናዎቹ የተጠቀሙባቸው ምንባቦች በሌላ ፈተናዎች የተሰራባቸው ብቻ ሳይሆኑ ከልዩ ልዩ መጻሕፍትና ሌሎች ጽሑፎች የተወሰዱት ራሳቸው ተገቢነት የሚጎላቸው ናቸው ማለት ይቻላል። ብዙዎቹ ምንባቦች የተወሰዱት፣ከብዙ አመታት በፊት ገበያ ላይ ከዋሉና በየትምህርት ቤቶቹ ቤተመጻሕፍት ሊገኙ ከሚችሉ ተማሪው እንደልብ ሊያገኛቸውና ሊያነባቸው ከሚችላቸው "የአሮጌ" ስራዎች ነው ማለት ይቻላል። ከዚህም በዚህ አቅጣጫ እንብዛ መረጻትን ለመፈተን መምህራኑ የሚከተሉት የምንባቦች አመራረጥ መንገድ አለ ታዊ ሙልክ የሚታይበት ነው ብሎ ማጠቃለል የሚቻል ይመስለናል።

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው እንብዛ መረጻትን ለመፈተን በየትምህርት ቤቶቹ የተመረጡት ምንባቦች በአብዛኛው በይዘታቸው የተለያዩ ቢመስሉም አጠቃላይ ስለሆነ ጉዳይ የሚያነሱ በመሆናቸው ዞር ዞር ወደተወሰነ አቅጣጫ ያዘነበሉ፣የቀሩትን የዘነጉ ከመሆን ሊያልፉ የቻሉ አይመስሉም። የተለያዩ ተመራማሪዎች የሚመክሩት ግን የተለያዩ የዕውቀት መስኮች/በጣም ሙ ያዊ ያልሆኑ/ላይቀር የተካተቱበት ቢሆን ተመራጭነት እንዳለው ነው (ክላፓም 1997፣ ሂዩዝ፣ 1995፣ ዌየር 1993...)። በፈተናዎቹ ተማሪዎቹን ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ በአማርኛ የሚዳሉ የጽሑፍ ጎደኑቶች ስላልተወከሉ በዚህም ጠንካራ ገጽታ ሊታይ አልቻለም። በተለይም በቅ ምንባቦች ቀደም ካሉ ጽሑፎች የተወሰዱ መሆን አሁን ያሉ ያግባሩ መንገዶችንና የወቅቱን አንብቦ መረጻት መቻል አለመቻላቸውንም ማረጋገጥ የሚያስችል ነው? የሚለው ራሱ ሊ ያወያይ የሚገል ይመስላል።

የምንባቦች አመራረጥን ተገቢ ከሚያሰኙት መመዘኛዎች ሌላው የምንባቦቹ ርዝመትና እጥረት ነው። ቀደም ሲል አጠር አጠር ያሉ ቢሆኑ መልካም እንደሆነ ተወስቷል። ይህ አጥረት ግን ውስን ያለው ነው። እንደግደሰን (1983) ለምሳሌ ዝቅተኛው ምንባብ ከ150 ቃላት ባያንስ ጥሩ ነው (በፈተናዎቹ ምንባቦች 150 ቃላት ግማሽ ገጽ አካባቢ ይሸፍናሉ።) እንደ ሂዩዝ (1995) ደግሞ በተለይ የአስሳ ክሌሎችን ለመፈተን 2000 ቃላት አካባቢ ያላቸው ምንባቦች ተገቢነት አላቸው። የነሱን እንዳለ እንቀበል ባይባልም አምንታዊ አለመሆኑን ለማስተባበል ግን የሚቻል አይደለም። ቀጣዩ ስንጠረዥ እንደሚያሳየው አጥሪታቸው ከሚገባው በላይ ነው ማለት ይቻላል። ከአንድ ገጽ በላይ የሆኑት በ1989፣ 4፤ በ1988፣ 4፤ በ1987 ፤1 ብቻ ናቸው። በ1990 አንድም የለ። በሌላ መልኩ ጥቂት መስመር (ከግማሽ ገጽ በታች) ያላቸው ምንባቦች በዛ ያሉ ናቸው። በ1990 ዓ.ም፣12፤በ1989 ዓ.ም፣7፤ በ1988፣8፤ በ1987፣13፤ በጠቅላላ 40 ናቸው።

ሰንጠረዥ 6፤ በሞዴል ፈተናዎቹ ከአንድ ገጽ በላይ፣ከግማሽ እስከ
አንድ ገጽና ከግማሽ ገጽ በታች የሚሆን ርዝመት
ያላቸው ምንባቦች ብዛትና መቶኛ፤

ቁም	ዩኑቨርሲቲው ብዛት	ከአንድ ገጽ በላይ		ከግማሹ-አንድ ገጽ		ከግማሽ ገጽ በታች		ጠቅላላ	
		ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ
1987	10	1		12		13		26	23
1988	11	4		17		8		29	25.66
1989	11	4		18		7		29	25.66
1990	12	-		17		12		29	25.66
ድምር		9	7.96	64	56.64	40	35.39	113	100

በነዚህ ምንባቦች መሣሪያነት ሁሉንም የእንብቦ መረዳት ክሂሎች በተለይም ሰፋ ያለ ምንባብ የሚያስፈልጋቸውን በአግባቡ ለመመዘን የሚቻል አይመስልም።

ከአንድ ምንባብ ሊወጡ የሚገባቸው ጥያቄዎች ቁጥርም ከግምት ውስጥ ሊገባ ይገባቸዋል። ይኸም ከምንባቡ ርዝመትና ከሚመዘነው ክሂል ጋር የተያያዘ ቢሆንም ከመርህ አንጻር ተመራጭነት ያለው ካንድ ምንባብ የሚወጡ ጥያቄዎች ብዙ ባይሆኑ ነው። አንዳንዶች ለምሳሌ ግድሰን (1983) እንደሚሉት በ100 ቃላት ከሶስት ጥያቄ በላይ ባይወጣ ጥሩ ነው።

ከዚህ አኳያ በጥናቱ የታቀፉት ትምህርት ቤቶች ፈተናዎች በምንባብ የጥያቄ ብዛት ምን መልክ እንዳለው የሚከተለው ሰንጠረዥ ከሚያመለክተው መገንዘብ ይቻላል።

ሰንጠረዥ 7፤ እንብቦ መረዳትን ለመፈተኛ መሣሪያነት በየዓመቱ
ከተመረጡት ውስጥ ከ10 በታች ፣10፣ከ11-15 እና
ከ15 በላይ ጥያቄዎች የወጡባቸው ምንባቦች ብዛትና መቶኛ፤

ቁም	ዩኑቨርሲቲው ብዛት	ከ10 በታች		10		11 - 15		ከ15 በላይ		ጠቅላላ
		ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት
1987	10	8		9		7		4		26
1988	11	9		8		9		3		29
1989	11	9		10		8		2		29
1990	12	12		10		6		1		29
ድምር		38	31.86	37	32.74	30	26.55	10	8.85	113

በንጠረዥ 7 እንደሚያመለክተው የጥያቄዎቹ ብዛት ቀደም ብሎ ከተገለጸው ከምንባቡቹ በጣም አጭር አጭር መሆን ጋር የሚጣጣም አይመስልም። ከ11 ጥያቄ በላይ የወጣባቸው ምንባቦች ብዙዎች ናቸው።

አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የሚመረጡ ምንባቦች ለሁለተኛና ለውጭ ቋንቋ ተማሪዎች ላይቀር በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ እንኳ ቢሆን ትክክለኛ የሆኑ ወይም ለፈተናው ሲባል ማሻሻያ ያልተደረገባቸው (Authentic) ምንባቦችን መጠቀም ተገቢነት ያለው እንደሆነ ብዙ የመሰከሙ ምሁራን ይጋግሙ የሚያስገንዝቡት ጉዳይ ነው። በተለይ ከተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርትና ፈተና ግደግ ወዲህ ይህ አተያይ ከፍተኛ ቦታ የተሰጠው ነው።

በዝህ ለጥናት በተመረጡት ሞዴል ፈተናዎች በዚህ አቅጣጫ የታየ ከትምሪራዊ አተያይ መርህው ጋር የሚዛረር ተግባር ያለ አይመስልም። ሁሉም ማሻሻያ ሳይደረግባቸው የተወሰዱ ሆነው ነው የተገኙት ግለት ይቻላል። በርግጥ በእንዳንድ ፈተናዎች ምንባቦች ግርጌ ለፈተና እንዲያመች ተሻሽሎ የተወሰደ የሚል ሰፍሯል። ሆኖም ተወሰደባቸው ከተባሉት ስራዎች ጋር በማመሳከር ግረጋገጥ እንደተቻለው ከዋናው ጽሑፍ በተለየ መልኩ ቃላትን በመለወዋ፣ አላጥር በመቁ _ የተደረገ እንዳችም ለውጥ ማየት አልተቻለም። ምናልባት ለውጥ የተባለወ ሙሉው ጽሑፍ አለመወሰዱ ሊሆን ይችላል። ሌላው ምክንያት በመምህራኑ ያለው ግንዛቤ አሻሽሎ መጠቀም ተገቢነት ያለው ስለሚመስል ሊሆን ይችላል። ይህን የሚያጠናክር ከመጠይቅ የተገኘ ተጨማሪ መረጃም አለ። ይኸውም በለንጠረዥ 8 እንደተመለከተው በጥያቄ ቁጥር 8_1 ለተጠየቁት ጥያቄ 73.33፤ የሚሆኑት አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የሚመረጡት ምንባቦች የጠወለጉት እንዳለ ሳይሆን በማሻሻል ነው ብለዋል። ይህ የሚያሳየው አብዛኞቹ መምህራን ከተመራማሪዎች አመለካከት ጋር የሚዛረር ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን ነው። ያውም ለአብዛኞቹ ቀንቀው እኖ መፍቻቸው ለሆነው ተማሪዎቻቸው ነው ይህን አይነት አሰራር ቢከተሉ የጠወዱት፤ በተግባር ባያደርጉትም።

በቀጣጠው እንቀፅ እንደተወሳው ይህንኑ የምንባብ አመራረጥን በሚመለከት መምህራኑ በመጠይቁ የተለያዩ ጥያቄዎችን ተጠይቀው ነበር። በጥያቄ ቁጥር 5፣ 6፣ 7፣8_1፣ 8_2፣ 9 እና 10።

በንጠረዥ 8 እንደሚያሳየውም ለጥያቄ 5፣ 73.33፤፣ የሚስማሙ መሆናቸውን ገልፀዋል። አንስማማም ያሉት 13.33፤ የሚሆኑት ናቸው። ይህም በዚህ አቅጣጫ አብዛኞቹ መምህራን ቢያንስ ተገቢ የሆነ አመለካከት ያላቸው መሆኑን ያሳያል። በተግባራዊ ስራዎቻቸው (ባዘጋጇቸው ፈተናዎች) የታየው ፅውንታ ግን ከሀሳባቸው ጋር የመጣጣም ደረጃው ዝቅ ያለ ሆኖ ነው የተገኘው።

ሰንጠረዥ 8፤ እንብቦ መረዳትን ለመፈተን የምንባቦች አመራረጥን በሚመለከት ከመምህራኑ የተገኙ መረጃዎች፤

የጥ ቁጥር	ጥያቄ	አማራጮች					
		5 + 4	%	3	%	2 + 1	%
1	የተለያዩ ናኒንብቦ መረዳት ክህሎትን ለመፈተን የተለያዩ ምንባቦችን ለመምረጥ ይሞክራሉ?	14 8 22	73.33	4	13.3	4 - 4	13.33
2	ምንባቦቹ ኒመረመሩና ክምንባቡ ዋነኞቹን ኒመሉ ኒያኒቸ ኒንዳሆኑ ይደረጋሉ?	16 7 23	76.67	3	10	3 1 4	13.33
3	የተለያዩ ክህሎትን ለመፈተን ያገለገሉ ምንባቦችን መምረጥ የተሳለጠ ነው።	5 2 10	33.33	4	13.3	10 6 16	53.33
4	ኒንብቦ መረዳትን ለመፈተን ከየሊያዩ ቋሎርች ሚመረጡ ምንባቦች ሚጫቤሉት ኒንሳኒ ኒሆነን ኒደሚያዎቹ ፊደሚር ችግር፣ ለየያቂ አመካየ ሚሆመቱ ማየኒ ያደረጉበው ነው?	14 8 22	73.33	5	16.67	2 1 3	10
5	ኒንሳኒ ምንም ማየኒያ ሳይደረግባቸው ያቀነባብው/መኒየው/ ይመስሳል?	10 5 15	50	8	26.67	6 1 7	23.33
6	ምንባቦቹ ያኒበበር ያሌየረቶ የሚ ኒመልኒየው ሚኒኒው ዋቁት ዋያቄዎች ኒንዲቀየጹ ይደረጋሉ?	3 7 10	33.33	3	10	12 5 17	56.67
7	ብዙ ምንባቦች ለማኒየት ዋረት ሚኒደረግ ሲሆንም ያኒሚያዩ ኒጨየሌ ጠቅቀው ሚገንዘቢቡበው ወይም ኒሚያዩ ፊደመው ያህኒየው ሰዓኒየው ሚኒኒው ምንባቦች/ ኒንዳኒሳቸው ይደረጋሉ?	4 7 11	36.6	5	16.67	4 10 14	46.67

አማራጮች ፡ 5. በጣም እስማማለሁ፤ 4. እስማማለሁ፤ 3. ለመወሰን እቸገራለሁ፤ 2. አልስማማም፤ 1. በጣም አልስማማም የሚሉ ሲሆኑ ትንተናው 5 እና '4'ን ባንድ፤ '3'ን ለብቻ፤ 2 እና '1'ን ባንድ ክፍል (category) በመመደብ ነው የተካሄደው።

ለጥያቄ 6 ደግሞ 76.67 በመቶው እስማማለሁና በጣም እስማማለሁ፤ 13.33ፊ አልስማማምና በጣም አልስማማም፤ 10ፊ ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል። ከአብዛኞቹ የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ምንባቦቹና ከምንባቦቹ የሚወጡት ጥያቄዎች አድሏዊ እንዳይሆኑ የሚደረግ መሆኑን ነው።

በተግባር፤ ባዘጋጇቸው ፈተናዎችም በ1990 በትምህርት ቤት 10 ከአፎይታ መፅሐት የተወሰደ የተባለው ምንባብ ከፆታ አንፃር አድሏዊ የሆነ፤ ተማሪዎች ሌላ ሀሳብ ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርግ አይነት ከመምሰሉ በቀር ሌሎቹ ለተወሰነ ባህል፤ ለተወሰነ የትምህርት መሰክ ተማሪዎች፤ ለተወሰነ ፅድሚና ፆታ፤ ... የተለየ ፅድል የሚሰጡ ወይም አድሏዊነት የሚታይባቸው ሆነው አልተገኙም። አጠቃላይ የሆነ ይዘት (ጉዳይ) የሚያነሱ መሆናቸው በዚህ በኩል አስተዋፅኦ ያበረከተ ይመስላል።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ለS_1 73.33ፊ እስማማለሁና በጣም እስማማለሁ፤ የሚል መልስ ሰጥተዋል። 10ፊ የሚሆኑት እንስማማም ብለዋል። 16.67 በመቶው ደግሞ ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው።

ባንፍሩ ለቀጣዩና ከዚህ ጋር ለተያያዘው ጥያቄ ለጥያቄ 8_2 (እንዳለ ምንም ማሻሻያ ላይደረግባቸው ተቀንጭበው /ሙሏቸው/ ይወሰዳሉ) ለሚለው 50 በመቶው እስማማለሁና በጣም እስማማለሁ፣ 23.33፧ አልስማማምና በጣም አልስማማም 26.67፧ ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል። በዚህኛው ጥያቄ የተገኘው መልስ የላይኛውን የሚገረር ይመስላል። በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱንም ስልቶች እንጠቀማለን ከሚል አስተያየት የመጣ ይመስላል፤ ለሁለቱ ድጋፍ የሌው ስላሉ።

ለጥያቄ 9፣ 56.67 በመቶው ምንባቦችን ያላንበበና ያልተረዳ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች እንዲቀላቀሉ የማይደረግ መሆኑን አልስማማምና በጣም አልስማማም በማለት ገልፀዋል። ይህ ተግባር እንደሚከናወን የገለፁት ደግሞ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው 33.33፧ የሚሆኑት ናቸው። ከዚህም በፈተናዎቹ ጥያቄዎች ላይ ያለምንጭ ሊመለሱ የሚችሉ ጥያቄዎች መኖር ባጋጣሚ ወይም በጥንቃቄ ጉድለት የተከሰተ ብቻ ላይሆን ይችላል ማለት ነው።

በመርህ ደረጃ ግን ይህ አይነት አሰራር የማይደገፍ እንዲያውም የሚወገዝ ነው ማለት ይቻላል።

የመጨረሻው ጥያቄ ቀደም ሲል የተወያየንበት ነው። ከተመራማሪዎች አተያይ ጋር የሚስማማ መልስ የሰጡት መላሾች 46.67፧ ናቸው። 36 በመቶው ተፈታኞቹ ቀድመው ሊያነቧቸው የሚችሏቸው ምንባቦች እንዳይካተቱ የሚደረግ ጥረት አለመኖሩን ነው የጠቆሙልኩት። 16.67 በመቶው ደግሞ ለመወሰን የተቸገሩ ናቸው። በዚህ ጥያቄ ከተገኘው መረጃ መረዳት የሚቻለውም ቁጥራቸው ቀላል የማይባል መምህራን ለመፈተኛነት የሚመረጡ ምንባቦች ከየት መመረጥ እንዳለባቸው በቂ ግንዛቤ የሌላቸው መሆናቸውን ነው። ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በተግባር በፈተናዎቹ ላይ ጎልተው ከታዩት ድክመቶች አንዱ ይኸው ነው። ተግባሮች እንደልብ ሊያገኟቸውና ሊያነቧቸው ከሚችሏቸው ፅሑፎች ብቻ ሳይሆን በየቤቱ ለፖ ከሚገኙት ከ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናዎች ላይቀር ምንባቦች የሚወሰዱ መሆኑን ነው ግረ,ንገጥ የተቸገሙ።

4.1.2 የቮክሊስቱ ከሂሎች ውክልና በፈተናዎቹ ጥያቄዎች

ባንብቦ መረዳት ፈተና እንዚህን የመሳስሉትን ባጠያየቅ ዘዴዎች ምርጫ የተነሳ ሊከሰቱ የሚችሉ ትግርች ለግቃለል የሚቻለው ዌየር (1993፣ 1990)፣ ሂዩዝ (1995)፣ ኦልደርሰን፣ ኮፖምናምል (1995)፣ ሀሪሰንና ግከካን (1994)፣ ሂተን (1991፣ 1990) በመጥቀስ በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው እያንዳንዱ ዘዴ የትኛውን ንዑስ ክሂል ለመመዘን አመችነት እንዳለው እያንጎጠቡ የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎችን እያሰባጠሩ መጠቀም ሲቻል ነው።

በምዕራፍ አንድ እንደተወሳው በዚህ ጥናት በዚህ ክፍል የፈተናዎቹን ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት ለመመርመር የሚሞከረው ከሁለት አቅጣጫ ነው፤ ከትምራዊ አተያየትና ከመማሪያ መፅሐፉ አኳያ።

በመጀመሪያ ከላይ በተዘረዘሩትና በሌሎችም ምሁራን አንብቦ መረዳትን ለመፈተን አመቺነት እንዳላቸው ከተመሰከረላቸው ያጠያየቅ ዘዴዎች ጋር ፈተናዎቹ ያላቸውን ተዛምዶ እንመለከታለን። እንብቦ መረዳትን ለመመዘን የሚያገለግሉ ብዛት ያላቸው ያጠያየቅ ዘዴዎች በተለያዩ ተመራማሪዎች፣ ለምሳሌ ከላይ በተጠቀሱት በነዌየር (1993፣ 1990) ሂዩዝ (1995) ... የተዘረዘሩ ቢሆንም በ2.7.2.2 እንደተወሳው ለፈተናዎቹ መመርመሪያነት የተመረጡት በብዙ ጥቂ የመስኩ ምሁራን ተስማሚነታቸው ተደጋግሞ የተመሰከረላቸው በሚከተለው ንጉረሄ የቀረቡት ሰባቱ ዘዴዎች ብቻ ናቸው።

ሰንጠረዥ 22፤ የሞዴል ፈተናዎቹ የአንብቦ መረዳት ክፍል ያጠያየቅ ዘዴዎች በተለያዩ ተመራማሪዎች ጥናቶች ከቀረቡት የአንብቦ መረዳት ፈተና ያጠያየቅ ዘዴዎች ጋር ያላቸው ተዛምዶ፤

		1. ምርጫ ዕጥ		2 ባዶ ቦታዎችን መሙላት						3 እውነት (ወይስ)		4 አዛምድ		5 ቅደም ተከተል መለየት		6 መረጃ ግኝጋገር		7 አጭር መልስ		ሌሎች	
				2.1 ሰርአታዊ ግድፈቶች				2.2 ሆን ተብሎ የተገደፉ													
				ምርጫ ዕጥ		ምርጫ የማይሰጥ		ምርጫ ዕጥ		ምርጫ የማይሰጥ											
1987	ትሪቤት	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ
	21	1								-											
	09	2																			
	13	1																			
	19	1																			
	18	2																			
	20	3																			
	14	3																			
	18	3																			
	14	3																			
	06	3																			
ድምር		24	100																		
1988	23	3																			
	05	3																			
	17	3																			
	12	0																			
	10	3																			
	22	0																			
	16	0																			
	11	0																			
	24	0																			
	08	3																			

		1. ምርጫ ሰጭ		2 ባደ. ቢታምችን መመላት								3 እመ.ነት (ዘሰት)		4 አዛምድ		5 ቅደም ተከተል መለየት		6 መረጃ ማፀጋገር		7 አጭር መልስ		ሊሎች	
				2.1 ስርአታዊ ገርፈፃን				2.2 ሆን ተብሎ የተንደፉ															
				ምርጫ ሰጭ		ምርጫ የማይሰጥ		ምርጫ ሰጭ		ምርጫ የማይሰጥ													
1989	ት/ቢት	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ	ብዛት	ፐ
	21	3																					
	09	2																					
	11	1																					
	19	3																					
	24	2																					
	18	2						1															
	20	1																					
	14	2																					
	10	2																					
	06	2						1															
	17	3																					
	ድምር	27	93.1					2	6.9														
1990	21	3																					
	08	2																					
	17	2																					
	23	3																					
	04	1																					
	13	1																					
	22	2																					
	12	2																					
	16	2																					
	07	2																					
	15	2																					
	ድምር	23	79.3					6	20.7														
ጠቅላላ ድምር		50	172.4					8	27.6														

ሰንጠረዥ 22 እንደሚያመለክተው በ1987 ዓ.ም. 26 (100%)፤ በ1988 ዓ.ም.፣ 29 (100%)፣ በ1989 ዓ.ም.፣ 27 (93.1%)፤ በ1990 ዓ.ም.፣ 29 (100%)፣ ባጠቃላይ በአራቱ ዓመታት 111(98.2%)=2 (1.8%) የሚሆኑት መመሪያዎች /instructions/ በተራ ቁጥር 1 በተመለከተው በምርጫ ሰጭ ያጠያየቅ ዘዴ ብቻ የተጠየቁ ናቸው። እንዲሁም በተራ ቁጥር 2 ስር ከተዘረዘሩት ውስጥ 2ቱ (6.9%) መመሪያዎች በ1989፣ በ2.2 በተመለከተው ያጠያየቅ ዘዴ ተጠይቀዋል። የቀሩት 6 ያጠያየቅ ዘዴዎች በየትኛውም ዓመት ፈተና ያልተሰራባቸው ናቸው።

ባጠቃላይ የመረጃ ትንተናው ከሚያሳየው ማረጋገጥ የተቻለው አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የሚያገለግሉ የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎችን የማይጠቀሙ መሆናቸውን ነው። የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎችን የማይጠቀሙ ከመሆናቸው በተጨማሪም በክለሳው ክፍል እንደቀረበው በብዙ ሶቹ ተመራማሪዎች አንብቦ መረዳትን ለመፈተን ከሚሰራባቸው ዘዴዎች ብዙ አሉታዊ ነኖች ያሉበት እንደሆነ የሚጠቀሰውን ይበልጥ የሚጠቀሙ መሆናቸውንም ያሳያል። ምርጫ ሰጭ ዘዴ በተለይ ቼየር (1993)ን ጥቂ በማድረግ እንደተገለፀው ከዋቅመ- ጉዳቱ የማያመዝን በመሆኑ ብዙ የተማሪ ቁጥር ባለባቸው እንደነ ቻይና ባሉ ሀገሮች ሳይቀር እየተተወ የመጣ ዘዴ ነው።

ከዚህ የመረጃ ትንተና ግኝት በመነሳት መምህራኑ አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ከተመራማሪዎቹ አተያይ አኳያ ሲታዩ አምንታዊ የሆነ ተዛምዶ የሌላቸው ናቸው ብሎ መደምደም የሚቻል ይመስለናል። ከዚህም የተነሳ በክለሳው-ና በዚህ ንውስ ርዕስ ስር መግቢያ የተገለፁት ችግሮች ለምላሌ በውስን ዘዴዎች የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክሂሎትን በአግባቡ ለመመዘን ያለመቻል፣ በአጠያየቅ ዘዴዎች ውስን መሆን የተነሳ ለክሎቱ የሚገቡ ፆታዊ፣ ማህበረሰባዊና ስነልቦናዊ አድሎዎች እንዲከሰቱ የተመቻቸ ሁኔታ የተፈጠረ መሆኑ ነው ነልቶ የሚታየው።

የ12ኛ ክፍል የእግርኛ መማሪያ መፅሐፍ የአንብቦ መረዳት ክፍል ያጠያየቅ ዘዴዎች

ቀደም ሲል በ4.1.1 እንደተወሳው በዚህ መማሪያ መፅሐፍ 12 ምንባቦች ተካተዋል። ለክፍሉ ከተዘጋጀው የመምህሩ መምሪያና ከራሱ ከመማሪያ መፅሐፉ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው ከምንባቦቹ ቀጥሎ በመልመጃ እንድ ስር የሚቀርቡት ጥያቄዎች አንብቦ መረዳትን የሚመለከቱ ናቸው። በመልመጃ ሁለትና ሦስት ስርም ውስን ይሁኑ እንጂ የአንብቦ መረዳት ክሂሎትን የሚያለማምዱ ጥያቄዎች አሉ። በነዚህ መልመጃዎች በተለይም በመልመጃ አንድ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች እንዴት መስራት እንዳለባቸው የሚሙሩ የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎች ተካተዋል። ቀጥሎ ከቀረበው ሰንጠረዥ ማስተዋል እንደሚቻለው በክለሳው ክፍል ከተዘረዘሩት ያጠያየቅ ዘዴዎች ውስጥ የተወሰኑት በዚህ መቆሌፍ ውስጥ ይገኛሉ።

ሰንጠረዥ 23፤ የመግሪያ መፅሐፉ ያጠያየቅ ዘዴዎች አይነት፣ የየአይነቶቹ ድግግሞሽና መቶኛ፤

ያጠያየቅ ዘዴዎች																			
...		...		...		...		...		...		...		...		...		...	
ቁ	%	ቁ	%	ቁ	%	ቁ	%	ቁ	%	ቁ	%	ቁ	%	ቁ	%	ቁ	%	ቁ	%
...	...	8	88	3	7.3	13	31.7	3	7.3	4	9.8	3	7.3	2	4.9	1	2.4	1	2.4

ማስታወሻ፣ "ብ" በአጠያየቅ ዘዴዎች የድግግሞሹን ብዛት የሚያመለክት ነው።

ሰንጠረዥ 23 እንደሚያሳየው በመግሪያ መፅሐፉ በከፍተኛ ደረጃ የተንፀባረቀው አጭር ሙልሰ ጠያቂ ያጠያየቅ ዘዴ ነው። መፅሐፉ ካካተታቸው 10 ያህል የአንብቦ መረዳት ክፍል ያጠያየቅ ዘዴዎች ውስጥ 31.7 በመቶውን የሸፈነው ይህ በክለሳው ክፍል የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ንፁሳን ክሂሎችን ለመመዘን የሚያስችል ነው የተባለው ዘዴ ነው። ምርጫ ሰጭ በ17.07፤ በሁለተኛነት ይከተላል። እውነት/ሀሰትና ግለፅ በ9.76፤ የሶስተኛነትን ደረጃ ያዘዋል። በተራ ቁጥር 3፣ 5 እና 7 የተመለከቱት/አዛምድ፣ ትርጉም/ፍቺ አመልክትና አብራራ/ ደግሞ ሶስት፣ ሶስት ጊዜ በመከሰት በ7.31፤ የ4ኛነትን ደረጃ ይዘዋል። አንዳንድ ጊዜ ብቻ በመከሰት የመጨረሻውን ደረጃ የያዙት በተራ ቁጥር 9 እና 10 የተመለከቱት አስረዳና እንደመመረያው መልሰ የሚሉት ያጠያየቅ ዘዴዎች ናቸው።

ለማጠቃለል ከትንተናው መረዳት እንደሚቻለው የ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ክፍል ከ10 ያላነሱ ያጠያየቅ ዘዴዎችን በውስጡ ያካተተ ሲሆን ከዘግ /objective/ (ከምርጫ ሰጭ፣ እውነት/ሀሰት አዛምድ) ይልቅ ለክፍት (subjective) ያጠያየቅ ዘዴዎች የበለጠ ቦታ የሚሰጥ ነው። ሰንጠረዥ 23 እንደሚያመለክተው ከ14 የተዘረዘሩት ዝግ ያጠያየቅ ዘዴዎች 34.15፤ ያህሉን ብቻ ሲወክሉ የቀሩት ደረቅ ጥያቄዎች 65.85፤ የሚሆነውን ይሸፍናል (ወክለዋል)። ይህም ምንም እንኳ እንደ መረጃ ማሸጋገር ያሉት ለአንብቦ መረዳት ትምህርት ተስማሚነት ያላቸው ያጠያየቅ ዘዴዎች ያልተካተቱበት መፅሐፍ ሆኖ ቢገኝም በተመራማሪዎቹ የሚደገፈውን ክፍት (subjective) ያጠያየቅ ዘዴዎች ይበልጥ የሚጠቀም መሆኑን ያሳያል።

የመግሪያ መፅሐፉና የሞዴል ፈተናዎቹ የአንብቦ መረዳት ክፍል ያጠያየቅ ዘዴዎች ተዛምዶ፤

ሂዩዝ (1995)፣ ቄየር (1993) እና ሌሎችም ተመራማሪዎች እንደሚገልፁት ፈተናዎች ተግሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት የተለማመዷቸውን ያጠያየቅ ዘዴዎች የሚያንፀባርቁ መሆን ይኖርባቸዋል። በመግሪያ መፅሐፎቻቸው ቀርበውላቸው በክፍል ውስጥ ትምህርት ያልተዋወቋቸውን ያጠያየቅ ዘዴዎች ለመጠቀም ቢፈለግ እንኳ ከፈተናው በፊት በቅድሚያ በክፍል ውስጥ እንዲለማመዷቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው።

በሌላ አቅጣጫ ሲታይም በመማሪያ መፅሐፉ(ፎቹ) የቀረቡት ያጠያየቅ ዘዴዎች ሁሉ በፈተናዎቹ አለመቻሬን የአግባብነት /validity/ ደረጃን ዝቅ ያደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ እና በተያያዘ ቀደም ሲል የተገለፁት የተለያዩ ንዑሳን ክሂሎችን ለመመዘን አለመቻል፣ ለተመሰነ ጥቃ ግላዊ ባህሪ ... የማድላት አይነት ችግሮች እንዲከሰቱም በር ሊከፍት ይችላል።

ከነዚህ መርሆዎችና አተያየቶች በመነሳት ቀጥሎ የሞዴል ፈተናዎቹ የመማሪያ መፅሐፉን ያጠያየቅ ዘዴዎች የማንፀባረቅ ደረጃ ለመመርመር ይሞከራል።

ሰንጠረዥ 24፤ የመማሪያ መፅሐፉና የሞዴል ፈተናዎቹ የአንብቦ መረዳት ክፍል ያጠያየቅ ዘዴዎች ተዛምዶ፤

ተ.ቁ	ያጠያየቅ ዘዴው ዓይነት	የመማሪያ መፅሐፍ		የሞዴል ፈተናዎቹ											
				1987 10 ቅ/ቤት			1988 11 ቅ/ቤት			1989 11 ቅ/ቤት			1990 11 ቅ/ቤት		
		ቁ	%	ብ	%	ለዉ	ብ	%	ለዉ	ብ	%	ለዉ	ብ	%	ለዉ/ነ
1.	ምርጫ ንባብ	1	17.1	29	100	- 82.9	29	100	- 82.9	27+2	93.1+ 6.90	- 82.9	29	100	- 82.9
2.	ሐቁ-ነክ ጥያቄ	8	9.8												
3.	ተመሳሳይ	3	7.3												
4.	ትክክለኛ መልስ	13	31.7												
5.	ከጎደሉት ቃላት ተገቢውን ቃል መምረጥ	3	7.3												
6.	ትክክል	9	9.8												
7.	ትዕዛዝ	3	7.3												
8.	ሀተማ	3	4.9												
9.	ሀተማ	1	2.4												
10.	ትክክለኛውን መልስ	1	2.4												

ማስታወሻ - *በ1989 ዓ.ም. ምርጫ ሰጭ በሚለው ትይዩ 27 + 2 በሚለውና 93.1+6.9 በሚለው ውስጥ +2 እና + 6.9 ለብቻ መጠቀሳቸው የተጠየቁት በምርጫ ሰጭ ያጠያየቅ ዘዴ ቢሆንም ሆን ተብሎ የተገደፈን ቃል (ሀረግ) መተካትን ጠያቂ ጥያቄዎች መንገድ የቀረቡ በመሆናቸው ትንሽ ለየት ማለታቸውን ለማመልከት ነው።

ሰንጠረዥ 24 እንደሚያመለክተው የመማሪያ መፅሐፉና የሞዴል ፈተናዎቹ ባጠያየቅ ዘዴ የሚገናኙት ከተዘረዘሩት 10 የመማሪያ መፅሐፉ ያጠያየቅ ዘዴዎች ውስጥ ባንዱ በምርጫ ሰጭ (ተራ ቁጥር 1) ብቻ ነው። ይህ ያጠያየቅ ዘዴ በመማሪያ መፅሐፉ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክፍሎች 17.07፤ ጊዜ የተደጋገመ ሲሆን በፈተናዎቹ ደግሞ 100፤ ጊዜ ተከስቷል። - 82.9 ልዩነት በሁለቱ መካከል ይታያል። ይህም ፈተናዎቹ ይህን ያጠያየቅ ዘዴ ከመማሪያ መፅሐፉ እጅግ በሚበዛ ልዩነት የሚጠቀሙበት መሆናቸውን ያሳያል።

በጎሙተ ምህረቶቹ መካከል አለመመሳሰል የሚታየው ይህ ያጠያየቅ ዘዴ በ1987 ዓ.ም. በ10 ፈተናዎች 26 ጊዜ፣ በ1988 ዓ.ም. በ11 ፈተናዎች 29 ጊዜ፣ በ1989 እንዲሁ በ11 ፈተናዎች 29 ጊዜ፣ በ1990 ዓ.ም. በ12 ፈተናዎች 29 ጊዜ የተከሰተ በመሆኑ ነው። ከዚህ ውጭ በመቶኛና በልዩነት መጠን ተመሳሳይ የሆነ ክስተት ነው የሚታየው።

ሌላው ግኝት፣ ይኸው ስንጠረዥ፣ (ስንጠረዥ 24) ከሚያሳየው መገንዘብ እንደሚቻለው ከምርጫ ሰጭ ውጭ ያሉት ሌሎቹ የመግሪያ መፅሐፉ ያጠያየቅ ዘዴዎች ተመክለው የማያውቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ መቻሉ ነው። አንድም ሌላ የመማሪያ መፅሐፉ ያጠያየቅ ዘዴ ባንድም አጋጣሚ፣ ባንድም ፈተና ሲንፀባረቅ አይታይም። በርግጥ በ1989 ሁለት ፈተናዎች ሆነ ተብሎ የተገደፈን /selective deletion gap filling/ ቃል/ሀረግ የመመላት ያጠያየቅ ዘዴ ተጠቅመዋል። ሆኖም በምርጫ ሰጭ ያጠያየቅ ዘዴ የቀረበ በመሆኑ በዚያው በምርጫ ሰጭ ዘዴ ከመፈረጅ የወጣ ሊሆን አልቻለም።

ይህም የሚያሳየው ፈተናዎቹ ተማሪዎቹ በመማሪያ መፅሐፉ ቀርበውላቸው የተለማመዷቸውን ያጠያየቅ ዘዴዎች የማያንፀባርቁ መሆናቸውንና በዚህም በኩል ከፍተኛ የሆነ ድክመት የሚታይባቸው እንደሆኑ ነው።

ካጠያየቅ ዘዴዎች ጋር ለተያያዙት ጥያቄዎች ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ግን በተግባር በፈተናዎቹ ከታየው ጋር የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም። ቀጥሎ የቀረበው ስንጠረዥ እንደሚያሳየው መጠይቁን በመሙላት ከተሳተፉት ውስጥ "የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ለመመዘን ምርጫ፣ እውነት/ሀሰት፣ ማዛመድ፣ ክፍት ቦታ መሙላት፣ መረጃ ማሸጋገር፣ አጭር መልስ መስጠት... የሚባሉትን ያጠያየቅ ዘዴዎች መጠቀም የተለመደ ነው።" ለሚለው ለጥያቄ 11፣ 43.3% የሚሆኑት እምንታዊ መልስ ሰጥተዋል። የዚህን ተቃራኒ ሀሳብ ለያዘው ለጥያቄ 12 ደግሞ 56.6% የሚሆኑት የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎችን መጠቀሙ የሚሰጠው ጥቅም ስለሌለ ውስን ዘዴዎችን መጠቀም የተለመደ ነው የሚል አስተያየት ሰጥተዋል። ለጥያቄ '13' 36.6% የሚስማሙ መሆናቸውን አመልክተዋል።

ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው መላሾች ለጥያቄ 11፣ 12፣ 13 ና 14 በተግባር በፈተናዎቹ ከታየው ፅውንታ የሚፃረር አስተያየት ሰጥተዋል።

ይህን አይነት አስተያየት ሊሰጡ የቻሉበት ምክንያት ምናልባት ባይፈፅሙትም መሆን የንበረበት መሆኑን ስለሚያምኑበት አይፈፀምም ማለቱ ስለከበዳቸው ሊሆን ይችላል (ፈተናዎቻቸው አብረው የሚመረመሩና እውንታው የሚታወቅ መሆኑን ባለማወቅ)። ወይም ሌላ ምክንያት ሊኖር ይችላል።

ባንዱም ፈተናዎችን ሲያዘጋጁ የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎችን እንደማይጠቀሙ፣ የመግሪያ መፅሐፉን ያጠያየቅ ዘዴዎች ለማንፀባረቅ እንደማይሞክሩ ከመማሪያ መፅሐፉ ያጠያየቅ ዘዴዎች ውጭ ሌሎች ተጨማሪ ዘዴዎችን እንደማይጠቀሙ የገለፀት መላሾች ቁጥርም ብዙ ነው። በዚህ አቅጣጫ የተሰጠው የሁሉም ጥያቄ መልስ ከ50% በላይ የሆነ ነው።

ከዚህም ሙምህራኑ አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎችን አለመጠቀሙ በፈተናው ህያውነት /reliability/፣ አስተማማኝነት /validity/... ላይ የሚያመጣውን አደጋ በሚመለከት ወይ ግንዛቤያቸው በቂ አይደለም ወይም ግንዛቤው ቢኖራቸውም በተግባር ለመጠቀም ፍላጎቱ የላቸውም።

ሌላ ምክንያት ለመስጠት እንዳይሞክር በዚህ የመጠይቁ ክፍል 15ኛ ጥያቄ ለሆነው "በጥቅሉ ከ1986 ወዲህ በየአመቱ የተሰጡት የ12ኛ ክፍል ሞደል ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ክፍሎችን ለመፈተን ብቃት ያላቸው ናቸው።" ለሚለው 83.3% የሚሆኑት የሞደል ፈተናዎቹ አንብቦ መረዳትን ለመመዘን ብቃት ያላቸው ናቸው በማለት የመለሱ ከመሆናቸውም በተጨማሪ አስተያየት ካላቸው እንዲገልፁ በሚጠይቀው 16ኛው ክፍት ጥያቄ ላይ ያስፈሩት አንድም ነገር ወይም ሌላ ነገር ስለሌለ በዚህ የተነሳ ሊሆን ይችላል ለማለት ያስቸግራል።

ሰንጠረዥ 25፤ ያጠያየቅ ዘዴዎችን በሚመለከት ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘ መረጃ፤

ተ.ቁ	ጥያቄው	አማራጮች					
		5 - 4	%	3	%	2 - 1	%
11	የአንብቦ መረዳት ክፍሎችን ለመመዘን፣ ምርጫ አመነ/ልክ፣ መዛመድ፣ ክፍል በቃ መመላለት፣ መረጃ ማደንገር፣ አጭር መልስ መስጠት ... የሚሉትን ያጠያየቅ ዘዴዎች መጠቀም የተለመደ ነው።	3 - 10 13	43.33	1	3.33	12 - 4 16	53.33
12	የተጠያቂ ያጠያየቅ ዘዴዎችን መጠቀም የሚሰጠው ጥቅም ስለሌለ ውስን ዘዴዎችን ብቻ መጠቀም የተለመደ ነው።	6 - 11 17	56.66	3	10	9 - 1 10	33.33
13	በመማሪያ መፅሐፈቸ የተጠቀሚየው ያጠያየቅ ዘዴዎች ውስ በሞዴል ፈተናዎቹ ያገለግሉዎታል።	4 - 7 11	36.66	2	6.6	13 - 4 17	56.66
14	በመማሪያ መፅሐፈቸ የተጠቀሚየው ያጠያየቅ ዘዴዎች ውስን ስለሆኑ በሞዴል ፈተናዎቹ በቁንቁ ፈተና የመማሪያዎቹ ይዘንቁ መረጃዎች ከየክፍሉ ፈተና ተነሺነት አለየው የሚሰው ተጨማሪ ያጠያየቅ ዘዴዎችም መጠቀሙ ግድ ስለሆነብን ተግባራዊ አያደረግነው ነው።	3 - 11 14	46.66			11 - 5 16	55.33
15	በጥቅሉ ከ1986 ወዲህ በየአመቱ የተሰጡት የ12ኛ ክፍል ሞዴል ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ክፍሎችን ለመፈተን ብቃት ያላቸው ናቸው።	5 -20 25	83.3	2	6.6	1 -2 3	10

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና ጥቆማ

5.1 ማጠቃለያ /Summary/

በመግቢያው እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ12ኛ ክፍል የሞዴል ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ክፍል የይዘትና የላህይ አግባብነትንና ያጠያየቅ ዘዴዎችን ብቃት ለመመርመር ነው። ዋና ዋና አነሳሽ ምክንያቶቹ፦

- በአንብቦ መረዳት ፈተና መመዘን የሚገባቸው ክሂሎች ሁሉ በፈተናዎቹ ጥያቄዎች፦ ሀ. ይመዘናሉ (ይሸፈናሉ)? ለ. አመዛዘኑ (አሸፋፈኑ) በቂ፣ ወካይና ተመጣጣኝ በሆነ ናሙና ነው?
- በመርሀ ትምህርቱ የአንብቦ መረዳት ክፍል ይዘትነት የቀረቡት ክሂሎች ሁሉ በሞዴል ፈተናዎቹ፦ ሀ. ይሸፈናሉ? ለ. የሚሸፈኑት በቂ፣ ወካይና ተመጣጣኝ በሆነ ናሙና ነው?
- በፈተናዎቹ የሚመረጡት ምንባቦችና ያጠያየቅ ዘዴዎች የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ለመመዘን የሚያስችሉ ወይም የአመራረጥ መርሆዎችን፣ ቴክኒኮችንና መመዘኛዎቹን የሚከተሉ ናቸው? የሚሉት ጥያቄዎች ነበሩ።

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስና ከጥናቱ አላማ ግብ ለመድረስ በቅድሚያ ተጠኝዎችና የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል። ተጠኝዎቹ በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ከ1987 - 1990 የተሰጡት የሞዴል ፈተናዎች ናቸው። የእነዚህን ፈተናዎች የይዘትና የላህይ አግባብነትና ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት ለመመርመር፣ ፈተናዎቹን፣ ቸክሊስት፣ መጠይቅ፣ የ12ኛ ክፍል የእግርኛ መርሀ ትምህርትና የመማሪያ መፅሐፍ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያንት ጥናቱ ተገልግሏል።

በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎችም በተለያዩ ንፅፅን ርዕሶች ስር በምዕራፍ አራት ተተንትነዋል።

በመጀመሪያ የተተነተነው የምንባቦቹ አመራረጥ ነው። በዚህ ክፍል በተለያዩ ምሁራን ጥናቶች በቀረቡት መርሆዎች ቴክኒኮችና አተያዮች መነሻነት በተደረገው ግምገማ በሞዴል ፈተናዎቹ የምንባቦቹ አመራረጥ አምንታዊም፣ አሉታዊም ገፅታዎች እንደሚታዩ ማረጋገጥ ተችሏል። ሆኖም አሉታዊ የሆኑት በመብዛታቸው የተነሳ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን

በአግባቡ ለመመዘንና ወካይ ናሙና ናቸው ለመባል የሚያበቃ ጥንካሬ እንዳልተገኘባቸው ጥናቱ አመልክቷል።

አምንታዊ ገፅታቸው ለፈተና ሲባል ማሻሻያ ያልተደረገባቸው /Authentic/ የሆኑ ሲሆኑ ተመጣጣኝነት ባይታይባቸውም ከሁለቱ የፅሑፍ አይነቶች (ከፈጠራዊና ከኢፈጠራዊ) የተወከሉ ናቸው። በተወሰነ ደረጃ ተፈታኞቹ በመማሪያ መፅሐፉ የተዋወቋቸው የፅሑፍ አይነቶች ነፀብራቆች ናቸው። ባንድ ፈተና የሚመረጡት ምንባቦች አጠቃላይ ስለሆኑ ጉዳዮች የሚያነሱ ቢሆኑም በአብዛኛው በይዘት የተለያዩ ናቸው።

በሌላ አቅጣጫ ደግሞ ምንም እንኳ እነዚህ አምንታዊ ጎኖች ቢታዩባቸውም ብዛት ያላቸው ድክመቶች (አሉታዊ ገፅታዎች) እንደሚታዩባቸው ትንተናው አመልክቷል። ከነዚህ ድክመቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፦

በተለያዩ የእይራረስ ስልቶች የተፃፉ ፅሑፎች የሚካተቱባቸው ሆነው ሊገኙ አልቻሉም። ከተወሰኑ ይራስያን ድርሰቶች የሚወሰዱ ስለሆኑ ሊሆን ይችላል የተለያዩ የአፃፃፍ መንገዶችን (style) የሚወክሉ አይደሉም። በምንባብ ብዛትም ተመራማሪዎችን በመዮቀስ እንደተገለፀው) ቢበዛ መነሻ እንጂ መድረሻ ሊሆን ባይገባውም በሞዴል ፈተናዎቹ ከፍተኛ የምንባብ ቁጥር ሦስት ነው። በዚህ በምንባቦቹ ቁጥር ማነስና በመሳሰሉት ሌሎች ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፤ በዝርዝር የፅሑፍ አይነትም ተማሪዎቹ ከትምህርት ቤት ውጭ ሊያጋዮሟቸው የሚችሏቸው የተለያዩ የፅሁቀት መስኮችን የመወከል አቅም ያላቸው ምንባቦች አልተካተቱባቸውም። ለእንባቦ መረጻት መፈተኛነት የሚመረጡ ምንባቦች በተቻለ መጠን ለተፈታኞቹ አይን እንግዳ የሆኑ እንዲሆኑ ጥረት መደረግ እንዳለበት የሚያመለክት መርህ ቢኖርም በነዚህ ፈተናዎች የተመረጡት አብዛኞቹ ከ"አሮጌ" መጻሕፍትና ከ12ኛ ክፍል መልቀቂያ የተለያዩ አመታት ፈተናዎች የተወሰዱ ሆነው ተገኝተዋል። በ4.1.1 በሰንጠረዥ '6' እንደቀረበውም የብዙዎቹ ምንባቦች ርዝመት ከግማሽ ገፅ በታች ነው። ከ113ቱ ምንባቦች ውስጥ ከአንድ ገፅ በላይ የሆኑት ጠጠኛ ብቻ ናቸው። ባንድ ምንባብ ተደጋፊነት የሌላቸው (ብዙ ጥያቄ) የማውጣት ልማድ ያለ መሆኑንም ጥናቱ አሳይቷል።

በመምህሩ መጠይቅ የምንባቦችን አመራረጥ በሚመለከት በተጠየቁት ጥያቄዎች የተሰበሰቡት መረጃዎችም አብረው በዚህ ክፍል ተተንትነዋል። ጥያቄዎቹ የመምህራኑ የምንባቦች አመራረጥ ሂደት ትምራዊ መርሆዎችንና አተያዮችን ያገናዘበ መሆን አለመሆን የሚጠይቁ ናቸው። ለነዚህ ጥያቄዎች ከተሰጡት መልሶች የተገኘው የመረጃ ውጤት ትንተና እንዳመለከተው ብዙዎቹ መላሾች ከመርሆዎቹና ሳይንሳዊ አተያዮች ጋር ተግራራ የሆነ አተያይ አላቸው። ይሀም ምናልባት በስልጠናም ሆነ በንባብ ግንዛቤያቸው ባለመዳበሩ የተነሳ የተከሰተ ሊሆን እንደሚችል ትንተናው ጠቁሟል።

ከምንባቦቹ አመራረጥ ግምገማ በመቀጠል በፈተናዎቹ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችና በአንብቦ መረዳት ፈተና ሊመዘኑ የሚገባቸው ክሂሎች መካከል ያለውን ተዛምዶ (የይዘት አግባብነት) ለመመርመር ተሞክሯል።

በዚህ ክፍል በቅድሚያ በቮክሊስቱ መሰረትነት የፈተናዎቹን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የመከፋፈል ተግባር በባለሙያዎቹ የተከናወነ ሲሆን በክፍፈላውም በአራቱ አመታት ከተጠየቁት 1187 ጥያቄዎች ውስጥ ሶስቱ (አራቱ) ከፋፋዮች በአከፋፈል የተስማሙባቸው 1118ቱ ላይ ትንተናው ተካሂዷል።

በዚያው ክፍል የቀረበው የሰንጠረዥ 13 ድምር እንደሚያሳየው የመጀመሪያዎቹን ሰባት ደረጃዎች የያዙት በተራ ቁጥር 3.2፣ 1.1-3፣ 4.2.1.1-3፣ 4.1.4-6፣ 2.1.3፣ 4.2.2.1-3፣ እና 1.1 የተወከሉት ክሂሎች ናቸው። እንዲሁም በተራ ቁጥር 5፣ 4.1.1፣ 4.1.3-5፣ የተመለከቱት ክሂሎች አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ጥያቄዎችም ቢሆን በአራቱም አመታት መሸፈናቸውን ትንተናው አረጋግጧል። የቀሩት በተራ ቁጥር 4.1.2፣ 4.1.6፣ 4.1.7፣ 4.1.8 የተወከሉት ክሂሎች ደግሞ ባንዱም አመት ባንድም ጥያቄ ተሸፍነው እንደማያውቁ የመረጃው ውጤት ትንተና አመልክቷል። ከነዚህ ውስጥ በተራ ቁጥር 4.1.6 የተወከለው "ከልዩ ልዩ መግለጫዎች የመረጃ ሀሳብ ማግኘት" የሚለው ከ9 ያላነሱ ንውሳን ክሂሎች በውስጡ የሚገኙበት ነው።

በዚሁ ክፍልም ሆነ በቀጣዩ ከክሂሎች መሸፈን አለመሸፈን የይዘት አግባብነት ጉዳይ ምርመራ በተጨማሪ የክሂሎቹን አወካከልም ለማየት የተሞከረ ሲሆን የተወሰኑት ክሂሎች ከበቂ በላይ የሆነ በሚመስል የጥያቄ ብዛት እንደተወከሉና የተወሰኑት ደግሞ በቂ፣ ወካይና ተመጣጣኝ ባልሆነ ናሙና እንደተወከሉ ትንተናው አሳይቷል።

የተወሰኑት፣ ብዛት ባላቸው ሊወከሉ የተወሰኑት አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ጥያቄዎች እንዲሁም የተወሰኑት ጭራሽ ሊወከሉ ያልቻሉበት ምክንያት በመማር ማስተማሩ ሂደት ከሚሰጣቸው ትኩረት አንጻር እንደሆነ ለማረጋገጥም በመምህሩ፣ መጠይቅ ከተሰበሰበው መረጃ ጋር በማዛመድ ለማየት ተሞክሯል። ሆኖም ከመምህራኑ በተገኘው መረጃና በፈተናዎቹ ጥያቄዎች የክሂሎቹ አወካከል መካከል ተዛምዶ አልታየም የሚባል ባይሆንም መምህራኑ በማስተማሩ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣቸዋል ካሏቸው ውስጥ በፈተናዎቹ ባነስተኛ ጥያቄዎች የተወከሉ መኖራቸውን ጥናቱ አመልክቷል።

የባለሙያዎቹን 1139 ጥያቄዎች ክፍፍል መሰረት በማድረግም በፈተናዎቹ ጥያቄዎችና በ12ኛ ክፍል መርሀ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ይዘትነት የቀረቡ ክሂሎች መካከል ያለውን የተዛምዶ /የይዘት አግባብነት/ ደረጃ ለመመርመር የተደረገው ትንተና በቮክሊስቱ

መሰረትነት የተካሄደው ትንተና ቀጣይ ክፍል ሲሆን በዚህ ትንተና የተገኘው ውጤት ከቀዳሚው (በቮክሲስቱ መሰረትነት ከተካሄደው) ብዙም የማይለይ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል። እንደ ቀዳሚው ሁሉ በዚህም በብዙ ጥያቄ የተወከሉ፣ በጥቂት ጥያቄ የተወከሉ፣ ባንድም ጥያቄ መወከል ያልቻሉ አሉ። ከነዚህ በተጨማሪ በሁለቱም (በቮክሊስቱም በመርሀ ትምህርቱም) መሰረትነት በተካሄዱት የባለመዛያዎቹ ልየታዎች:- 1. ሌሎች ክሂሎችን የሚመዝኑ፣ 2. እንብቦ መረዳትን የማይመዝኑ፣ 3. ምን እንደሚመዝኑ ለመለየት ያስቸገሩ ጥያቄዎች መካተታቸውን ትንተናው አመልክቷል።

በሌላ አቅጣጫ ደግሞ ብዛት ያላቸው ክሂሎች ባለመሸፈንና 'ሌሎች ክሂሎች' የሚለው ክፍል በአያሌ ጥያቄዎች መወከል የመርሀ ትምህርቱ ክፍል ከቮክሊስቱ የሚለይ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። በቮክሊስቱ 'ሌሎች ክሂሎች' የሚለው ለምሳሌ በ42 (3.76ፊ) ጥያቄ ነው የተወከለው። በመርሀ ትምህርቱ ግን በ446 (39.16ፊ) ጥያቄ ነው የተወከለው። ይህም በተወሰነ መልኩ ሲታይ መምህራኑ ባንብቦ መረዳት ትምህርት የምናስተምራቸው ክሂሎች በመርሀ ትምህርቱ የቀረቡትንና በራሳችን ዝግጅት የምንጨምራቸውን ነው ካሉት ጋር የሚገናኝ፣ አምንታዊ የባክዋሽ ውጤት ሊኖረውም የሚችል ቢሆንም በመሳሪያው (በመርሀ ትምህርቱ) ከቀረቡት ክሂሎች ውስጥ ብዙዎቹ ባንድም ጥያቄ ካለመሸፈናቸው አኳያ ሲታይ አሉታዊነቱ እንደሚኖላ ትንተናው አመልክቷል።

በዚሁ የትንተና ክፍል የይዘት አግባብነት ደረጃን ከፍ ማድረጊያ ስልትነት የሚታወቁትን የፈተና እዘገጃጀት ቅድመ ሁኔታዎች በሚመለከት በመምህሩ መጠይቅ የተጠየቁት ጥያቄዎች የተገኘው መረጃም አብሮ ተተንትኗል። ትንተናው እንዳመለከተውም አንዳንዶቹ መምህራን ስለነዚህ የፈተና ዝግጅት ቅድመ ሁኔታዎች (ስለይዘት/ክሂል ልየታ ...) ግንዛቤው የሌላቸው ይመስላል። እንዳንዶቹ ደግሞ ግንዛቤው ያላቸው ቢመስሉም ግንዛቤው በትምራ በሚታመንበት አቅጣጫ አይመስልም።

ከይዘት አግባብነት መረጃ ትንተናና ማብራሪያ በመቀጠል የላህይ አግባብነትን ለመመርመር በተግሪው መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ተተንትኗል። በትንተናውም አብዛኞቹ ተፈታኞች ባጠቃላይ የተፈተኑትን የሞዴል ፈተና በሚመለከት አምንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ለጥያቄ ቁጥር 2.1፣ 2.5 እና 2.8 ከሰጡት አስተያየት ማረጋገጥ ተችሏል። በተለይ የአንብቦ መረዳት ክፍሉን በሚመለከትም ብዛታቸው አጠቃላይ ፈተናውን በሚመለከት ተገቢነት ያለው ፈተና የሚመስል ነው ካሉት የሚያንስ ቢሆንም አብዛኞቹ አምንታዊ አመለካከት እንዳላቸው የመረጃ ትንተናው አሳይታል። በሌላ በኩል ደግሞ ላንድ ጥያቄ፣ ለጥያቄ 2.4 ከተሰጠው በቁር ለቀሩት 8 ጥያቄዎች አምንታዊ መልስ የሰጡት ከ70ፊ በታች የሆኑ ስለሆኑና ከነዚህ 70ፊ በታች የሆኑት ውስጥም ብዙዎቹ አልስማማም እና በጣም አልስማማም የሚል አስተያየት ስለሰጡ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ተፈታኞች ቁጥርም ቀላል እንዳይደለ ትንተናው አመልክቷል።

በመጨረሻ የቀረበው የመረጃ ትንተና የአጠያየቅ ዘዴዎቹን ብቃት የሚመለከት ነው። በዚህ የትንተና ክፍል 1. በሞዴል ፈተናዎቹ ያጠያየቅ ዘዴዎችና በተለያዩ ተመራማሪዎች አንብቦ መረዳትን ለመፈተኛነት ብቃት እንዳላቸው በተመሰከረላቸው ያጠያየቅ ዘዴዎች፣ 2. በሞዴል ፈተናዎቹ ያጠያየቅ ዘዴዎችና በመማሪያ መፅሐፉ ያጠያየቅ ዘዴዎች መካከል ያለው ተዛምዶ የተመረመረ ሲሆን በሁለቱም ክፍሎች ሆን ተብሎ የተፈጠረ ቀርቶ ባጋጣሚ የተከሰተ ሊመስል የሚችል ተዛምዶ እንኳ እንደሌለ የትንተናው ውጤት አረጋግጧል። ከዚህም በተጨማሪ የአራቱም አመታት ፈተናዎች አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የተጠቀሙበት ዘዴ አንድ ብቻ እንደሆነና እሱም አንብቦ መረዳትን ለመፈተን ዝቅተኛ ቦታ የሚሰጠውና በብዙ አገሮች፣ ብዙ የተግሪ ቁጥር ባላቸው በነጥይና ሳይቀር እየተተወ የመጣው ምርጫ ሰጭ እንደሆነ ትንተናው አሳይቷል።

ያጠያየቅ ዘዴዎችን በሚመለከት ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና ያመለከተው ግን ብዛት ያላቸው መምህራን የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎችን በፈተናዎቹ እንደሚጠቀሙ፣ ተግሪዎች በመማሪያ መፅሐፋቸው የተለማመዷቸውን ያጠያየቅ ዘዴዎች በፈተናዎቹ እንደሚንፀባረቁ እንደገለፀ ነው። ይህም ባይፈፅሙትም መሆን ያለበትን ከመገንዘብ የተሰነዘረ ሊሆን እንደሚችል ነው። እውነታውን የገለፀት ቁጥርም ቀላል አይደለም። የነዚህኞቹ ደግሞ የአጠያየቅ ዘዴዎቹ ውስን መሆን የሚያስከትለውን አደጋ ካለማወቅ የመነጨ ይመስላል የሚል እንድምታ ተሰጥቶበታል።

5.2 መደምደሚያ /Conclusion/

በዝርዝር የቀረቡትን የጥናቱን ውጤቶችና ማጠቃለያውን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ከቀረቡት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል።

1. አንብቦ መረዳትን ለመፈተን የተመረጡት ምንባቦች ከምንባብ አመራረጥ መርሆዎችና ቴክኒኮች አኳያ ሲታዩ የተወሰኑ ጠንካራ ጎኖች ቢኖራቸውም ደካማ ጎናቸው የጎላ ነው። ከምክንያቶቹ አንዱም መምህራኑ ከሳይንሳዊ የምንባቦች አመራረጥ መርሆዎች፣ ቴክኒኮችና አቀያየሶች ጋር በቂ ትውውቅ የሌላቸው መሆን እንደሆነ ተገምቷል። መምህራኑ በመጠይቁ ይህንኑ (የምንባቦችን አመራረጥ) አስመልክቶ ለተጠየቁት የሰጧቸው መልሶች ይህንኑ ድምዳሜ የሚያጠናክሩ ናቸው። ሀላፊነትን ለመወጣት አለመትጋት (ለሀላፊነት ግዴለሽ መሆን) ሊላው ምክንያት ሊሆን ይችላል።

2. በየክለስቱ ከተለዩት የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ውስጥ አብዛኞቹ በአራቱም አመታት በሞዴል ፈተናዎቹ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መሸፈን ችለዋል። በ16 ክፍሎች /Categories/ ተመድበው ከቀረቡት ውስጥ ያልተሸፈኑት በቁጥር 4.1.2፣ (የዐ.ነገሮችንና የአንቀፆችን ተግባቦታዊ ተግባር መረዳት) 4.1.6፣ (በስንጠረዥ፣ በግራፍ... የቀረቡ

መረጃዎችን መረዳት) 4.1.7 (ማሳጠር) እና 4.1.8 (መተንበይ) የተወከሉት ክፍሎች ብቻ ናቸው። ሆኖም በነዚህ ባልተሸፈኑት ውስጥ የሚገኙትንዐሳን ክሂሎች በተለያዩ ምርምሮች ባንብቦ መረዳት ትምህርትም ሆነ ፈተና ከፍተኛ ትኩረት ሊያገኙ የሚገባቸው እንደሆኑ የሚመስከርላቸው ከመሆናቸው አኳያ ሲታይ አሸፋፈኑ በአምንታዊነት ጎን ብቻ እንዳይፈረጅ አሉታዊ የሆነ የባክዋሽ ውጤትም የሚታይበትም እንዲመስል ያደረገው ይመስላል።

3. በቮክሊስቱ ከተለዩት ክሂሎች ውስጥ በፈተናዎቹ ጥያቄዎች መወከል የቻሉት አወካከል፡- በቂ ወካይና ተመጣጣኝ በሆነ ናሙና ነው ሊባል የሚችል አይመስልም። ናሙናው በቂ፣ ወካይና ተመጣጣኝ ካልሆነ ደግሞ የፈተናዎቹ የይዘት አግባብነት ደረጃ አምንታዊ ሊሆን አይችልም።

4. በ12ኛ ክፍል መርሀ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ይዘትነት ከቀረቡት ክሂሎች ውስጥ በፈተናዎቹ ጥያቄዎች ብዙዎቹ ቢሸፈኑም፣ ያልተሸፈኑትም ቁጥር ጥቂት አይደለም። በተለይ በተራ ቁጥር 2፣ 13፣ የቀረቡት በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የመጀመሪያው ከዘጠኝ ሁለተኛው ከስድስት ያላነሱ ክሂሎችን በውስጣቸው የያዙ ሆነው ሳለ ባንድም አመት ባንድም ጥያቄ መሸፈን አለመቻላቸው ሂዩዝ (1995) እንዳሉት መምህራኑ የሚፈትኑት መፈተን ያለባቸውን ሳይሆን ለመፈተን አመች የሆኑላቸውን ነው ወደሚል ድምዳሜ የሚመራ ይመስላል። በዚህ የተነሳ ይሁን በሌላ ምክንያት መመዘን ካለባቸው ክሂሎች ብዙዎቹ አለመሸፈናቸው የይዘት አግባብነቱን ደረጃ ዝቅ ያደረገው ይመስለናል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከሰንጠረዥ 18 ና 19 መረዳት እንደሚቻለው በተወሰኑ አመታት በፈተናዎቹ ጥያቄዎች ተሸፍነው በተወሰኑት ያልተሸፈኑ ክሂሎች መኖርም ፈተና አዘገጃጀቱ ወጥነት /consistency/ የሌለው በዘፈቀደ የሚመራ (የይዘት/ክሂል ልየታን መሰረት የማያደርግ) እንዲመስል ያደረገው ይመስላል።

5. በመርሀ ትምህርቱ ያልተካተቱ ክሂሎች ከጠቅላላው ጥያቄ ከ⅓ በላይ የሆነ ቁጥር ባላቸው ጥያቄዎች ተወክለው መገኘት አምንታዊ የባክዋሽ ውጤት ሊኖረው ቢችልም ብዛት ያላቸው በመሳሪያው (በመርሀ ትምህርቱ) የቀረቡት ክሂሎች ከመዘንጋታቸው አንፃር ሲታይ ግን በአሉታዊ አሰራርነት እንዲፈረጅ ሊያደርገው የሚችል ይመስላል።

6. እንደቮክሊስቱ ሁሉ በመርሀ ትምህርቱ ከተካተቱት ክሂሎች ውስጥ በፈተናዎቹ ጥያቄዎች መሸፈን የቻሉት ክሂሎች አወካከል በቂ፣ ወካይና ተመጣጣኝ በሆነ ናሙና ነው ለማለት የሚያስችል መስሎ አይታይም።

7. የሞዴል ፈተናዎቹ ለአብዛኞቹ ተፈታኞች ተገቢ የመመዘኛ መሳሪያ መስለው የሚታዩ ሆነው ተገኝተዋል። ይሁን እንጂ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ተፈታኞች በተለይ ለአንብቦ መረዳት ክፍሉ አሉታዊ የሆነ አመለካከት ያላቸው ይመስላል። ከቋንቋ ፈተና ብያኔ፣ ከቋንቋ ፈተና ይዘት መሠረቶችና ከይዘት አግባብነቱ ትንተና ግኝቶች አኳያ ከታየ ግን ትክክለኛ አስተያየት የሚመስለው የአንብቦ መረዳት ክፍሉ ተገቢ የመመዘኛ መሳሪያ አይመስልም ያሉት ነው።

8. የሞዴል ፈተናዎቹ ያጠያየቅ ዘዴዎች በተለያዩ ተመራማሪዎች ከሚታመንባቸው የአንብቦ መረዳት ክሂሎች መፈተኛ ዘዴዎች ጋርም ሆነ ተማሪዎች በመማሪያ መፅሐፋቸው ከተለማመዷቸው ያጠያየቅ ዘዴዎች ጋር ተዛምዶ ያላቸው ሆነው አልተገኙም።

9. ብዛት ካላቸው ያጠያየቅ ዘዴዎች ውስጥ ሁሉም ፈተናዎች አንድ (ምርጫ ስሮጡን) ብቻ የሚጠቀሙ ሆነው መገኘት፣ በተፈታኞቹ የፈተና አሰራርና ውጤት ላይ ተፅዕኖ የሚኖረው ከመሆኑ በተጨማሪ አሉታዊ የባክዋሽ ውጤትም ይኖረዋል።

10. ባጠቃላይ በናሙና ትምህርት ቤቶች ከ1987 - 1990 የተሰጡት የሞዴል ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ክፍል የይዘት አግባብነትና ያጠያየቅ ዘዴዎች ከጠንካራ ጎናቸው ይልቅ ደካማው የሚጎላ ነው። የምንባቦቹና ያጠያየቅ ዘዴዎቹ አመራረጥ የሚታመንባቸውን መርሆዎች፣ መመዘኛዎችና አተያየቶች መሰረት ያደረገ ሳይሆን ዘፈቀዳዊ የሚመስል ነው። ምንባቦቹ ወካይና የተለያዩ ክሂሎችን ለመመዘን የሚያስችሉ መስለው የሚታዩ አይደሉም። ያጠያየቅ ዘዴዎቹም እንዲሁ የተለያዩ ክሂሎችን ለመመዘን የሚያስችሉ፣ በተለያዩ ተመራማሪዎች የሚደገፉትን የአመራረጥ መርሆዎችና ቴክኒኮች በተወሰነ ደረጃ እንኳ ሊከተሉ የቻሉ፣ የመማሪያ መፅሐፉ ያጠያየቅ ዘዴዎች ነፀብራቆች የሆኑ አይደሉም። በቸክሊስቱ የተለዩትም ሆኑ በመርሀ ትምህርቱ የአንብቦ መረዳት ይዘትነት የቀረቡት ክሂሎች፣ አብዛኞቹ በፈተናዎቹ ጥያቄዎች መሸፈን ቢችሉም ያልተሸፈኑትም መሸፈን የነበረባቸው ናቸው ግለት ይቻላል። የተሸፈኑትም በጥያቄዎቹ ያላቸው ውክልና በቂና ወካይ የሆነ ተመጣጣኝነት የሚታይበት ናሙና ሆኖ የተገኘ አይመስልም። የነዚህ አሉታዊ ነኖች ድምርም የፈተናዎቹን የይዘት አግባብነት ደረጃ ዝቅተኛ ነው ለመባል ያበቃው ይመስላል። ከሁሉም የአምንታዊነት ደረጃ ከፍ ብሎ የተገኘው የፈተናዎቹ የላህይ አግባብነት ብቻ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

5.3 ጥቆማ /Recommendations/

ከጥናቱ ውጤቶችና ከመደምደሚያዎቹ በመነሳት የሚከተሉት ጥቆማዎች ተሰንዝረዋል።

ሀ. በትምህርት ቤት ደረጃ፦

1. አንብቦ መረዳትን ለመፈተን ምንባቦች ሲመረጡ የአመራረጥ መርሆዎችን... መሰረት በማድረግ ቢሆን /የሚሆንበት መንገድ ቢፈለግ/፣
2. ባጠቃላይ መመዘን የሚገባቸውን የክሂልና/የፅውቀት ክፍሎች፣ በተለይ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን በፈተናዎች ሀ. ለመሸፈን፣ ለ. በበቂ፣ ወካይና ተመጣጣኝ ናሙና ለመወከል የሚያስችል የይዘት /የክሂል/ የባህሪ... ልየታ የመጠቀም ልማድ ቢዳብር፣ በፅሑፍ የሰፈረ መምሪያም ቢዘጋጅ፣
3. በየትምህርት ቤቱ ያሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ክፍሎች ለምሳሌ የትምህርት ክፍሉ ተቀዳሚ መምህራን መመሪያው በሚያዘው መሰረት ፈተናዎቹ ከመሰጠታቸው በፊት ብቃት ጉድለታቸውን ያለይሉኝታ በአግባቡ

እየመረመሩ ቢያላልፉና ጉድለት የሚበዛባቸው እንደገና እንዲዘጋጁ ቢያደርጉ፤

4. በየትምህርት ቤቱ በትምህርት ክፍሉ ተቀዳሚ መምህር ሰብሳቢነት በሚካሄዱት ስብሰባዎች /ውይይቶች/ በፈተና አዘገጃጀት፤ በክሂሎቹ ንዑሳን ክሂሎች እንዴት እንፈትንና በፈተናዎች ብቃት-ጉድለት ላይ የመወያየት ባህል ቢፈጠር፤
5. የእንብቦ መረዳት ፈተና ሲዘጋጅ አንብቦ መረዳትን ለመፈተን ብቃት እንዳላቸው የተመሰከረላቸውን በክለሳው ክፍል (በ7.2.2 የቀረቡትን) የአጠያየቅ ዘዴዎች ለመጠቀም ቢሞክር፤
6. በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ከሚያስተምሩ የትምህርት ክፍሉ መምህራን የተውጣጣ የፈተና ኮሚቴ ቢቋቋምና በየጊዜው የተሰጡና የሚሰጡ ፈተናዎችን እየገመገመ የፈተናዎች አዘገጃጀት የሚሻሻልበትን መንገድ ቢፈልግ፤

ለ. ከትምህርት ቤት ውጭ

በተለያዩ የጥናቱ የትንተና ክፍሎች ከሌሎች መረጃዎች ጋር በማዋሀድ የተካሄደው ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና እንዳመለከተው መምህራኑ በጥቅሉ ስለፈተና፤ በተለይም ስለአንብቦ መረዳት ፈተና አዘገጃጀት በቂ የሆነ ሳይንሳዊ ግንዛቤ እንደሌላቸው መረዳት ተችሏል። ብዙዎቹ ድክመቶች የተከሰቱት ከግንዛቤ ማነስ ነው የሚመስለው። ዌየር (1993፤ 6) እና ሌሎችም ዘመናዊ የቋንቋ ፈተና ተመራማሪዎች እንደሚያስረዱት ደግሞ የማስተማሪያ መሳሪያዎች በዘመናዊ መንገድ ቢዘጋጁ፤ መምህራኑ በዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ቢካኑ፤ .... ከነሱ ጋር የሚስማማ ዘመናዊ የቋንቋ አፈታተን መንገድ ከሌለ ሌሎቹ ድካሞች ሁሉ ከንቱ ከመሆን ሊያልፉ አይችሉም። ስለዚህ፦

1. የመምህራን አስልጣኝ ተቋማት ይህን ችግር በመገንዘብ፤ የሚያስለጥኗቸው አጪ መምህራን ስለፈተና አዘገጃጀት በቂ ዕውቀት ይዘው የሚወጡበትን መንገድ ቢፈልጉ፤
2. የሚመለከታቸው ክፍሎች/ለምሳሌ ትምህርት ሚኒስቴር/ ከላይ እንደተገለፀው ፈተና የመማር ማስተማሩ ቁልፍ አካል እንደሆነ በመገንዘብ በስራ ላይ ያሉ መምህራን የሚሳተፉባቸው ልዩ ልዩ ስልጠናዎች፤ ወርክሾፖች፤ ሴሚናሮች እንዲዘጋጁ ቢያደርጉ፤

3. እያንዳንዱን ክሂልና በየክሂሉ የሚታቀፉትን ንዑሳን ክሂሎች እንዴት መመዘን እንደሚቻል የሚመራ/ሩ/ መምሪያ/መምሪያዎች/ በማዕከል ተዘጋጅተው በየትምህርት ቤቶቹ የሚገኙበት መንገድ ቢፈጠር፣
4. ፈተናን በሚመለከት ታትመው የወጡ መጻሕፍትና ሌሎች ጠቃሚ ፅሑፎች በየትምህርት ቤቶቹ መጻሕፍት ቤቶች የሚገኙበት መንገድ ቢፈጠርና መምህራን በንባብ ግንዛቤያቸውን እንዲያጎለብቱ በጎ ግፊት ቢደረግ።

ዋቢ ፅሑፎች (Bibliography)

ማስተዋል ውበቱ። 1989። " የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የተካሄደ ጥናት። " (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

በየነ ማሞ። 1985። "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋን ክሂሎች የሚያዳብሩ ናቸው።" (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ተስፋዩ ሸዋዬ። 1981። ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር። አዲስ አበባ፤ ያልታተመ)።

ትምህርት ሚኒስቴር። 1984። የአማርኛ መማሪያ (9-12ኛ ክፍል)። አዲስ አበባ፤ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት።

_____ ። 1984። የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ (9-12ኛ ክፍል)። አዲስ አበባ፤ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት።

ትንሳኤ ብርሃኔ። 1988። "የአማርኛ የቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት።" (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ጌታቸው አዱኛ። 1986። "ለአስረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ።" (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

Adams-Smith, D.E. 1981. Level of Questioning: Teaching Creative Thinking Through ESP. English Teaching Forum, 21: 15-17.

Alderson, J.C. 1988. "Testing Egnlish for Specific Purposes: How Specific Can We Get?" in A. Aughes (ed.), pp. 16-28.

Alderson, J.C. and A.H. Urquhart. 1984. "Introduction." in J.C. Alderson and A.H. Urquhart (eds.), pp. xv-xxviii.

Alderson, J.C. and A.H. Urquhart (eds.). 1984. Reading in a Foreign Language. London: Longman.

Alderson, J.C. and Y. Lukmani. 1989. "Cognition and Reading: Cognitive Levels as Embodied in Test questions." Reading in a Foreign Language. 52: 253-270.

Alderson, J.C., C. Clapham and D. Wall. 1995. Language Test Construction and Evaluation. Cambridge: Cambridge University Press.

Alemu Tesgaw. 1983. "Assessment of Grades Six and Eight English National Examination." (unpublished MA Thesis, A.A.U.)

Anastasi, A. 1982. Psychological Testing (Fifth ed.), New York: Macmillan.

Babbie, Earl. 1992. The Practice of Social Research (6th ed.), Belmont: Wadsworth Publishing Company.

Bachman, L.F. 1995. Fundamental Consideration in Language Testing (Third impression.), Oxford: Oxford University Press.

Bachman, L.F. and A.S. Palmer. 1997. Language Testing in Practice. Oxford: Oxford University Press.

Beard, R. 1987. Developing Reading 3-13. London: Hodders and Staughton.

Bloom, B.S., etal. 1956. Taxonomy of Educational Objectives: The Classification of Educational Goals, Handbook 1 Cognitive Domain. New York: David Mckay.

Brown, Annie. 1993. "The Role of Test-Taker Feedback in the Test Development process: Test Takers' Reactions to a Tape-Mediated test of Proficiency in Spoken Japanise" Language Testing. 10/3: 276-296.

Brown, J.D. 1994. Principles of Language Learning and Teaching. New Jersey: Protice Mull Regent.

Chikalanga, Issrael. 1992. " A Suggested Taxonomy of Inferences for Reading Teacher." Reading in a Foreign Language. 8/2: 697-707.

Candlin, C.N. 1994. From Testing to Assessment: English as an International Language. London: Clifford Hill and Hate parry.

Carroll, B.J. 1980. Testing Communicative Performance. Oxford: Pergamon.

Clapham, Carolin. 14 Nov. 1997. "Concepts in Language Testing." Institute of Language Studies. Addis Ababa University, Addis Ababa. (Lecture Note).

_____. 15 Nov. 1997. "The Effect of Background knowledge on Reading Comprehension." Institute of Language Studies. Addis Ababa University, Addis Ababa. (Lecture Note).

_____. 15 Nov. 1997. "Testing Reading." Institute of Language Studies. Addis Ababa University, Addis Ababa. (Lecture Note).

Davis, A. (ed.). 1968. Language Testing Symposium: A Psycholingustic Approach. London: Oxford University Press.

_____ 1988. "Communicative Language Testing." in A. Hughes (ed.), pp. 5-14.

_____ 1991. "Language Testing in the 1990s" in C.Alderson and B. North (eds.), Language Testing in the 1990s. Modern English publication and the British Council, Macmillan Publishers Ltd., Great Britain.

Dejenie Leta. 1990. "How can we Improve the English Language Component of the Ethiopian School Leaving Certificate Examination (ESLCE)?" Addis Ababa (unpublished paper).

_____ 1994. "Language Testing and its practical Application. (The Testing of Reading in Focus)." Addis Ababa. (unpublished paper).

Greenall, S. and M. Swan. 1991. Effective Reading Skills for Advanced Students (5th printing.), Cambridge: Cambridge University Press.

Grellent, F. 1981. Developing Reading Skills: A Practical Guide to reading Comprehension Exercises. New York: Cambridge University Press.

Gronlund, N.E. 1988. How to Construct Achievement Tests (Fourth Ed.), New Jersey: Printice Hall, Inc.

Gronlund, N.E. and L.L. Robert. 1990. Measurement and Evaluation in Teaching. New York: Macmillan publishing Co.

Harlen, W. (ed.). 1994. Enhancing quality in Assessment. London: Paul Chapman Publishing Ltd.

_____ 1994. "Introduction." In W. Harlen (ed.), pp.1-10.

_____ 1994. "Issues and Approaches to Quality Assurance and Quality Control in Assessment." In W. Harlen (ed.), pp.11-24.

Harrison, A. 1983. A Language Testing Handbook. London: Macmillan Press.

Harris, M. and P. McCan. 1994. Assessment. Scotland: Heinemann.

Heaton, J.B. 1975. Writing English Language Tests. London: Longman.

_____ 1990. Classroom Testing. London: Longman.

_____ 1991. Writing English Language Tests (4th impression.), London: Longman.

Hopkins, C.D. and Richard L. Antes. 1989. Classroom Testing: Construction (Second Ed.), U.S.A.: F.E. Peacock Publishers, Inc.

Huges, A. 1988. "Achievement Proficiency: The Missing Link?" In A. Huges (ed.), pp. 36-42.

_____ (ed.) 1988. Testing for University Study ; ELT Documents 127. London: Modern English Publications.

_____ 1995. Testing for Language Teachers (Second ed.), Cambridge: Cambridge University Press.

Koul, Lokesh. 1996. Methodology of Educational Research (Second Revised Ed.), New Delhi: Vikas Publishing House PVT. Ltd.

Lado, R. 1961. Language Testing: The Construction and Use of Foreign Language Tests. London: Longman.

Lumley, Tom. 1993. "The Notion of Subskills in Reading Comprehension Tests: An EAP Example." Language Testing. 10/3: 211-234.

_____ 1995. "Replies" to Alderson, J.C. 'Responds.' Language Testing. 12/1: 125-129.

Madsen, H.S. 1983. Techniques in Testing. New York: Oxford University Press.

Marew Zewdie. 1992. "The Objectives and Content of the Ethiopian School English Syllabus: Its Adequacy, Relevance and Effectiveness." The Ethiopian Journal of Education. xiii/1: 1-40.

Munby, J. 1978. Communicative Syllabus Design. Cambridge: Cambridge University Press.

Nasr, Raja T. 1979. Teaching and Learning English (Fourth impression.), London: Longman.

Nuru Mohammed. 1992. "Levels of Questions: A Description of Textbook and Exam Questions in Higher Secondary Schools." (unpublished MA Thesis, Addis Ababa University).

Nuttal, C. 1982. Teaching Reading Skills in a Foreign Language. London: Heinemann.

Oller, John W Jr. 1979. Language Test at School: A Pragmatic Approach. London: Longman.

Satterly, David. 1994. "Quality in External Assessment." in Wynne, Harlen (ed.), pp. 53-68.

Spolsky, B. 1976. "Language Testing: Art or Science?" Proceedings of the Fourth International Congress of Applied Lingustics. Stuttgar: HochSchulverlog, Germany.

Stavans, A. and O. Brenda. 1993. "Assessing EFL Reading Comprehension: The Cause of Ethiopian Learners." System. 21/4: 481-493.

Spratt, M. 1988. "Reading Skills." In Matthews, Alan, Mary, Spratt and Les Dongersfield (eds.), At the Chalk Face: Practical Techniques in Language Teaching. London: The Bath Press.

Sunderland, Jane. 17 Nov. 1997. "Gender and Language Testing." Institute of Language Studies. Addis Ababa University. Addis Ababa. (Lecture Note).

Tesfahun Alemu. 1997. "Comparative Evaluation of the Validity of the Sixth Grade National and Regional Exams: In particular Reference to Gambela." (unpublished MA Thesis. A.A.U.)

Teshome Demisse. 1995. "The Construction and Validation of a Test of English for Tertiary Education with Reference to Addis Ababa University." (unpublished Ph.D Thesis. Addis Ababa).

Weir, C.J. 1988. "The Specification, Realisation and Validation of an Egnlish Language Proficiency Test." In A. Hughes (ed.), pp. 45-110.

_____ 1990. Communicative Language Testing. New York: Prentice Hall.

_____ 1993. Understanding and Developing Language Tests. London: Prentice Hall.

_____ 1997. "The Testing of Reading in A Second Language." in Language Testing and Assessment. Vol. 7. (Photocopied material).

Williams, E. 1984. Reading in the Language Classroom. London: McMillan Publisher Ltd.

Yalden, Janice. 1987. Principles of Course Design for Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Yusuf Omer Abdi. 1976. "A Descriptive Analysis of the Content Validity of the History Examination of the Ethiopian Secondary School Leaving Certificate." (upublished Ph.D Thesis. Southern Illnois University).

አባሪ ሀ

አማርኛን በማስተማር ሂደት በ12ኛ ክፍል ፈተናዎች በአንብቦ መረዳት ክፍል ሊመዘኑ የሚገባቸው ንዑሳን የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ቸክሊስት መፍቻ።

1. ቃላትና ሀረጎች

በፅሑፉ ውስጥ በግልፅ ከሰፈሩና ካልሰፈሩ መረጃዎችና ፍንጮዎች ወይም ከቀደመ ዕውቀት /Background knowledge/ በመነሳት ወይም ሁለቱንም በቅንጅት በመጠቀም፦

1.1 እንግዳ ያልሆኑ ቀጥተኛ /የመዝገበ ቃላት/ ትርጉማቸውን ይዘው የገቡ ቃላትንና ሀረጎችን ፍች መረዳት፣

1.2 አሻሚ /የተለያየ ፍች/ ያላቸው ቃላትና ሀረጎች በገቡበት አውድ የያዙትን ፍች መረዳት፣

1.3 የእንግዳ ቃላትን /unfamiliar lexical items/ ፍች ከቃላት ምስረታና ከአውድ ፍንጭ/ምች/ መረዳት፣

1.4 የፈሊጣዊ አነጋገሮችን ፍች ከአገባባቸው መረዳት፣

1.5 የዘይቤያዊ አገላለፆችን ፍች ከገቡበት አውድ መረዳት፣

1.6 የተረትና ምሳሌዎችን ፍች ከገቡበት አውድ መረዳት፣

2. አያያዦች (Cohesion Devices — Linking words; Logical Devices; Grammatical, lexical items)

2.1 ወኪሎችን /references/ መረዳት፣ ለምሳሌ ተውላጠ ስሞችን

2.2 የአገባብ (ዲስኩር) አመልካቾችን /discourse markers/ መረዳት፣

ለምሳሌ የጊዜ አመልካቾችን /መጀመሪያ፣ ቀጥሎ፣ በሚቀጥለው ..../

የፅሑፍ (ዲስኩር) አደረጃጀትን (ከዚህ ጋር፣ ባጭሩ፣ .... የሚሉት አይነቶችን)

2.3 የወኪሎችንና የአገባብ (ዲስኩር) አመልካቾችን አገባብ በመገንዘብ በዐረፍተ ነገር፣ በዐረፍተ ነገሮችና በአንቀፆች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን መረዳት፣

3. አሰሳ ንባብ

3.1 የፅሑፍን ዋና ሀሳብ በፍጥነትና ቅኝት ንባብ /skimming/ መረዳት /understanding the gist of a text/፣

3.2 የተለየ መረጃን በፍጥነትና ቅኝት ንባብ /scanning/ ፈልጎ ማግኘት /to locate specific information/፣

4. ጥልቅ ንባብ

4.1 በግልፅ የሰፈሩ ሀሳቦችና መረጃዎች ተኮር

4.1.1 የዐረፍተ ነገርን ትርጉም መረዳት፣

4.1.2 የፀረፍተ ነገሮችንና የአንቀፆችን ተግባቦታዊ ተግባር /value (function/ በግልፅ ከሰፈሩ ጠቋሚዎች /indicators/ መረዳት፣ ምሳሌ በያኝ /definition/፣ ምሳሌ ... መሆናቸውን መረዳት፣

4.1.3 ዋና ዋና ሀሳቦችን ከዝርዝር ሀሳቦች መለየት፣ (Distinguishing the main ideas from supporting details)፣

4.1.4 እውነታን ከአስተያየት መለየት (Distinguishing fact from opinion)፣

4.1.5 ምሳሌን /ማስረጃን/ ከመሪ ሀሳብ መለየት /Distingushing example from statement or generalisation/፣

4.1.6 በስንጠረዥ፣ በግራፍ፣ .... የቀረበን መረጃ መረዳት፣

4.1.7 ማሳጠር /summary writing/፣

4.2 ኢንፈረንስ . በፅሑፍ ውስጥ በግልፅ ያልቀረቡ ሀሳቦችንና መረጃዎችን መረዳት

4.2.1 እውደ ፍች ተኮር ኢንፈረንስ . አንባቢው ከፅሑፉ ይዘት ፍች በመነሳት ያለፈ ፅውቀቱን ሳይጠቀም የሚረዳው (.... logically derived from the semantic content of the text/ ሲሆን በውስጡም የሚከተሉትን ዋና ዋና ክሂሎች የያዘ ነው።

4.2.1.1 የተለዩ መረጃዎችን /referential/ መለየት፣

. የተለዩ ሰዎችን፣ መሳሪዎችን፣ ፅቃዎችን መለየት፣

4.2.1.2 ቦታ . ጊዜያዊ /Spatio - temporal/

- ቦታዎችን፣ ጊዜያትንና የሁነቶችንና የድርጊቶችን አውደ መረዳትና ለማን ? ምን? የት? መቼ? ጥያቄዎች መልስ የማግኘት ክሂልን፣

4.2.1.3 ተጠየቃዊ ገላጭ /logical explanatory

. መነሳሳትን /መቀስቀስን (motivation)

- ምክንያት . ውጤቶችን (causative) መረዳት፣

4.2.2 እውደ ፍች ተኮር ያልሆነ ኢንፈረንስ /pragmatic inference/ በቀጥታ በፅሑፉ ከሰፈረ ሀሳብና መረጃ የማይገኝ ወይም የአንባቢውን የቀደመ ፅውቀት /the reader's store of prior knowledge (schemata) የሚጠይቅ ሀሳብንና መረጃን የመረዳት ክሂልን የሚመለከት ሲሆን በውስጡም -

4.2.2.1 አብራሪያዊ መረጃዊ /Elaborative informational/ ኢንፈረንስን፣

. የተለዩ መረጃዊ

. ቦታ.ጊዜያዊ

4.2.2.2 አብራሪያዊ ገላጭ /elaborative explanatory/ ኢንፈረንስ

. መቀስቅሳዊ

. ምክንያት፣ ውጤታዊ፣

4.2.2.3 ግምገማዊ /evaluative/ ኢንፈረንስ የሚባሉትን ክሂሎች ያቀፈ ነው።

አባሪ ለ

የ12ኛ ክፍል የአማርኛ መርሀ ትምህርት ቡ"የማንበብ ክሂልን ያዳብራል" አጠቃላይ አላማ ስር ሁለት የአንብቦ መረዳት ነክ ግለትም " አንብቦ ሀሳቦችን ይገነዘባል"ና ፍሬ ሀሳቦችን ከዝርዝር ሀሳቦች አንብቦ መለየት ይችላል ዝርዝር አላማዎች ግብ ማድረሻነት በይዘትነት የተመረጡ ክሂሎች ዝርዝር በዋናቱ ትንተና ከተሰጣቸው ተራ ቁጥር አንፃርና ሌሎች በአጭሩ የታከሉ ሶስት ክፍሎች (ተራ ቁጥር 14፣ 15ና 16)።

1. በአስላ ንባብ የሚፈለጉ ነጥቦችን ማግኘት	2. ከልዩ ልዩ መግለጫዎች የመረጃ ሀሳቦችን ማግኘት							
	1. ከሥዕላ ሰዕል	2. ከርዕ ግራፍ	3. ከግርጌ መግለጫ	4. ከሰን ጠረጰ	5. ከካ ርታ	6. ከቅርፃ ቅርፅ	7. ከኅ ራፍ	8. ከተጨማሪ ማብራሪያ	9.ከግርጌ ማስታወሻ

3. ቀና ቀናና ንዑስ ርእሶች	4. ፍሬ ነገሮች፣ መንደርደሪ ያዎች	5. የድርጊቶችና የጊዜ ቅደም ተከተል	6. የመንስኤና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት	7. መደምደሚያ ወይም ውሳኔ ሀሳብ ላይ ለመድረስ	
				7.1 ሁኔታዎችን ተመልክቶ ነው እያሉ መደምደም	7.2 ሁኔታዎችን ተመልክቶ ይሆናል እያሉ መደምደም

8. አንድን ነገር ወይም ሁኔታ ከሌላ ነገር ወይም ተመሳሳይ ሁኔታ ጋር ማነፃፀር /አናሎጂ/	9. የሚያስፈልጉ ቅና የማያስፈልጉ ዝር ዝር ሁኔታዎ ችን መለየት	10. የማወዳደር ችሎታ	11. በሀቅና በስሜታዊ አስተያየት መካከል ያለው ልዩነት	12 ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ	13 ሌሎች	14 በሲለበሱ ያልተካተቱ የአንብቦ መረዳት ክሂሎች

15 ለመለየት ያስቸገሉ (ጥያቄዎች)	16 የአንብቦ መረዳት ክሂል ያልሆኑ፣

ማሳሰቢያ - ሌሎች የሚለው ክፍል በሲለበሱ ውስጥ 1. የቤተ መጻሕፍት አጠቃቀም፣ 2. በቡድንና በተናጠል ድምፅን ከፍ አድርጎ ማንበብ፣ 3. ጥሩ የማንበብ ልምዶችን መመስረት፣ 4. በዝግታ አንብቦ ሐሳብን መረዳት፣ 5. በፍጥነት አንብቦ ሀሳብን መረዳት፣ 6. የመረጃ መጻሕፍት አጠቃቀም፣ 6.1. የአውደ ጥበብ (ኢንሳይክሎፒዲያ)፣ 6.2. የአልማናክ አጠቃቀም፣ በሚል መጠሪያ የተካተቱትን የሚያቅፍ ነው።

አባሪ ሐ

በ12ኛ ክፍል የእግርኛ ሞዴል ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ክሂሎች አፈታተን የይዘትና የላህይ አግባብነትና ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት ለማጥናት የተዘጋጀ መጠይቅ፣ ከ1986-1990 12ኛ ክፍል እግርኛ በአስተማሩና በሚያስተምሩ መምህራንና ተቀዳማ መምህራን ብቻ የሚሞላ

ውድ መምህራን!

የዚህ መጠይቅ አላማ በ12ኛ ክፍል የእግርኛ ሞዴል ፈተናዎች የአንብቦ መረዳት ክሂሎች አፈታተን የይዘትና የላህይ አግባብነትና ያጠያየቅ ዘዴዎች ብቃት ላይ ለሚደረገው ጥናት የሚያገለግሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው። ጥናቱ የተተለመውን ግብ ሊመታ የሚችለው በመምህራን ቅንና ሙያዊ ድጋፍ ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብ ሲቻል ነው። ስለዚህ በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ተገቢውን መልስ በመስጠት እንድትተባበሩኝ በትህትና እጠይቃለሁ።

የሚሰበሰበው መረጃ ለታሰበው አላማ ብቻ የሚውል ነው። ስም አይፃፍም። ለመጠይቁ የሚሰጠው መልስ በምስጢር የሚያዝ ነው።

ለሚደረግልኝ ትብብር ሁሉ በቅድሚያ አመሰግናለሁ።

I. ዳራዊ መረጃ

መመሪያ አንድ፡ እባክዎን ከተዘጋጁት ☐ ውስጥ በሚመለከትዎ ላይ " x " ያድርጉ፤ በክፍት ቦታዎች ደግሞ ተገቢውን መልስ ይፃፉ።

1. ፆታ

ወንድ ☐ ሴት ☐

2. የትምህርት ደረጃ

12 ፡ 1 ☐ ቢ.ኤ ☐

12 ፡ 2 ☐ ኤም.ኤ ☐

12 ፡ 3 ☐

3. የሰሉጠንበት የትምህርት አይነት

አቢይ	ንኡስ
አማርኛ ☐	እንግሊዝኛ ☐
ፒላንጂ ☐	አማርኛ ☐
እንግሊዝኛ ☐	አማርኛ ☐

ሌላ ከሆነ ቢገልፁልኝ? _____

4. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት _____
5. የእና መፍቻ ቁጥርዎ _____
6. አማርኛን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያስተማሩባቸው አመታት ብዛት
   አዲስ አበባ _____ ከአዲስ አበባ ውጭ _____ በድምሩ _____
7. አማርኛን ያስተማሩባቸው የክፍል ደረጃዎች /አንድ ከሆነ አንዱ፣ ካንድ በላይ ከሆኑ ያስተማሩባቸው ክፍሎች ሁሉ ይጠቀሳሉ/።

   9ኛ ☐ 10ኛ ☐ 11ኛ ☐ 12ኛ ☐

ሙያዊ ሁለት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ለእያንዳንዳቸው ከተሰጡት አምስት አማራጮች ውስጥ መልስ ነው ከሚሉት ግርጌ "x" በማድረግ ይመልሱልኛል።

ተራ ቁጥር	ጥያቄ	አማራጮች				
		በጣም አስማማ ለሁ	እስማ ማለሁ	ለመወ ሰን አቸ ገራለሁ	አልስማ ማም	በጣም አልስ ማማም
1	ከፈተናው ዝግጅት በፊት የሚደረግ የይዘትና ያጠያየቅ ዘዴ ለየታ (ዝርዝር) /specification/ ማውጣት የተለመደ ነው፣					
2	ለየታ ማውጣቱ የተለመደ ከሆነ፣ የአንብቦ መረዳት ክየሎትን በአግባቡ የሚያካትት ነው፣					
3	ጥያቄ አውጭዎች በቅሉቱ የሰፈረ መመሪያ /ምት/ /written guidelines/ አላቸው፣					
4	በሞዲል ፈተናዎቱ የሚመዘኑት የአንብቦ መረዳት ክየሎት ፡					
4.1	በመርሀ ትምህርቶቱ የተዘረዘሩት ብቻ ናቸው፣					
4.2	በመግለጥ መቆሐፎቹ መልመጃዎች የቀረቡት ብቻ ናቸው፣					
4.3	በመርሀ ትምህርቶቱና በመግለጥ መቆሐፎቹ መልመጃዎች የቀረቡት ብቻ ናቸው፣					
4.4	በመርሀ ትምህርቶቱና በመግለጥ መቆሐፎቹ መልመጃዎች የቀረቡትና በመምህራኑ ትምህርት አሰጣጥ ፒደት የታክሉት ናቸው፣					
5	የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክየሎትን ለመፈተን የተለያዩ ምንባቦትን ለመምረጥ ይሞክራል /ለምግሌ በፈጣን ያሰላ ንባብ ዝርዝር ጉዳትን ለይቶ የማመልከት ችሎታን ለመመዘን ብቻ ዝርዝር ጉዳትን የታዘ ምንባብን የመምረጥ አይነት/፣					
6	ምንባቦት ሲመረጡ፣ ጥያቄዎች ሲወጡ አድሏዊ /bias/ እንዳይሆኑ ይደረጋል፣					
7	የተለያዩ ክየሎትን ለመፈተን የተለያዩ ምንባቦትን መምረጥ የተለመደ አይደለም፣					
8	የአንብቦ መረዳት ክየሎትን ለመፈተን የሚመረጡ ምንባቦች ከለዩ ልዩ መዜኔፍት፣ መቆሌቶት፣ ጋዜጦትና ከመሳሰሉት ፡					
8.1	እንዳለ ሳይሆን ለተግሪዎት ፅድሜና ችሎታ የሚመጉ፣ ለጥያቄ አወጣጥ የሚያመቹ እንዲሆኑ ተሻሽለው ይቀርባሉ።					
8.2	እንዳለ፣ ምንም ማሻሻያ ሳይደረግባቸው ተቀንጭበው /ሙሏቸው/ ይመጸሉ።					
9	ምንባቦቱን ያጻጻፉበትና ያልተረዳ ተማሪ ሊመልሳቸው የሚችሉቸው ጥቂት ጥያቄዎች እንዲቀጻቀሉ ይደረጋል።					

የራ ቁጥር	ጥያቄ	አማራጮች				
		በጣም አስማማ ለሁ	አስማ ማለሁ	ለመወ ሰን እች ገራለሁ	አልስ ማማም	በጣም አልስ ማማም
10	ብዙ ምንባቦችን ለማካተት ጥረት የሚደረግ ቢሆንም የተማሪዎቹን አጠቃላይ ፅሁፍት የሚመለከቱ ወይም ተማሪዎቹ ቀድመው ያነቧቸው /ሊያነቧቸው የሚችሏቸው ምንባቦች/ እንዳይካተቱ ይደረጋል።					
11	የአንባቢ መረዳት ክሂሎትን ለመመዘን ምርጫ፣ እውነት ሰለት፣ ማዛመድ፣ ክፍት ቦታ መሙላት፣ መረጃ ግኙንኙ፣ አጭር መልስ መስጠት ... የሚባሉትን ያጠያየቅ ዘዴዎች መጠቀም የተለመደ ነው።					
12	የተለያዩ ያጠያየቅ ዘዴዎችን መጠቀሙ የሚለጠው ጥቅም ለለል ሙሰን ዘዴዎችን ብቻ መጠቀም የተለመደ ነው።					
13	በመግለያ መቆለፎቹ የተለግመሏቸው ያጠያየቅ ዘዴዎች ሁሉ በሞዴል ፈተናዎቹ ይንፀባረቃሉ።					
14	በመግለያ መቆለፎቹ የተለግመሏቸው ያጠያየቅ ዘዴዎች ሙሰን ስለሆኑ በሞዴል ፈተናዎቹ በቋንቋ ፈተና ተመራግለዎች ለአንባቢ መረዳት ክሂሎት ፈተና ተገቢነት አላቸው የሚባሉ ተጨግሪ ያጠያየቅ ዘዴዎችንም መጠቀሙ ጎድ ስለሆነብን ተግባራዊ አያደረግነው ነው።					
15	በጥቁሉ ክ1988 ወዲህ በየአመቱ የተሰጡት የ12ኛ ክፍል ሞዴል ፈተናዎች የአንባቢ መረዳት ክሂሎትን ለመፈተን ብቶት ያላቸው ናቸው።					

16. የሚነሰቡት አስተያየት ካለዎት? _____

<u>መመሪያ ሶስት</u>፡- አንብቦ የመረዳት ክሂሎች ትምህርት ሲቀርብ የሚከተሉት ንዑሳን የአንብቦ መረዳት ክሂሎች የመካተት ደረጃቸው የቱን ያህል ነው? ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አምስት አማራጮች ውስጥ መልስ ነው ከሚሉት ስር "x" በማድረግ ይመልሱልኛል።

ተ.ቁ ቁጥር	ጥያቄ	አማራጮች				
		በጣም እስማማለሁ	እስማማለሁ	ለመወሰን እቸገራለሁ	አልስማማም	በጣም አልስማማም
1	ቀጥተኛ ፍቺያቸውን ይዘው የገቡ ቃላትንና ሀረጎችን መፍታት፣					
2	አሻሚ / ambiguous/ ፍችዎች ያላቸውን ቃላትና ሀረጎች አውዳዊ ፍች መለየት፣					
3	እንግዳ የሆኑ /unfamiliar/ ቃላትን ፍች ከቃላት ምስረታና ከአውድ ፍንጭ /ምት/ መረዳት፣					
4	የፈጠማዊ አነጋገሮችን ትርጉም ከአገባባቸው መረዳት፣					
5	የዘይቤያዊ አገላለፆችን ትርጉም ከአውድ መረዳት፣					
6	የቀረቡና ምሳሌዎችን ትርጉም ከአውድ መረዳት፣					
7	ወኪሎችን /references/ /ምሳሌ ተውላጠ ስሞችን/ና ሌሎች አያያዦችን መረዳት፣					
8	በአረፍተ ነገሮችና በአንቀጾች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን መረዳት፣					
9	የቋሌፍን ዋና ሀሳብ በአሰላ ንባብ መረዳት፣					
10	የቋሌፍን የተለየ መረጃ በአሰላ ንባብ ማመልከት፣					
11	የአረፍተ ነገርን ትርጉም መረዳት፣					
12	የአረፍተ ነገሮችንና የአንቀጾችን ተግባቦታዊ ተግባር መረዳት፣ ለምሳሌ በሆነ፣ ምሳሌ፣ ... መሆናቸውን፣					
13	ዋና ዋና ሀሳቦችን ከንዑስ ሀሳቦች መለየት፣					
14	አውነታን ከአስተያየት መለየት፣					
15	ምሳሌን /ማስረጃን/ ከመሪ ሀሳብ መለየት፣					
16	የቋሌፉን ይዘት ማሳጠር /summary writing/፣					
17	በአንጠራ፣ በአፅዕ፣ በማራዘ ... የቀረበ መረጃን መረዳት፣					
18	ሙቀንበጽ፣					
19	ከቋሌፍ ይዘት /semantic/ በመነሳት ያለፈ ፅውቀትን ሳይጠቀሙ መረዳት፣					
20	ከቋሌፍ ፍች ሳይሰን የቀደመ ፅውቀትን በመጠቀም የመቀስቀስን /motivation/ ፣ የምክንያት ውጤትን፣ የንፅፅርን ከሂሎች ማዳበር፣					
21	እዚህ ያልተጠቀሱ ያንብቦ መረዳት ክሂሎች ካሉ /እናንተ የምታስቀምጧቸው/ እባክዎ ይዘርዝሯቸው?					
22						

መመሪያ አራት :- አንብቦ የመረዳት ክሂሎች ፈተና ሲዘጋጅ የሚከተሉት ክሂሎች ተዘውታሪነት የቱን ያህል ነው? ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አምስት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛው መልስ ነው ከሚሉት ስር "x" በማድረግ ይመልሱልኛል።

ተ.ቁ	ጥያቄ	አማራጮች				
		በጣም አስማማ ለሁ	አስማ ማለሁ	ለመወ ሰን እኞ ገራለሁ	አልስማ ማም	በጣም አልስ ማማም
1	ቀጥተኛ /የመሠረታዊ ቃላት/ ፍቻቸውን ይፀው የገቡ ቃላትንና ሐረጎችን መፍቻት፣					
2	አጸሚ ፍች ያላቸውን ቃላትና ሀረጎች አውዳዊ ፍች መለየት፣					
3	የአንባቢ ቃላትን ፍች ከአውድ ፍንጭ /ምች/ ና ከቃላት ምስረታ መለየት፣					
4	በቆራፍ ውስጥ የሚገኙ ፈሊጦችን አገባባዊ ፍች መለየት፣					
5	በቆራፍ ውስጥ የሚገኙ ጸየቢያዊ አገላለፆችን አገባባዊ ፍች መረዳት፣					
6	በቆራፍ ውስጥ የሚገኙ ቀረቶና ምሳሌዎችን ፍች ከአገባባቸው መረዳት፣					
7	ቁኪሎችንና ሌሎች አያያዦችን መረዳት፣					
8	በሐረፍቶ ነገሮችና በአንቀፆች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን መረዳት፣					
9	የቆራፍን ዋና ሀሳብ በአጭሩ ንባብ መረዳት፣					
10	የቆራፍን የተደበ መረጀ በአጭሩ ንባብ ማመልከት፣					
11	የሐረፍቶ ነገርን ትርጉም መረዳት፣					
12	የሐረፍቶ ነገሮችንና የአንቀፆችን ቀጣባይታዊ ቀጣባር መረዳት፣					
13	ዋና ዋና ሀሳቦችን ከዝርዝር ሀሳቦች መለየት፣					
14	አውነታን ከአስቀያየት መለየት፣					
15	ምሳሌን ከመሪ ሀሳብ መለየት፣					
16	የቆራቶን ይዘት አጥቅሮ መጻፍ /summary writing/ ፣					
17	ስለንሐረቹ፣ በማራፍ፣ በአህል ... የቀረበ መረጀን መረዳት፣					
18	የመቀንበጽ ክሂል፣					
19	ከቆራቶ ይዘት ፍች በመነሳት ያለፈ ልመቀትን ሳይጠቀሙ መረዳት፣					
20	ከቆራቶ ፍች ሳይሆን የቀደመ ልመቀትን በመጠቀም የመቀስቀስን የምክንያትና ውጤትን፣ የማምጣትን ክሂሎች ማሳበር፣					
21	ካላይ ከተቀረፁት ውጭ የሆኑ የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ፈተና ሲታዘጋጁ የምትጨምሯቸው ክሂሎች ካሉ ቢዘረዝሯቸው?					
22	ምንባቦችን ከአንብቦ መረዳት ውጭ የሆኑ የክሂልና/የፅሑቀት ክፍሎችን ለመመዘን የምትጠቀሙባቸው ከሆነ እባክዎ ለማየው ይጠርዝልኛው?					

አባሪ መ

በአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች

የዚህ መጠይቅ አላማ በ12ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ለመመዘን በሚመረጡት ምንባቦች፣ ከምንባቦቹ በሚወጡት ጥያቄዎችና በአጠያየቅ ዘዴዎቹ ላይ ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከት በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ ነው።

ጥናቱ የተተለመለትን ግብ ሊመታ የሚችለው ትክክለኛ መረጃ ማሰባሰብ ሲቻል ነው። ስለዚህ በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ተገቢውን መልስ በመመለስ እንድትተባበሩ ትጠየቃላችሁ።

በመጠይቁ ላይ ስም አይፃፍም። ለመጠይቁ የሚሰጠው መልስ በምስጢር የሚያዝ ነው።

መጠይቁን በመሙላት ለምታደርጉት ቅን ትብብር በቅድሚያ እናመሰግናለን።

ክፍል አንድ፣ አጠቃላይ መረጃ፤

መመሪያ አንድ፡- ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ሳጥን ባለበት ቦታ የ "x" ምልክት በማድረግ በክፍት ቦታ ላይ ደግሞ ትክክለኛውን መልስ በመጻፍ መልስ/ሽ/።

1.1 ፆታ፡- ወንድ ☐ ሴት ☐

1.2 ዕድሜ፡- 16 ና ከ16 ዓመት በታች ☐ ከ17 . 18 ዓመት ☐

ከ19 . 20 ዓመት ☐ ከ20 ዓመት በላይ ☐

1.3 የአፍ መፍቻ ቋንቋህ/ሽ/ _____

1.4 የትምህርት ቤትህ/ሽ ስም _____

1.5 ከ9 . 11 ያሉትን ደረጃዎች የተማርክበት/ሽበት/ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ ውስጥ፣ _____ከአዲስ አበባ ውጭ _____

ክፍል ሁለት፣ የፈተናውን አንብቦ የመረዳት ክሂል ክፍል በተመለከተ፤

መመሪያ ሁለት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ለእያንዳንዳቸው ከተሰጡት አምስት አማራጮች ውስጥ መልስ ነው ከምትለው/ከምትይው/ ግርጌ የ "x" ምልክት በማድረግ መልስ/ሽ/።

የቃ ቁጥር	ጥያቄ	አማራጮች				
		በጣም አስማ ማለሁ	አስማ ማለሁ	ለመወ ሰን እች ገራለሁ	አልስ ማማም	በጣም አልስ ማማማም
፡ ፩	በጥናቱ ጾታ ምዴል ፈተና ንውታዬን የሚለካ ነው።					
፡ ፪	በክፍል ውስጥ ትምህርት የተለማመድኒቸውን የአንብቦ መረዳት ክፍሎች በፈተናው እንድገለፅ የሚያደርጉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ስለቀረቡልኝ ጾሀን ክፍል ስለራ ደስ እያለኝ ነበር።					
፡ ፫	በፈተናው የቀረቡት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የሚለዳደቀውን፣ አብዛኞቼን ንውታዎች /ክፍሎች/ በክፍል ውስጥ ትምህርት ያልተለማመድኒቸው ስለሆኑ ለመመለስ ተቸግሬ ነበር።					
፡ ፬						
፡ ፭	የአንብቦ መረዳት ክፍል ጥያቄዎች መመሪያዎች /instructions/ ግልፅ ናቸው።					
፡ ፮	ለዚህ ፈተና የተፈቀደው ጊዜ በቂ ነው /አልበዛም __ አላነሰም/					
፡ ፯						
፡ ፰	ምንባባቱ ሁሉም ከወደውና ስለነበር ጥያቄዎቹን ለመመለስ ተቸግሬ ነበር።					
፡ ፱	የፈተናው ርዝመት ተገቢነት ያለው ነው። /አልረዘመም፣ አላጠረም/					
፡ ፲	የተለያዩ ቋሚዎችን የሚወክሉ የተለያዩ ምንባቦች ተመርጠው ለአንብቦ መረዳት ክፍሎች መመዘኛ እንዲያገለግሉ መደረጉን ወደደዋለሁ።					
፡ ፲፩	ከየቋሚው ቋሚዎች የተወሰኑ ምንባቦችን ብቻ ያካተተ ፈተና ስመሆኑ አልወደደኩትም።					
፡ ፲፪	በመግለፆ መዝሐፉ መጨመጃዎች የተለማመድኒቸው ምርጫ እመነት (ዕውነት) ክፍት ቦታ መላ፣ አጭር መልስ ሰጥ፣ አሳጥረህ ግፃ፣ አዘምድ፣ ያሐያዩ ዘዴዎች ተቀላቅለው የቀረቡበት ምንባቦ መረዳት ክፍሎች አፈታተን ስለሆነ ወደደዋለሁ።					
፡ ፲፫						
	የተለያዩ ያሐያዩ ዘዴዎችን ከመጠቀም ይልቅ ከሁለትና ሦስት ያልበለጡትን ብቻ መጠቀሙን አልወደደኩትም ።					
	ምንባባቱና ከምንባባቱ የወጡት ጥያቄዎች ለ፲፯ ክፍል ተማሪ የሚሥማኑ ናቸው።					
	የፈተናውን የአንብቦ መረዳት ክፍል በተመለከተ አስተያየት ካለህ/ሽ/ በተሰጠው ክፍት ቦታ መጻፍ ይቻላል።					
	_____					
	_____					
	_____					
	_____					
	_____					
	_____					
	_____					
	_____					
	_____					
	_____					

17

ከከበ ጽባሕ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አዲስ አበባ
የ1987 ዓ.ም የዓመቱ ማጠቃለያ የአማርኛ ፈተና
ለ11ኛ ክፍል

የተፈቀደው ጊዜ 90 ደቂቃ

ማሳሰቢያ የጥያቄዎቹን መልስ በመሉ ለመልስ መስጫ በተዘጋጀልህ ቦታ ላይ አመልክት።

ክፍል አንድ ምንባብ

.... ያለምንም ጉርምርምታ ፀጥ ብሎና የሰላማዊነትን ግርማ ሞገስ ተጎናጽፎ ከሚንዣቀዣቀው ዝናብ ለማምለጥ በየቤቱ ጥግ የተጠለለው መንገደኛ ወጨፎና ወጀብ ባለመኖሩ ዘና ብሎ ቁሟል። ከዝናቡ ጋር ፉክክር የያዙ የሚመስሉ መንገደኞችም ልብሳቸውን ሰብሰብ አድርገው ሊሮጡ አልፎ አልፎ ይታያሉ።

ዕውሩ ለማኝ አባ አያሌውም እኩፋዳቸውን አቀፈው ፣ ድሪቷቸውን እስከ ቅንድባቸው ተከናንበው ጭብጥ ብለው ተቀምጠው እንጀት የሚበላ እንጉርጉሯቸውን ሲያጓጕዱት ረጋ ካለው የዝናብ እወራረድ ጋር ተቀነባብሮ እልም ካለ ርሃብ ዱር ይጨምራል። ያለፈው ህይወታቸው ትዝታ ዓዙን ጠቅልሎ ማንጎበብ የሚጀምረው ገና ዝናብ ሊመጣ ማጉረምረም ሊጀምር ነው። እንጀ ጊዜ መዝፈን ከጀመሩ ደግሞ ግጥም አያልቅባቸውም። ጕሮሮአቸው አደጫክርባቸውም። ያላለፉት የህይወት ዘመን በግጥም እየተንዶለዶለ የሚፈስላቸው እንጂ በአማግሌ ጭንቅላታቸው ተቀነባብሮ የሚቀርብ አይመስልም።

እንጉርጉሯቸው ልቤን ሰልቦኝ ስለእናታቸው ፣ ስለቤተሰባቸውና ስለሀገራቸው፣ ስለወንዙ፣ ስለጻሩ ሲያንጎራጉሩ ፣ የወላጆቼ ቤተ አፈር ፈጭቼ ፣ ውሃ ቀድቼ ያደግሁበት ባዕድ ሰው የሌለበት ሰፈሬ ወንዙ፣ ጻሩ በዓይነ ህሊናዬ ሲያንዣብብብኝ፣ ዜማቸውን ቁየር አደረጉና ስለ ከንፈር ወጻጅ፣ ስለልጅነት ፍቅር ሲያዝጉደጉዱት እንደገና ልቤን እንደቦይ ውሀ ነድተው ከፍቅር ዓለም ውስጥ አስገቡኝ።

/ያልተሸጠ ሰደጣን ገጽ 128 እስከ 129/

በምንባቡ መሠረት መልስ

___1. በምንባብ ውስጥ የተገለጸውን ዝናብ ሁኔታ የሚያመለክተው ሀረግ የትኛው ነው? ሀ/ ወጀብማ ዝናብ ሐ/ በረደማ ዝናብ
ለ/ ጸፍ ዝናብ መ/ ካፊያ ዝናብ

___2. በምንባቡ ውስጥ " በየቤቱ ጥግ" የሚለው የሚተካ ሀረግ የቱ ነው?
ሀ/ በየቤቱ ሥር ለ/ በየቤቱ ጕን ሐ/ በየቤቱ ጓዳ መ/ በየቤቱ ጓሮ

___3. ምንባቡ " የተጠለለው" የሚለውን ቃል የሚተካ የቱ ነው?
ሀ/ የተጠጋ ነው ለ/ የተከማቸ ነው ሐ/ የተከለለው መ/ የተሰበሰበው

/ ___4. በምንባቡ ውስጥ " ከዝናቡ ጋር ፉክክር የያዙት" የተባሉት እነማናቸው?
ሀ/ በዝናብ ውስጥ የሚጓዙ ስፖርተኞች ሐ/ በዝናብ ውስጥ የሚያንጎራጉሩት
ለ/ ከዝናቡ የተጠለሉት ሰዎች ሸማግሌ
መ/ በዝናብ ውስጥ የሚጓዙ ሰዎች

___5. በምንባቡ ሁለተኛ አንቀጽ ውስጥ " የሀሣብ ዱር" የሚለው ሐረግ ምን ማለት
ነው? ሀ/ የሀሳብ ቅዠት ሐ/ ያለፈ ትዝታ
ለ/ የበረሃ ሀሳብ መ/ የሰመመን አንቀልፍ

/ ___6. አባ አያሌው ተቀምጠው የሚያንጎራጉሩት የት ነው?
ሀ/ እመንገድ ዳር ሐ/ አቤቱ ጥግ
ለ/ እመንገድ መሀል መ/ ቦታው አልተገለጸም

___7. በምንባቡ ሶስተኛ አንቀጽ ውስጥ " ልቤን ሰለበኝ" ሲል____ ለማለት
ነው። ሀ/ ልቤን ሰርቆኝ ሐ/ ሰመመን አስይዞኝ
ለ/ ቀልቤን አሳጥቶኝ መ/ ትካዜ አሳድሮብኝ

/ ___8. ከእውሩ ለማኝ የማይጠበቀው ምንድነው?
ሀ/ ሰለ አለማዊ ጉዳይ ማንጎራጎራቸው
ለ/ ዝናብ ውስጥ ቁጭ ብለው ማጎንጎራቸው
ሐ/ ሊያንጎራጉሩ ጉሮሮአቸው ያለመጻከሩ
መ/ ስለ ሕይወት ዘመናቸው በግጥም ማሰላሰላቸው

___9. በምንባቡ ውስጥ " ልቤን ሰልቦኝ" የሚለውና " ልቤን እንደ ቦይ ውሀ
ነድተው" የሚሉት ሀረገች እገባባቸው እንጻት ነው?
ሀ/ ተቀራኒ ናቸው ሐ/ ተጻጋጋፊ ናቸው
ለ/ ተመሳሳይ ናቸው መ/ ግንኙነት የላቸውም

___10. በምንባቡ ውስጥ ያሉት ገፀ ባህርያት ስንት ናቸው?
ሀ/ አንድ ለ/ ሁለት ሐ/ ሶስት መ/ አራት

___11. መንገደኞች ልብላቸውን ሰብስብ እድርገው ሲሮጡ የሚለው____ነው::
ሀ/ለማድረቅ ያሰቡት ነው ሐ/ የለበሱትን ነው
ለ/የተሸከሙትን ልብስ ነው መ/" ሀ" ና " ሐ" መልስ ይሆናሉ

___12. አባ አያሌው ያቀፉት እቦፋጻቸው የተባለው____ ነው::
ሀ/ ቦርጫቸውን ሐ/ እቀማጻቸውን
ለ/ ሥልቻቸውን መ/" ለ" ና " ሐ" መልስ ናቸው

___13. " ጭብጥ ብለው" የሚለውን የሚተካ ሀረግ____ነው::
ሀ/ ክንብንብ ብለው ሐ/ ኩርፍ ብለው
ለ/ እንጉብሰው መ/ ኩርምት ብለው

___14. ከዝናቡ ጋር ፉክክር የያዙት____ ናቸው::
ሀ/ አባ አያሌው ለ/ ዜማዎቹ ሐ/ ተላላፊዎቹ መ/ ስፖርተኞቹ

___15. " ባዕድ ሰው የሌለበት" ሲል____ ለማለት ነው::
ሀ/ እንግዳ ሳው ለ/ጸጉረ ልውጥ ሐ/" ሀ" ና " ለ" መ/ መልስ የለም

1987 ዓ.ም

16. አባ አያሌው የአድማጫቸውን ልብ እንደቦይ ነድተው የከተቱት____ነው።
ሀ/ ወደ ወላጆቹ መንደር ሐ/ ወደ ጉቅር ዓለም
ለ/ ወደ አደገበት አካባቢ መ/ ሁሉም መልስ ናቸው

17. አባ አያሌው ለየተንደለደለ የሚፈስላቸው ግጥም_____ነው።
ሀ/ስለ እናታቸው ለ/ስላለፈ ህይወታቸው ሐ/ስለወንዙ መ/ስለዱሩ

18. " በዓይነ ህሊናዬ" በሚለው ውስጥ " ዓይነ ህሊና" የሚለው_____ቃል ነው።
ሀ/ድርብ ለ/ ነጠላ ሐ/ ህዳግ መ/ነጠላና ድርብ

19. " ሊያንሾጮጮዱት" የሚለውን_____መተካት ይቻላል።
ሀ/ሊያክለፈልፉት ለ/ሊያከታትሉት ሐ/ ሊነዱት መ/" ሀ ና ለ" መልስ ናቸው

20. " የሚያንረመርም" የሚለው ቃል የገባው_____ለመግለጽ ነው።
ሀ/ እንጉርጉሮውን ለ/ዝናቡን ሐ/አባ አያሌውን መ/ትካዜን

ክፍል ሁለት

ለሚከተለው ተረትና ምሳሌ እቹ ሊሆን የሚችል ሌላ ተ/ምሳሌ ምረጥ

21. " ልጅ እደነድ አንድ አደራርድ"
ሀ/ ሠርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ
ለ/ ለማኝ እያማርጥም ማር እደኮመጥጥም
ሐ/ ካልታረደ እደታይ ሰባቱ ካልተናገሩ እደገኛ ብልሃቱ
መ/ ሁሉም መልስ ይሆናል።

22. " ነጋር ከሰነበተ ጠላ ከሻገተ"
ሀ/ ዲያቆን ከዘፈነ ፍየል ከቀዘነ
ለ/ ብርሌ ከነቀ እደሆንም ዕቃ
ሐ/ ካረጁ እደበጁ
መ/ ሁሉም መልስ ይሆናል።

23. "ሞር ለውርወራ ገንዘብ ለሥራ"
ሀ/ እገደ ወንዙ ደሻገሩ እንደ አገሩ ደኖሩ
ለ/ ለምሽት መብራት ለመከራ ጊዜ ብልሃት
ሐ/ ሥራ ለሰሪው እሾህ ለአጣሪው
መ/ መልሱ አልተሰጠም

24. ሐምሌ ቢያባራ በጋ ደመስላል
ሀ/ በሰጋ እሞኝ ቤት ተንጋጋ
ለ/ የበሬ ሆዳም ቢሞት እደጎጃም
ሐ/ የድመት ማንቀላፋት እደጦቾን ለማጥፋት
መ/ የሞኝ ለቅሶ መልሶ መላልሶ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 2ኛ ደረጃ ተ/ቤት

የ12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሙያ ፈተና የካቲት 1987

1. የሚከተሉትን ሁለት ጽንሰሐሾች አገባብህ ከ1_25 የተዘረዘሩትን ዋ ያቀፃቸ በሆንበት መሠረተ መልስ ::

ም ን ባ ብ 1

ልርሰተ ግለሰ ታሪክ፣ ቂለተር ፀሐፊዎች፣ ባለቀ ኔዎች፣ ሊቃውንት፣ ፈላሥፍች የሚፅፏቸው መጻሕፍተ ፣ ናቸው :: ሐዝቦች በሥለጣኔ በኩል ያረጉትን ርምጃ ብንመለከተ በታ ሪክ ቸው ውስጥ የሥለጣኔ የልርሰተ ዙ ዎች በቀርብ የተያያዙ የተቀራኙ፤ የተጣሰሩ . ሆነው ይገኛሉ :: ለንቡ ሕዝብ በሥለጣኔ ጉዳ መጋዝ ሲደምር ,በሕይወተ ምለራፍች ጉለህ ሂነው የሚታዩ ልርሰ ቶች ፣ ናቸው :: የሕዝቡ መገፈሰ ለዲስ ገፃተ የሚያገኘው ሰሚቱ . ለዲስ ወኑ የሚፈተረው፤ ለስተያየቱ ለዲስ ሕይወተ የሚወስነው በጠቀሲሳው የሰዝቡ ሕይወ ለዲስ ተርጉም፤ መገፈሰም ለዲስ ገቀ፣ ቲ የሚ'ረው ፀሐፊዎቹ በሚያፈራ ዋቸው ልርሰ ቶች ለማበይነተ ነው ::

የለንቡ ልርሰተ ዋጋ በሠስተ ነገር'ች ላይ ይመሠረታል :: ለንደ'ኛ የፀሁፉ ውነተ፤ ሁለ ኛ' የሰባቡ ፍሬ ነገር፤ ሦስ ተኛ' የተዋቀረ ለ ፃራረብ ፣ ቸው :: በልርሰተ ሥራ ውስጥ የሚገኙተ የቃሬተ ዝርዝር ነገር'ች ሁሉ ለለ ነዚህ ለሠስ ቱ መሠረታዊ ነገር'ች ለንደ ዘርፍች ሆነው ይቀመራሉ ::

ለንቡ ሰው ለልርሰተ ውስተ ሊሰጠው የሚቻለው ባለሙያ ሲሆን ነው :: ይህን የመሰለው ሙያ የሚገኝው በ'ስየለ ብቃ ነው :: ሥጠ ታም ለብር ይወለጻል ለንጂ በተምሀርተ ሊያገኙተ ለይታለም :: በተምሀርተ ሊገኝ ቢታለማ ,'ር ስየቡኒቨርሰቲው በያመ የሚወሰተ በሰዙ ሺህ የሚቀረ'ተ ተማሪዎች ሁሉ ደራሲያን ይሆኑ ነበር :: ነገር ግን ልርሰተ በሥስታ ብቃ የሚገኝ በመሆኑ በየዘመኑ የሚነቡተ ደራሲያን ቁጥራቸው በጣም ያነ ሂ' የሚታወስት ሲለዚህ ነው ::

የደራሲ ሥስታ የሚመነጨው ከሰዓተ ነው :: የደራሲ ሰዓተ ተታኝቶ ለንደ ተቋመጠ በገ' ደ ቀመራል :: የተታኝ ባገ' ፕ ቂተ ነገር ሲነሳው ልምፅ ይሰጣል፤ ደምፅም ያምራል ለጆር ይሳፍሳል :: ደራሲም በዓቱ ለገጂ'ቀስቀስ ለማድረግ ተገሽ ነገር ይበቃዋል :: በዓቱም በ'ቂ ወጠ ጊዜ በውስ ልርሰተ ልምፁን ያስማል ::

ሳገ'ውም ልርሰተ በወሰው ተምሀርተ ከሌለው ዋጋው ገደሉ ይሆ'ል :: ለንድ ልርሰተ ለጅግ ውስ ሆ' ውስው ገለሰ ሊሆን ይችላል :: የቃለ ተ ለስከስ የልርሰ ተ ጥራተ በሰቀሳሳው የፀሁፌ ለ ፃራረብ ለገስን የሌለው ሆ' ሳለ በውስጡ ምንም ነገር ካለያዘ የልርሰ ተ ዋጋ ሰማንያ ከመ'ቱ ገደሉ ነው ለያለ ይቻላል :: ዋ ው ጥያቄ መሠረታዊ ነገር ከ የ'ተ ይገ'ለ ከሚለው ላይ ነው :: ብዙ በማንበብ፤ ብዙ በማሲብ፤ ብዙ በመመለከተ፤ ባያ በባለሀነተ ይገ'ለ :: ይህ ጉዳይ ለለገደላቸው ብዙ ደራሲያን ልርሰ ታቸው ለጥ ቂተ ጊዜ ከ ተወደደ በኋላ ወዲያው ምንም ያህለ ሳይቀይ እየተረሳ ሔደ ጠርቦ ይም ታለ ::

1. ለምንባቡ ተስማሚ ርእስ ___3___ ነው :: ሀ/ የልርሰተ ለጻጻፍ ለ/ ልርሰተ ሐ/ ልርሰተና ሥለጣኔ መ/ የልርሰተ ፕበብ

2. ሰደራሲው ለስተያየተ ልርሰተ ___1___ ፀሁፍ ነው ::
ሀ/ ውስ የሆነ ለጆ ምርጥ ታሳተን የያዘ ሐ/ በወረቀተ ላይ የሠፈረ
መ/ ሙ'ነገር ያዘለ

.../2

3. ፀር በተ ለአገሯ ሕዝብ ጠቀሳሳ አደጋ-መከላከያ ሊሆን ይችላል የሚባለው _____ ነው
ሀ/ የፀር በተ መሥፈርት ጠቀሳሳ አደገተን ስለሚያስከትል
ለ/ የፀር በተ መስፈርት ከጠቀሳሳ አደገተ ስለሚቀደም
ሐ/ ጠቀሳሳ አደገተ የፀር በተ መስፈርተን ስለሚያስከተል
መ/ ጠቀሳሳ አደገተ፣ የፀር በተ መስፈተ ስለማይነጠሉ

4. በደራሲው ለስተያየተ የስዘብ ሕይወተ ለዚህ ተርጉሞ፣ ጠይለ የሚያገኘው 1 ነው ::
